# ምስክሮቼ ትሆናላችሁ

2007

ዶ/ር እያሱ ፈረንጅ

27/01/2016
ኢያሱ ፈረንጅ (ዶ/ር)

# ምስክሮቼ ትሆናላችሁ

በዶ/ር ኢያሱ ፈረንጅ
2007 ዓ.ም

ምስክሮቼ ትሆናላችሁ

በዶ/ር ኢያሱ ፈረንጅ

አሳታሚና አከፋፋይ ዶ/ር ኢያሱ ፈረንጅ

2007 ዓ.ም

ስልክ- የቢሮ 0115505907

ሞባይል- 0911468460

ኢሜይል- eyasuferenj@gmail.com

ከዚህ በፊት በደራሲው የተጻፈ

ዘመን ተሐድሶ

ይህን መጽሐፍ በትምህርተ ጥቅስ ካልሆነ በስተቀር ያለ ደራሲው ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት የተከለከለ ነው።

## መታሰቢያነቱ

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ በወንጌል አገልግሎት እየተጋደሉ ላለፉትና አሁንም በመጋደል ላይ ላሉ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የወንጌል አርበኞች ሁሉ ይሁን።

## ምሥጋና

ይህን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየት የሰጡትን ፕሮፌሰር ተክተል ዮሐንስን፤ ዶ/ር ወንዱፊራው አድነውንና ዶ/ር ኤርሚያስ ማሞን፤ የፊደላትንና የኮምፒውተር ጽሑፉን ግድፈቶች በማስተካከል ልቅም ያለ ሥራ የሠራችውን ወ/ሮ ነጻነት ጴጥሮስን ጌታ አብዝቶ ይባርካቸው።

## ማውጫ

**ገጽ**


መግቢያ ........ 2

ምዕራፍ አንድ፦ የወንጌላዊነት አገልግሎት ........ 5

1. የወንጌል ስርጭት ትርጉም ........ 5
2. ወንጌላዊ ማነው? ........ 10
3. የወንጌላዊ መሰያዎች ........ 19
4. የወንጌላዊው መልእክት ........ 26
5. የወንጌል ስርጭት ዘዴ ........ 37
6. የኢየሱስ ክርስቶስ ስልት ........ 66
7. የጳውሎስ የወንጌል ስርጭት ስልት ........ 81
8. የወንጌል ስርጭት ስሕተቶች ........ 90
9. የወንጌል ስርጭት ቁልፎች ........ 94

ምዕራፍ ሁለት፦ የወንጌል ተልዕኮና አውዳዊ አገልግሎት ....... 107

1. ባሕል ምንድነው? ........ 107
2. ኢየሱስ ክርስቶስና ባሕል ........ 113
3. ወንጌልና ባሕል ........ 119
4. የሌላውን ባሕል መልመድ ........ 123
5. በባሕል ተጽዕኖ መጨነቅ ........ 128
6. በባሕል ተጽዕኖ መጨነቅን ማስቀረት ........ 133
7. አውዳዊነት ........ 137
8. ተግባቦት ........ 143

ምዕራፍ ሦስት፦ ምዕመናን በወንጌል ምስክርነት ........ 152

1. ምዕመናን እነማን ናቸው?........ 153
2. የምዕመናን የወንጌል ተልዕኮ ........ 156

ማጠቃለያ ........ 189

ዋቢ መጻሕፍት ........ 191

## መግቢያ

"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" የሐዋ. 1:8

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ትዕዛዝ ያዘዘው ከትንሣኤው በኋላ ወደ አባቱ ሊሄድ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት ነበር:: ይህ ትዕዛዝ ሁለት አበይት መልእክቶች አሉት::

የመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የሚሰጥበት ዋነኛ ምክንያት የክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣዔ ምስክሮቹ እንዲሆኑ ኃይልን ለመስጠት ነው:: የትኛውም አገልግሎት ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊከናወን ይችል ይሆናል፤ፍሬያማ ሊሆን ግን አይችልም፤ ኃይል አይኖረውምና:: ኃይል ከሌለው ደግሞ ሥርዓት ብቻ ስለሚሆን የሕይወት ለውጥ ሊኖር አይችልም:: ከአገልግሎቶች ውስጥ ቀዳሚው ደግሞ የወንጌል ምስክርነት ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚከናወኑ አገልግሎቶች ኖረው የወንጌል ምስክርነት ከሌለ ትልቅ ኪሣራ ነው::

ሁለተኛው የወንጌል ምስክርነቱ በኢየሩሳሌም ተጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ መቀጠል እንዳለበት ነው:: ለዚህ ነው የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት በኢየሩሳሌም የጀመሩት የወንጌል ሥራ ዛሬ በዓለም ሁሉ የደረሰው:: የኢትዮጵያን



ቤተ ክርስቲያናት የወንጌል ምስክርነት ስንመለከት ወንጌል አሁን ያለበትን ደረጃ የደረሰው የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ያመኑ ሁሉ ይመሰክሩ ነበር:: ይህ ወንጌል በፍጥነት እንዲሮጥ ተወዳዳሪ የሌለው ዘዴ ነው:: ነገር ግን በብዙ ቤተ ክርስቲያናት በአሁን ጊዜ ከወንጌል ምስክርነት ይልቅ በዝማሬ፤ በአምልኮ፤ በፈውስና በመሳሰሉት በጸጋ ስጦታዎች አገልግሎት በመሟሟቅ ረክቶ መኖር የተለመደ እየሆነ መጥቷል:: የወንጌል ምስክርነት በበጀትም ሆነ በአገልግሎት ትኩረት እጅግ አነስተኛ ሥፍራ እየተሰጠው ነው:: ከዚህ ጋር አብሮ የሚታየው አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ጥሩ የወንጌል ምስክርነት አገልግሎት ቢኖራቸውም ከኢየሩሳሌም (ከአጥቢያቸው) መውጣት ግን አልቻሉም:: የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በአሁን ጊዜ ወደ 1,091 በመላው የአገሪቱ ክፍሎች የተሰማሩና ከአገር ውጭ አሥራ አምስት ቤተሰብ ሚስዮናውያንን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የገንዘብ ድጋፍ በማሰማራት ቀዳሚ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይሁን እንጂ በብዙ አጥቢያዎች የወንጌል ምስክርነት አገልግሎቱ እየተዳከመ መምጣቱ ግን ሊታሰብ የሚገባ ጉዳይ ነው::

በመሆኑም ይህ መጽሐፍ ከኢየሩሳሌም እስከ ምድር ዳር ድረስ ለሚኖረው የወንጌል ተልዕኮ ሦስት ዓላማዎችን ትኩረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው::

አንደኛው ለወንጌል አገልግሎት ራሳቸውን ለሰጡ ወንጌላውያን በቂ ማጣቀሻ አለመኖሩ ዋነኛ ችግራቸው ስለሆነ ይህንን ችግር መቅረፍ ነው:: ወንጌላውያን በግላቸው መመስከር ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ለዚሁ ዓላማ መቀስቀስ፣ ማሠልጠንና ማሰማራት አለባቸው:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ ተገቢውን መሣሪያ በእጃቸው ለጥቶ ማሰማራት በእጅጉ ይጠቅማል::

ሁለተኛው ወንጌላውያን ከአንድ ባሕል ወደ ሌላ ባሕል ሲሄዱ ሦስት ነገሮችን ለማስታረቅ ይገደዳሉ፣ የማይለወጠውን የወንጌልን እውነት፣ የኖሩበትንና ያደጉበትን የራሳቸውን ባሕልና የሚሄዱበትን አዲስ ባሕል አንድ ላይ ስለሚይዙ እንዴት አድርገው የወንጌሉን እውነት ሳይሸቃቅጡና ከሄዱበት አካባቢ ባሕል ጋር ሳይጋጩ ማገልገል እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው::

ሦስተኛው የወንጌል ምስክርነቱን ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች የተው ምዕመናንን ለማነሳሳትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማደፋፈር ነው:: እያንዳንዱ በክርስቶስ አምኖ የዳነ አማኝ የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት ለሌላው መመስከር አለበት:: ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታም ነው:: ይህች መጽሐፍ ይህንን ክፍተት ትሞላለች ተብሎ ይታመናል::



# ምዕራፍ አንድ
# የወንጌላዊነት አገልግሎት

ወንጌላዊና የወንጌል አገልግሎት የተሰኙት ቃላት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ በሰፋት የተለመዱና ተደጋግመው የሚሰሙ ቋንቋዎች ናቸው:: ወንጌላዊ ሲባል በብዙ አማኞች ዘንድ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን ሁሉ ሲመለከት፣ ለአንዳንዶች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተመረቀን ሁሉ ያካትታል:: በአንዳንዶች ዘንድ ሰባኪ ሁሉ ወንጌላዊ ተብሎ የሚጠራበት ሁኔታም አለ:: የወንጌል ስርጭትም እንዲሁ በብዙ መልክና ሁኔታ ይታያል:: እነዚህን ሁለት ነገሮች ለይቶና አጥርቶ ማየት ለወንጌል ስርጭት በጣም አስፈላጊ ነው::

## 1. የወንጌል ስርጭት ትርጉም

የወንጌል ስርጭት የሚለው ሐረግ በተለያየ መልክ የተብራራ ቢሆንም ሁሉም አንድ ዓይነት አሳብ አላቸው::

ቤን ካምፐቤል ጆንሰን የተባለ ጸሐፊ እንዲህ ብሏል::
የወንጌል ስርጭት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን የፍቅር ምሥራች ሰዎች በመረዳት በክርስቶስ እንዲያምኑና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነው ትዕዛዙን እንዲፈጽሙ ማድረግ ነው::
አንድ መዝገበ ቃላት ደግሞ የወንጌል ስርጭትን እንዲህ ሲል ተርጉሞታል::

ወንጌልን ማስራጨት ማለት መጽሐፍ እንደሚል ኢየሱስ ክርስቶስ ስኃጢአታችን እንደሞተና ከሞትም እንደተነሣ፤ አሁን ሁሉን የሚገዛ ጌታ ሆኖ በእርሱ ለሚያምኑና ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙት የኃጢአትን ይቅርታ እንደሚሰጥና ከኃጢአት ባርነት ነጻ እንደሚያወጣ የምሥራቹን ቃል ማወጅ ነው::

ሮጀር ግርንዌይ የተባለ ጸሐፊ ደግሞ

የወንጌል ስርጭት ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው እንዲድኑ የሚነገር የምሥራች ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝና ጌታ መሆኑና ደቀ መዛሙርቱ የሆኑት ደግሞ አሮጌውን ኑሮአቸውን ትተው አዲስ ሰው መሆናቸው የወንጌላት ማዕከላዊ እውነት ነው:: ስለዚህ የወንጌል ስርጭት ግቡ ያለ ጥያቄ ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ አምነው እንዲድኑ ማድረግ ነው:: ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ ወንጌል መልእክት ጥሪው በሐዋ. 26:18 ሲናገር "የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ" ብሏል::

በፓውል ሽልንግ አገላለጽ ደግሞ የወንጌል ስርጭት ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች ቃል ሰምተው እንዲያምኑ በቃልና በተግባር ማወጅ ነው:: ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲቀበሉና እንዲኖሩበት የማድረግ ሥራ ነው:: ይህም ሦስት ግቦች አሉት::



1. የወንጌል ስርጭት ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተዋወቅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው::
2. የወንጌል ስርጭት ሰዎችን በክርስቲያን ኅብረተሰብ ውስጥ (በቤተ ክርስቲያን) በንቃት በመሳተፍ አንዱ ሌላውን እንዲያንጸውና ከመንፈስ ቅዱስ እንዲማሩ ማድረግ ነው::
3. የወንጌል ስርጭት ሰዎችን ሁሉ ሁለንተናቸውን ለእግዚአብሔር እንዲገዙ ማድረግ ነው:: ይህም ሰዎች ሁሉ ሕይወታቸው ተለውጦ ለፈቃዱ እንዲገዙ ማድረግ ነው::

እንደ ጆርጅ ፔተርስ አባባል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የወንጌል ስርጭት ትርጉምን በትክክል የምንረዳው ከወንጌል ጋር የተያያዙ ሦስት የአዲስ ኪዳን ጥቅሶችን ስንመለከት ነው::

1. "ወንጌል" የሚለው ቃል የምሥራች ቃል ማለት ነው:: ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ 76 ጊዜ ተጠቅሷል::
2. ሌላው ቃል ወንጌልን መስበክ የሚለው ሲሆን የምሥራቹን ቃል ማወጅ፤መግለጥ ወይም ማስታወቅ ማለት ነው:: ይህም ቃል በእዲስ ኪዳን 51 ጊዜ ተጠቅሷል::
3. ወንጌላዊ የሚለው ቃል ደግሞ የምሥራቹን ቃል የሚያውጀውን ሰው ያሳያል:: ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል (የሐዋ. 21:8፤ ኤፌ.

4:11፤ 2ጢሞ. 4:5)። ነገር ግን የወንጌላዊነት ተግባር ሐዋሪያ በሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 15: 1-11 የወንጌል መልእክትን እንዲህ ሲል በግልጽ አስቀምጦታል። «ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ። . . . መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ . . . እንግዲህስ እኔ ብሆን እነርሱም ቢሆኑ እንዲሁ እንሰብካለን፤ እንዲሁም አመናችሁ» ያለው እውነት የወንጌል ስርጭትን ትርጉም ጥቅልል አድርጎ ያስቀምጣል። እንደ ጳውሎስ አገላለጽ የወንጌል ስርጭት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንደሞተ፤ እንደተቀበረ፤ እንደተነሣና ዳግመኛ ለፍርድ እንደሚመጣ በማወጅ ሰዎች ሁሉ በዚህ ጌታ አምነው ከፍርድ እንዲድኑ ማወጅ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የወንጌል ስርጭት አምስት በጣም አስፈላጊ ሐሳቦችን እንደያዘ ፕራካሽ የሱዲያን የተባለ የሕንድ ምሁር ጽፏል። እነርሱም:-

ሀ. *ወንጌል ለሰው ሁሉ የሚነገር የምሥራች ቃል ታሪክ ነው።* ይህ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ፤ ለሚያውቁት ሁሉ ሥልጣን የሚሰጥ፤ በሐዋሪያት የተሰበከና ለእያንዳንዱ ሰው የሚነገር ቃል ነው።

ለ. *አንዳንድ አማኞች ወንጌልን እንዲሰብኩ የተለየ ስጦታ ተሰጥቶአቸዋል።* ይህ ማለት የወንጌል ስብከት ስጦታ የተሰጣቸው ሁሉ ደካማ ጎን የሌለባቸው ፍጹም ሰዎች ናቸው ማለት አይደለም። ጢሞቴዎስ የራሱ ደካማነት ቢኖረውም ጳውሎስ የወንጌላዊነትን ሥራ እንዲፈጽም ልኮታል። ነገር ግን ስጦታው ያለው ሰው በክርስቶስ አምኖ የዳነ፤ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ያለው፤ ተግቶ የሚጸልይ፤ ለሚጠፉት የሚገደውና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመራ መሆን አለበት። እንደዚያ ከሆነ እግዚአብሔር ደካማነቱን አልፎ ይጠቀምበታል።

ሐ. *ወንጌልን መስበክ የኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ ነው።* አማኝ ሁሉ ወንጌልን በመመስከር የጌታችንን ትዕዛዝ መፈጸም አለበት። ትዕዛዙ ሥልጣንንም ይሰጣል። ጌታችን ኢየሱስ «ሂዱ . . . ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» (ማቴ. 28:19-20) ሲል ባለ ሥልጣኑ ጌታ ከላክ በኋላ አብሮ እንደሚሄድ አረጋጋጭ እውነት ነው።

መ. *የወንጌል ስርጭት አንድ ሰው ለብቻው የሚሠራው ሥራ አይደለም*። ጌታችን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን መረጣቸው፤ አሠለጠናቸው፤ ጸለየላቸው፤ አስተማራቸው፤ አስማራቸው፤ ሲሳሳቱ አረማቸው፤

አለማመዳቸው፤ አብሮአቸው እንደሚሄድም ቃል ገባላቸው። ይህ ጌታ ዛሬም አብሮ ይሠራል። ስለዚህ የወንጌል ስርጭት ሰው ከእግዚአብሔር አብ፤ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚሠራው የቡድን ሥራ እንጂ ብቻውን የሚሠራው ሥራ አይደለም።

ሠ. *የወንጌል ስርጭት ሁል ጊዜ አዳዲስ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማምጣት ነው።* የወንጌል ስርጭት ሰዎችን ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ማገላበጥ ወይም ማዛወር አይደለም፤ በመዋሰድ መብዛትም የወንጌል ስርጭት አይደለም። የወንጌል ስርጭት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማያውቁ አዳዲስ ሰዎችን የወንጌልን እውነት ሰምተው በእርሱ አምነው እንዲድኑ ማድረግ ነው።

## 2. ወንጌላዊ ማነው?

ወንጌላዊ ማለት ስጦታ ያለው፤ ሙሉ ጊዜውን ወንጌልን ለመስበክ የሰጠ ሰው ነው። ብዙ ሰዎች መጋቢያንን ወንጌላዊ ብለው የሚጠሩበት ጊዜ አለ፤ የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከ ሁሉ ወንጌላዊ የሚባልበትም ሁኔታ አለ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተመረቀ ሁሉ ወንጌላዊ እየተባለ ይጠራል። ይህ አለመረዳት የሚከሰተው በአብዛኛው የእግዚአብሔርን ቃል በማያውቁት ሰዎች ዘንድ ነው። ወንጌላዊ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል፤ ወንጌላዊው



ፊልጶስ (የሐዋ. 21:8)፤ የወንጌላዊው ስጦታ (ኤፌ. 4:11)፤ የወንጌላዊነት ሥራ (2ጢሞ. 4:5)።

### ሀ. ወንጌላዊው ፊልጶስ (የሐዋ.21:8)

ሐዋ. 21 ፊልጶስ ወንጌላዊ እንደሆነ ይነግረናል። «በነጋውም ወጥተን ወደ ቂሣሪያ መጣን፤ ከሰባቱም አንድ በሚሆን በወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ገብተን በእርሱ ዘንድ ተቀመጥን»። የእርሱን ስም መጀመሪያ የምናገኘው በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ለዲቁና አገልግሎት በተመረጡ በሰባቱ መካከል ነው (የሐዋ. 6:5)። እነዚህ ሰዎች በመልካም የተመሰከረላቸው፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉና ጥበበኞች ስለሆኑ በሐዋርያት የተሾሙ ናቸው (የሐዋ. 6:3)። በሳውል (በኋላ ጳውሎስ) የተቀሰቀሰው ስደት እነ ፊልጶስ የተሾሙበትን በየቀኑ ምግብን የማከፋፈልን አገልግሎት እንዳያከናውኑ ስላደረጋቸውና ከእነ ፊልጶስም ጋር አብሮ አገልጋይ የነበረውን እስጢፋኖስ እንዲገደል ምክንያት ስለሆነ ደቀ መዛሙርቱ በየሥፍራው ተበተኑ (የሐዋ. 8:1)። ፊልጶስም ወንጌላዊ ወደተባለበት ወደ ሰማርያ ሄደ። የእርሱ የወንጌል ስብከትና በፈውስና አጋንንትን በማውጣት የታጀበው አገልግሎቱ በሰማርያ ከተማ ብዙዎች ጠንቋዩን ሲሞንን ከሚከተሉበት ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዲሉ አደረጋቸው። በዚህ አዲስ በሆነው መነቃቃት ምክንያት በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስንና ዮሐንስን አዲሶቹ አማኞች የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንዲቀበሉ

እንዲጸልዩላቸው ወደ ሰማርያ ላኩአቸው (8:15)። የፊልጶስ አገልግሎት ጠንቋዩን ሲሞንን ሰውጦ የአገልግሎቱ ተባባሪ እስከ ማድረግና ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ (8:26-40) አሳምኖ እስከ ማጥመቅ ድረስ ጸጋ የተሞላበት ነበር። ይህም ማለት ፊልጶስ ወንጌልን ለም፦ራቅ አፍሪካ ለመናገር ቀዳሚው ሰው ነበር ማለት ነው። ይህም ፊልጶስ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት መታዘዙንና ስልቱን በውል ባይረዳውም በግል ምስክርነት ዘዴ ወንጌልን እንደሰበከ ያሳየናል። ምናልባትም ሉቃስ ይህንን ታሪክ የጻፈው ከወንጌላዊው ፊልጶስ አንደበት ሰምቶ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ (ሐዋ.21:8)።

ፊልጶስ አይሁዳዊ ያልሆኑ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣት የመጀመሪያው ሰው ነበር። ከዚያ በፊት ሰማርያውያን ከአይሁድ ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት አልነበራቸውምና (ዮሐ. 4:9)። የአይሁድን ማዕቀብ የጣሰና ወንጌል ለሰው ዘር ሁሉ እንዲደርስ ያደረገ የመጀመሪያ ሰው ሐዋሪያት ሳይሆኑ ፊልጶስ ራሱ ነበር። ለፊልጶስ ቀዳሚ አገልግሎቱ ወንጌላዊነት ሳይሆን ምግብን በተገቢው መንገድ ለሰዎች እንዲደርስ በማድረግ የዲቁና አገልግሎቱን መፈጸም ነበር። ነገር ግን በአገልግሎቱ ምክንያት ወንጌላዊ ተባለ።

በጥንት ዘመን ስም በከንቱ አይሰጥም። ሰዎች አካሄዱን፣ሥራውን፣ ባሕርውን፣ ቀዳሚ የሚያደርገውን ነገርና ሩጫውን አይተው ስም ይሰጣሉ። ለፊልጶስም



ወንጌላዊ የሚለው ስም የተሰጠው መንፈስ ቅዱስ በእርሱ በኩል ከሠራው ሥራና ከተግባሩ በመነሳት ነው። ፊልጶስ በጥበብ የተሞላ፣ እምነትና ጸጋ ያለው ትልቅ ሰው ቢሆንም ቀለል ያለ ኃላፊነት ሲሰጠውም ለመቀበል ታማኝ ሰው ነበር። ይህም የሚያሳየን እግዚአብሔር ታማኝና ጠንክረው የሚሠሩትን ሰዎች እንደሚጠራ ነው። እግዚአብሔር ለቤቱ ሥራ ሰነፍ ሰዎችን አይጠራቸውም።

- ሙሴ በቁጥቋጦ መካከል ስለሚነደው እሳት ለማየት ሲመጣ በጎችን ይጠብቅ ነበር (ዘጸ.3:1-6)
- ኤሊያስ ኤልሳዕን ሲጠራው ኤልሳዕ በ12 ጥማድ በሬዎች ያርስ ነበር (1ነገ. 19:19-21)
- ነህሚያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንዲጠግን ሲጠራ የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ ነበር (ነህ. 1:1-11)
- ጴጥሮስ ሰዎችን አጥማጅ እንዲሆን ሲጠራ ዓሣ አጥማጅ ነበር (ማቴ. 4:18-19)
- ማቴዎስ በተጠራ ጊዜ የሮማውያንን ቀረጥ የሚሰበስብ ነበር (ማቴ. 9:9)

ፊልጶስ በሦስት መንገድ የወንጌላዊነትን ሥራ እንደሠራ ሉቃስ ይነግረናል።

*ሀ) ታማኝ የጅማ ወንጌል ሰብሳቢ ሰባኪ ነበር።*

በኢየሩሳሌም ስደት በተነሳ ጊዜ ሐዋሪያት በኢየሩሳሌም የስደቱን ሁኔታ ሲከታተሉ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ተበታትነው ነበር። በዚህ ጊዜ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ሄዶ በከተማው የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራችና

የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ሰበከ (8:12)። በከተማውም ትልቅ ደስታ ሆነ። ስዲቁና አገልግሎት እንደ ተመረጠና እንደ ተሾመ ሰው መበለቶችን እንዲንከባከቡአቸው ማስተማር ነበረበት። ነገር ግን ወንጌልን በአሕዛብ ከተማ በግልጽ በመስበክ ታማኝነቱን አሳይቷል።

*ለ) በግል የወንጌል ምስክርነት ውጤታማ ነበር።*

ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ወደ ምድረ በዳ እንዲሄድ አዘዘው። ወዲያውም ታዘዘና ሄዶ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አገኘው። በሠረገላው አጠገብ እንዲቀመጥ ባዘዘው ጊዜ አልተቃወመም። እኔ በከተማ የጅማ ወንጌል ሰባኪ ነኝ፤ ለአንድ ሰው ስመስበክ ወደ ምድረ በዳ አልሄድም አላለም። ያንን ዕድል በመጠቀም ወንጌልን ሰብኮ በአፍሪካ የመጀመሪያውን አማኝ አገኘ። ስለዚህም የፊልጶስ አገልግሎት ስማርያውያንና አፍሪካውያንን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ ምክንያት የሆነ ቀዳሚ የወንጌል አገልግሎት ነበር።

*ሐ) የተዋጣለት የጉዞ ወንጌል ሰባኪ ነበር።*

ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ወደ ክርስቶስ ካመጣው በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወደ አዛጦን ወሰደው። ወደዚያም እየሄደ እስከ ቂሣሪያ ድረስ ወንጌልን ይሰብክ ነበር። ፊልጶስ በከተማ አደባባይ፤ በምድረ በዳ፤ በግልና በጉዞ ላይም ሁሉ ወንጌልን የሰበከ ሰባኪ ነበር።



**ሰ. የወንጌላዊ ስጦታ (ኤፌ. 4:11)**

አንድ ጊዜ አንድ ሰው በአንድ የባሕር ዳርቻ በሆነች ከተማ «እዚህ ውሃ ውስጥ ብዙ ዓሣዎች አሉን፤ ስለዚህም ጀልባዎችን ልከን ዓሣ ማጥመድ አለብን» ብሎ ተነሣ። በዚህ አሳብ ምክንያት የዓሣ አጥማጆች ማኅበር ተቋቋመ። ብዙ ሰዎችም ዓሣ ለማጥመድ ፍላጎቱ አደረባቸው። ብዙ ሥልጠናዎችም ተሰጡ። ብዙ ማስታወቂያዎችም እየተነገሩ ሰዎች እንዲሳተፉ ተበረታቱ። ፍላጎቱ ላላቸው ሰዎችም በዓሣ ማጥመድ ተግባር ውጤታማ ስልት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ እውደ ጥናቶችና ውይይቶች ተደረጉ። የሚገርመው ግን ከዚህ ሁሉ ጥረትና ብዙ የገንዘብ ወጭ በኋላ አንድም ሰው ሄዶ ዓሣ የሚያጠምድ አልተገኘም።

በውድ ዋጋ የተገዙ የዓሣ ማጥመጃ መረቦች ተጣጥፈው ተቀመጡ። የተሻሉ የተባሉ ጀልባዎች በባሕሩ ዳርቻ ተሰብስበው ቀሩ። ይሁን እንጂ አንድም ዓሣ ሲጠመድ አልተቻለም። ከብዙ ዓመታት በኋላ አንድ ወጣት ያለ ገንዘብና ያለ ምንም ዕውቀት ድንገት ሳያስበው ወደ ባሕሩ በሄደበት መረቡን ሲጥለው ሁለት ትላልቅ ዓሣዎችን ይዞ ወጣ። ወደ ከተማ ሲመለስ ዜናው በአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ሁሉ ጉድ እየተባለ ተነገረ። ብዙዎች ቃለ መጠይቅ አደረጉት። ብዙ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ፎቶ ለመነሳት ተሽቀዳደሙ። ሹራቦች የእርሱን ስኬት ለማስተዋወቅ ፎቶግራፎቹ ተሰጠፈባቸው። መጽሐፍ እንዲጽፍም ተጠየቀ። በከተማው ከአራት ግብዣ በኋላ ዋነኛ ተጋባዥ ተናጋሪ ሆነ። በዓሣ ማጥመድ ሙያ በዩኒቨርሲቲ ተጋባዥ መምህርም ሆነ። ከእነዚያ ሁለት ዓሣዎች በቀር ግን ዳግመኛ ዓሣ አላጠመደም።

መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ስጦታን የሚሰጠው እንዲያገለግሉት ነው:: እንደ ዓሣ አጥማጁ ወጣት በአንድ ሙከራ ወይም ድንገት በተገኘው ውጤት አንድን ሰው ስጦታ አለው ማለት አይቻልም::

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 12:6-8፤ 1ቆሮ. 12:4-11ና 28-30፤ኤፌ. 4:7-12 ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መመሪያ ሰጥቷል:: ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል የወንጌላዊነት ስጦታ አንዱ መሆኑን በኤፌሶን በተጠቀሰው ጥቅስ እናያለን:: "እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋሪያት፤ ሌሎቹም ነቢያት፤ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፤ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ" ይላል:: ስሙ እንደሚያመለክተው ወንጌላዊያን የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ለመሥራት የተመረጡ ናቸው:: ቃሉ ለፊልጶስ በሐዋ. 21:8 የተጠቀሰው ከተልዕኮ አንጻር ነው:: የምሥራቹን ቃል መመስከር የሁሉም አማኞች ኃላፊነት ቢሆንም የወንጌላዊነት ስጦታ የሚሰጠው ለተወሰኑ መንፈስ ቅዱስ ጸጋውን ለሚሰጣቸው ሰዎች ነው:: ለአገልግሎታቸውም ኃይልን የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ በማመን መፈጸም አለባቸው::

**ሐ. የወንጌላዊነት ሥራ (2ጢሞ. 4:5)**

በዚህ ክፍል ጢሞቴዎስ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ እንዲሠራ ተመክሯል:: "አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ



አድርግ፤ መከራን ተቀበል፤ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፤ አገልግሎትህን ፈጽም"::

ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ስለ ወንጌል ሊሠዋ በቀረበ ጊዜ ለጢሞቴዎስ ሁለት መልእክቶችን ጽፏል:: ምንም እንኳ አገልግሎቱ እየተገባደደና እርሱም የሚሠዋበት ጊዜ እየተቃረበ የነበረ ቢሆንም የወንጌል ሥራ ግን መቀጠል እንዳለበት ሐዋርያው ያውቃል:: ስለዚህም የአገልግሎት በትሩን በእምነት ልጁ ለሆነው ለጢሞቴዎስ ማስተላለፍ ነበረበት:: በጻፋቸው ሁለት መልእክቶችም የመጨረሻና በጣም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሰጥቷል:: ከእነዚህ አንዱ «የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ» የሚለው ነበር:: ጳውሎስ ከብዙ ጊዜ በፊት የጢሞቴዎስን የጸጋ ስጦታ ለይቶ ነበር:: ስለዚህም በዚህ በተሰጠው ጸጋ እንዲያገለግል ያበረታታዋል::

ጢሞቴዎስ እንደ ፊልጶስ በተፈጥሮ ጸጋ የወንጌል ሰባኪነትን አገልግሎት ተቀብሎ የሚሰብክ ሰው አልነበረም:: ጥርጣሬና ፍርሃት እንደ ነበረበት ከጳውሎስ መልእክቶች መረዳት እንችላለን:: የወንጌል ሰባኪነት ጸጋ አለው፤ ነገር ግን መለቀቅ ነበረበት:: ችግሮችንና መከራን ምክንያት አድርጎ በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ ይችል ነበር:: ለዚህ ነው ሐዋሪያው "ማንም ታናሽነትህን አይናቀው" (4:12) ብሎ ያደፋፈረው:: በጊዜው ከእርሱ ጋር ከሚያገለግሉ ሽማግሌዎች በዕድሜም አነስተኛ ስለ ነበር በቀላሉ ሰዎች

ሊንቁት ይችሉ ነበርና። በወቅቱ ጢሞቴዎስ የነበረበትን ሁኔታ ከመልእክቱ ማየት ይቻላል።

*ጤንነቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበረም።*
ጳውሎስ "ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ" (1ጢሞ. 5:23) ያለው ቃል ጢሞቴዎስ የጤንነት ችግር እንዳለበት ያሳያል። ይሁን እንጂ በሽታው ከወንጌል አገልግሎት እንዳላገደውና ጳውሎስም እንዳበረታታው እንመለከታለን።

*ፈሪና ቶሎ የሚቆጣ ባሕርይ ነበረው።*
ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን « ጢሞቴዎስም የመጣ እንደሆነ በእናንተ ዘንድ ያለ ፍርሃት እንዲኖር ተጠንቀቁ» (1ቆሮ. 16:10) ያለው ይህን ባሕርይ ያሳያል።

*በትውልዱ የተለያየ ዝሪያ ያለው ሰው ነበር።*
የጢሞቴዎስ እናት አይሁዳዊት ስትሆን አባቱ ደግሞ ግሪካዊ ነው። ይህ የተቀላቀለ ዝሪያነት ግን የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ከመሥራት አላገደውም። እግዚአብሔር በዘመናት የተናቁ ሰዎችን ጠርቶ ለዓላማው ይጠቀማቸዋልና።

ጢሞቴዎስ ከላይ የተጠቀሱ ደካማ ጎኖች እያሉበት የወንጌል ሰባኪነት አደራ ተሰጥቶታል። ሐዋሪያው ከችግሮቹ ባሻገር በጢሞቴዎስ ውስጥ ያለውን ታማኝ ልብና ወንጌልን ለማስራጨት የሚገባ ሰው መሆኑን አይቶት ነበርና።



## 3. የወንጌላዊ መለያዎች

ሉዊስ ፓላኦ የተባለ በአሜሪካን አገር ከዶ/ር ቢሊ ግራሃም ቀጥሎ ታዋቂ ወንጌላዊ የታላላቅ ወንጌላዊያን ባሕርያት የተባሉትን እንደሚከተለው ገልጾታል።
እኔ ያየሁት አንድ ትልቅ ነገር ታላላቅ የሚባሉ ወንጌላዊያን ሁሉ በአገልግሎታቸው ስኬታማ የሆኑባቸውን 10 ባሕርያት ሁሉም ይጋራሉ። መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የእያንዳንዱን አማኝ ልብና ሕይወት ለመቅረጽ እነዚህ ባሕርያት እጅግ ጠቃሚ ናቸው። እነዚህ ባሕርያት ቅንዓት (ለወንጌል አገልግሎት)፤ ክርስቶስን ብቻ መስበክ፤ ቅድስና፤ ራዕይ፤ ድፍረት፤ መገለጽ፤ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸው ትስስር፤ ፍቅር፤ ጸሎትና ታማኝነት ናቸው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለወንጌል አገልግሎት የተሰጡ ሰዎችን ስንፈልግ እንዴት እናገኛቸዋለን? ለዚህ ታላቅ አገልግሎት ሰዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ፍንጮች ምንድናቸው? የሚከተሉት አምስት መመዘኛዎች እንደ መርሖ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

**ሀ. ወንጌላዊ የወንጌላዊነት ስጦታ ያለው ነው።**
የእግዚብሔር መንፈስ አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ የተለያየ ስጦታ ይሰጣቸዋል። ከላይ በኤፌ. 4:11 እንደተመለከትነው ከስጦታዎች አንዱ ወንጌላዊነት ነው። አንድ አማኝ ወንጌላዊ ለመሆን የወንጌላዊነት ስጦታ ሊኖረው ይገባል። ለአንድ አገልጋይ ስጦታውን ለማወቅ

ሁለት ወሳኝ ነገሮች ያስፈልጋሉ:: እነዚህም የውስጥ መነሳሳትና የውጭ ምስክርነት ናቸው:: የውስጥ መነሳሳት ስንል አንድ አማኝ በውስጡ ሁል ጊዜ ቢያገለግል ደስ የሚለው፣ ካላገለገለ ደግሞ እረፍት የማይሰጠው ነገር ካለ ያ ስጦታው ነው ማለት ነው:: ከሌላ ሰው ጋር ሲነጋገርም ሁል ጊዜ አጀንዳው ይህ ጉዳይ እንዲሆን ይፈልጋል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ይህ አገልግሎት እንዲያድግ የዘወትር ፍላጎቱ ነው::

በአንድ ወቅት የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሦስቱን አንጋፋ ወንጌላዊያን አባባ ማሔን፣ አባባ ኤካሶንና አባባ ኦምቦሌን ከዕድሜያቸው አንጻር ማረፍ እንዳለባቸው በማመን በቀጣይነት በጸሎት እንዲያገለግሉ የጸሎት ክፍል ተሰጥቶአቸው እያረፉ እንዲያገለግሉ ያደርጉአቸዋል:: አባባ ኤካሶ ከሌሎች ይልቅ ደፋር ስለነበሩ ለሦስት ሳምንታት የቦንጋን ቤተ ክርስቲያናት እጎበኛለሁ ብለው ከሦስት ወራት በላይ ወንጌልን እያገለገሉ ይቆያሉ:: አባባ ኦምቦሌ ትሁት ስለሆኑ እንደታዘዙት እየጸለዩ ይቆያሉ:: አባባ ማሔ የወንጌልን ሥራ ትቶ በጸሎት ብቻ መወሰኑን እንደ አባባ ኦምቦሌ ባይቀበሉትም እንደ አባባ ኤካሶ ደፍረው መሄድም አልሆነላቸውም:: ስለዚህም አንድ ቀን ጠረጴዛ (የወላይታ ቃለ ሕይወት ጽ/ቤት ግቢ) ባለው ትልቅ ሜዳ መሐል ቆመው ብቻቸውን ሲተክዙ አገኟቸው:: ቀርቤ ምን ሆኑ? ስላቸው «እኔኮ ዛሬም እንደ ካሌብ ጉልበታም ነኝ፣ መኪናቸውንም አልፈልግም፣ የትራንስፖርት ገንዘባቸውንም



አልፈልግም፣ በእግሬ ሄጄ ማገልገል እችል ነበር» አሉኝ:: ልብ እንበል! በእግሬ እሄዳለሁ የሚሉት ወደ ሐመር ሲሆን ይህም ሥፍራ ከወላይታ ወደ 350 ኪ.ሜ. አካባቢ ይርቃል:: ይህ ነገር ለመሪዎች ሲነገራቸው ተፈቀደላቸውና ለሦስት ወር በዚያ ጠረፍ አገልግለው ሲመለሱ በበረሃ ቆይተው ሳይሆን ቤት ውስጥ በጥንቃቄ የተቀለበ ነበር የመሰሉት:: ይህን ያደረገው በውስጣቸው ያለው ትልቅ የወንጌላዊነት ስጦታ ነበር::

ሁለተኛው የሰዎች ምስክርነት ነው:: ጸጋ የሚገለጥ ነገር ነው:: ጌታ ኢየሱስ «በፍሬአቸው ታውቁአቸዋላችሁ» እንዳለው በፍሬ የሚታይ ነገር ነው:: በ1ሳሙ. 3:20 «እስራኤል ሁሉ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር ነቢይ ይሆን ዘንድ የታመነ እንደ ሆነ አወቀ» የሚለው አሳብ የሳሙኤል አገልግሎትና የነቢይነት ስጦታ ለሚያገለግላቸው ሰዎች በግልጽ ይታወቅ እንደ ነበር ያሳያል:: አንዳንድ አገልጋዮች ስለ ስጦታ ሲጠየቁ «ጌታ ተናገረኝ» ይላሉ:: ጌታ ይናገራል፣ ይህ የሚያከራክር ነገር አይደለም:: ነገር ግን ይህ ጌታ ሲናገር ለሚያገለግሉአቸው ሰዎች ካልታየ ስጦታው ነው ለማለት አይቻልም:: አንዳንዶቹም ጌታ ተናግሮአቸው ሳይሆን የፈለጉትን አሳብ ለመፈጸም እንዳይከለከሉ የሚጠቀሙት የተለመደ አባባል ሆኗል:: አንድ አማኝ በርግጥ ስጦታው እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ነገሮች በእርግጠኝነት መታየት አለባቸው:: አንድ ሰው የወንጌላዊነት ስጦታ አለው

ስንል በእነዚህ ሁለት መንገዶች ተፈትኖ ያለፈ ነው ማለት ነው።

ለ. ወንጌላዊ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት አለው።
አንድ ሰው ወንጌላዊ ከሆነ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ያልዳኑትን መስክሮ ለማምጣት የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሊኖረው ይገባል። ማቴ. 22:29 «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ» ይላል። በወንጌል የሚያገለግል አገልጋይ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ከሌለው የሚናገረው የራሱን አሳብ ወይም በቤተ ክርስቲያን የሰማውን ስብከት ነው። ይህ ደግሞ ትክክለኛ መልእክት ሊሆን አይችልም። አንድ ወንጌላዊ ስለ ወንጌል ምስክርነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን፤ ስለ እግዚአብሔር አብ፤ ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ፤ ስለ ሰው፤ ስለ ኃጢአት፤ ስለ ዳግም ምጽአትና ስለ መጨረሻው ፍርድ ጠንቅቆ ማወቅ አለበት።

ሐ. ወንጌላዊ ተግቶ የሚፀልይ ነው።
ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች «ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ፤ በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምስጢር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ፤ ልናገር እንደሚገባኝ ያህል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ» (ቆላ. 4:2-5) ብሎአቸዋል። በእነዚህ ጥቅሶች ሦስት አሳቦችን እናገኛለን። የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን



ምዕመናን በጸሎት የተጉ መሆን አለባቸው። ለራሳቸው በጸሎት ሳይተጉ ለሌላው ሊጸልዩ አይችሉምና።

ሁለተኛው ለእነ ጳውሎስ አገልግሎት እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ እንዲከፍት መጸለይ ነው። እግዚአብሔር በር ካልከፈተ ወንጌልን መመስከር አይቻልም። አንዳንድ ጊዜ እኛ የምናስበውና እግዚአብሔር የሚፈልገው የተለያየ ይሆናል። እኛ የተከፈተ በር ነው ብለን የምናስበው የተዘጋና እኛ የተዘጋ ነው ብለን የምናስበው የተከፈተ ሊሆን ይችላል። ያንን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በኢያሱ ም. 2 ኢያሱ የላካቸው ሰላዮች ወደ ጋለሞታይቱ ረዓብ ቤት የመግባት ታሪክ ነው። ይህች በሰው የተነቀፈችና የተገለለች ሴት፤ በከተማው ካሉት ሰዎች ይልቅ እነዚህን ሰላዮች ተቀብላ የእግዚአብሔር አሳብ የሚፈጸምባት መሣሪያ ትሆናለች ብሎ ማንም አይገምትም። እግዚአብሔር ግን ሰላዮችን ወደዚህች ሴት መርቶ ፈቃዱን ገለጠ። ሐዋ. 16:6-10 ስንመለከት እነ ጳውሎስ በእስያ ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ከለከላቸው። በቢታንያም እንዲሁ። ቀጥሎ አንድ ሰው በመቄዶኒያ «ተሻገርና እርዳን» የሚለውን በራዕይ አይቶ ወደዚያ ሄዱ። ስለዚህም የቃሉ ደጅ እንዲከፈትና የተከፈተውን በር እንዲያሳይ መጸለይ እንደሚያስፈልግ ከነዚህ ክፍሎች እንማራለን።

ሦስተኛው እነ ጳውሎስ በድፍረት እንዲናገሩ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው መጸለይ ነው። የእግዚአብሔር ሥራ

የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው:: «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» (ዘካ. 4:6):: የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል የሚመጣው ደግሞ በጸሎት ነው::

አንድ ወንጌላዊ ስለ ራሱና ስለ ሌሎች ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ካልቻለ ስለ እግዚአብሔር ከሌሎች ጋር መነጋገር አይችልም:: አንድ ሰው «ብዙ የሚጸልይ ሰው ትልቅ ኃይል አለው፤ ጥቂት የሚጸልይ ሰው ትንሽ ኃይል አለው፤ ምንም የማይጸልይ ሰው ምንም ኃይል የለውም» ብሏል:: ለውጤታማ የወንጌል አገልግሎት ወንጌላዊው ተግቶ የሚጸልይ መሆን አለበት:: የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት በጸሎት ይተጉ እንደነበር በተደጋጋሚ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ተጽፏል (1:14፤2:5፤42፤4:24):: ስለዚህም አንዱ የወንጌላዊ መለያ በጸሎት የሚተጋ መሆኑ ነው::

መ. ወንጌላዊ ለሚጠፉ ነፍሳት ሸክም አለው::
የወንጌላዊነት አገልግሎት ፕሮግራሞችን ማከናወን አይደለም፤ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ዘርቶ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በኩል እንዲታረቁ ማድረግ ነው እንጂ:: ለዚህ ደግሞ ወንጌላዊው መጀመሪያ ለሚጠፉት ሰዎች ሸክም እንዲኖረው ያስፈልጋል:: ማቴ. 9:36 «ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ አረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው» ይላል:: በዚህ ቦታ «ባየ ጊዜ» የሚለው ቃል ሰዎችን በተፈጥሮ ዓይን ሳይሆን በርኅራኄ እግዚአብሔር እንደሚያያቸው ማየትን



ያመለክታል:: ወንጌላዊው በተፈጥሮ ዓይን የሚያይ ከሆነ ሊያዝንላቸውም፤ ሸክም ሊኖረውም አይችልም:: በውስጥ መንፈሳዊ ዓይኑ ካየ ግን ችግራቸውንና ጭንቀታቸውን መንፈስ ቅዱስ ስለሚያሳየው ያዝንላቸዋል:: ወንጌላዊ ይህ ጸጋ ሊኖረው ይገባል::

ሠ. ወንጌላዊ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ የሚያገለግል ነው::
ወንጌላዊ ሁል ጊዜ ሳይደክምና ሳይታክት እንዲያገለግል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ማገልገል ወሳኝ ነው:: በፍርሃቱ ጌታ ኢየሱስን አላውቀውም ብሎ ሦስት ጊዜ የካደው ጴጥሮስ እንኳን የካህናት አለቆችና የመቅደስ አዛዦች ባሰሩአቸው ጊዜ ከዮሐንስ ጋር ሆኖ ወንጌልን በግልጥ የተናገረው በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ በኋላ ነው:: ሰዎችን በጣም የገረማቸው ደግሞ እነዚህ ሰዎች መጻሕፍትን የማያውቁና ያልተማሩ መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ድፍረት መስጠት ብቻ ሳይሆን አላዋቂዎችንም ጥበበኛ ያደርጋቸዋል::

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌ. 5:18 «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ» ያለው አሳቡን በደንብ ይገልጸዋል:: በወይን ጠጅ የሰከረ ሰው አነጋገሩን፤ አካሄዱን፤ አስተሳሰቡንና አመለካከቱን ሁሉ የሚቆጣጠረው የወይን ጠጅ ይሆናል:: ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላም እንደዚሁ ነው:: አነጋገሩን፤ አካሄዱን፤

እስተሳሰቡንና አመለካከቱን ሁሉ የሚቆጣጠረው መንፈስ ቅዱስ ነው።

እዚህጋ አንድ ልጠቀስ የሚገባ ነገር በልሳን የመናገር ጉዳይ ነው። በልሳን መናገር አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው። ይሁን እንጂ ስው መንፈስ ቅዱስ ሳይስጠውም ከሥጋ የሆነ ልሳን ሲናገር ይችላል። ስው በልሳን እየተናገረም ያልተስወጠ ሕይወት ሊኖረው ይችላል። በመንፈስ ቅዱስ በትክክል የተሞላ ስው በልሳን መናገር ይችላል። ይህ ግን በተስወጠ ሕይወትና በገላ. 5:22 በተጠቀሱት የመንፈስ ፍሬዎች መታየት አለበት።

### 4. የወንጌላዊው መልእክት

የወንጌል ስርጭት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክት ከሌለው የወንጌል ስርጭት ሊባል አይችልም። ወንጌላዊያን ለሚናገሩት መልእክት እርግጠኞች ካልሆኑ ወንጌልን ለመስበክ የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ ከንቱ ከመሆኑም በላይ የሚስሟቸውንም ግራ ያጋባሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ያውጅ ነበር (ማቴ. 3:1፤ 4:17፤ ሐዋ. 1:3)። የመልእክቱም ይዘት ስዎች የእግዚአብሔር መንግሥት ስለቀረበች ንስሐ እንዲገቡ የተደረገ ጥሪ ነበር።



ሐዋሪያትም የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ሰብከው ነበር (ሐዋ. 8:12፤ 19:8፤ 20:25፤ 28:23–31) ስእነርሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ሥራ የወንጌል ስብከት ዋነኛ መልእክታቸው ነበር።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስዎች እያደጉ ሲመጡ እርስ በርስ በመጣላትና በመለያየት ሥጋዊያን መሆን ሲጀምሩ ሐዋሪያው ጳውሎስ የሰበከላቸውን ወንጌል እንዲያስታውሱ ይመክራቸዋል። የመለያየታቸው አንዱ ምክንያት በጸጋ ስጦታ ጉዳይ ነበር። ሐዋሪያው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የተለያየ የጸጋ ስጦታ እንደ ሰጠ (1ቆሮ. 12-14) ከተናገረ በኋላ ስለ ሰበከላቸው ወንጌል እንዲህ ሲል ይነግራቸዋል።

«ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ . . . መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤. . . እንግዲህስ እኔ ቢሆን እነርሱም ቢሆኑ እንዲሁ እንሰብካለን፤ እንዲሁም አመናችሁ» 1ቆሮ. 15:1-11

ይህን ክፍል ስንመለከት ሐዋሪያው የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት (ቁ.3)፤ ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የኃጢአት ይቅርታና ደኅንነት እንደተዘጋጀ (ስለ ኃጢአታችን ቁ.3)፤ ስዚህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ እንደሆነ፤ ይህ የሞተው ጌታ ደግሞ እንደ ተነሣና ለዚህም ትንሣኤውን

በዓይናቸው ያዩት ሐዋሪያት ምስክር እንደ ሆኑ (5-8) ያስታውሳቸዋል፡፡

የወንጌል መልእክት መሠረቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ሥራ ነው፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ ሲጽፍ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና (ዮሐ. 3:16-17) ብሏል፡፡ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣበት ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ የወንጌል መልእክትም ይኸው ነው፡፡

ሉዊስ ፓላው የዮሐንስ ወንጌልንና የ1ኛ ቆሮንቶስ 15ን ክፍሎች አንድ ላይ በማቀናጀት እንዲህ ብሏል፡፡

የወንጌል ስብከት ይህንን መልእክት (ዮሐ. 3:16-17ና 1ቆሮ. 15:3-4) ማስተላለፍ ነው፡፡ አንተ ወንጌላዊ ከሆንክ በአንድ ለአንድ ቢሆን፣ በቤት ለቤት ቢሆን፣ በቤት ባለች ቤተ ክርስቲያን ቢሆን፣ በጅማ ስብከተ ወንጌል ቢሆን አንተ የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ወንጌል ሰባኪ ነህ፡፡ ወንጌላዊ ማስትም ይኸው ነው፡፡ በተጓዳኝ ሌሎች ሥራዎችን ትሠራ ይሆናል፡፡ አንተን ወንጌላዊ የሚያሰኝህ ግን የወንጌሉን ምሥራች ስትሰብክ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወትና (ሰው ሆኖ መወለዱን፣ መከራ መቀበሉን፣ መሰቀሉን፣ መሞቱንና መነሣቱን) ሥራውን (ትምህርቱን፣ ስብከቱን፣ ፈውሱን) ስትሰብክና ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ



ኢየሱስ በማመን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ ስትጋብዛቸው ነው፡፡

የወንጌል ምሥራች ምንን ያካትታል?

**ሀ. የእግዚአብሔር ኃይል ምሥራች**

ሐዋሪያው ጳውሎስ ሮሜ 1:16 ላይ «በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና» ሲል ወንጌል ኃይል እንደሆነ ይናገራል፡፡ ሰዎች ሁሉ ሲሰሙትና ሲቀበሉት የሚገባ መልእክት ይህ የእግዚአብሔር ኃይል የሆነው የወንጌል እውነት ነው፡፡

**ለ. የእግዚአብሔር ፍቅር ምሥራች**

«እግዚአብሔር ፍቅር ነው» 1ዮሐ. 4:16፡፡ ይህ ፍቅር ደግሞ በሁኔታዎች የማይወሰን ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ይህንን እውነት አያውቁም፡፡ ለዚህ ነው አንዳንድ ሰዎች ወንጌል ሲመሰክርላቸው «እኔን ጌታ እንዴት ይወደኛል?» ብለው ዓለማዊ ሕይወታቸውን በማሰብ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ለማመን የሚቸገሩት፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጠው በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ በመውደዱ ነው (ዮሐ. 3:16)፡፡ ጌታ ኢየሱስ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» (ዮሐ. 15:13) ብሏል፡፡ ሐዋሪያው

ዮሐንስ በመልእክቱ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማረውን በተደጋጋሚ ጽፎታል፡፡ በ1ዮሐ. 4:9-10

«በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡ ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም» ብሏል፡፡

በማቴ. 5:45 ላይም «እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና» ሲል የእግዚአብሔር ፍቅር ለፍጥረት ሁሉ በሁኔታዎች ሳይወሰን እንደተገለጠ እንመለከታለን፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር አንዲያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለኃጢአተኛ ዓለም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት አሳልፎ በመስጠትና ለኃጢአተኞችና ለጻድቃን ያለ ልዩነት ፀሐይንና ዝናብን በመስጠት የተገለጠ ቢሆንም ላላመኑት ግን ተሰውሮባቸዋል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች «የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙ ት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ፤ የማያስተውለው ልባቸው ጨለመ» ይላል (ሮሜ 1:20-21)፡፡ ስለዚህም ይህ



የእግዚአብሔር ፍቅር ሰዎች ሁሉ ሲሰሙትና ሊያውቁት የሚገባ የወንጌል መልእክት ነው፡፡

### ሐ. የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ምሥራች

ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አሳልፎ ሰጠ፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ «አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል» (ዕብ. 9:26) ይላል፡፡ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» (1ቆሮ. 5:7) ብሏል፡፡ 1ዮሐ. 3:16 «እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና፤ በዚህ ፍቅርን አውቀናል» ይላል፡፡ በ2:2 ላይም «እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፤ ስለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ስለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ» ይላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ እንዲሰጥ ያደረገው በሁኔታዎች የማይወሰነው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ ይህ ዓለም ሁሉ እንዲያውቀው የሚገባ መልእክት ነው፡፡

### መ. የእግዚአብሔር ሕያውነት ምሥራች

በ1ተሰ.1 ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ከጣዖታት ተመልሰው ወደ ሕያው እግዚአብሔር እንዴት ዘወር እንዳሉ ያሳስባቸዋል፡፡ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ እርሱ ብቻውን ሕያው አምላክ ነው፡፡ የአቴና ሰዎች ብዙ አማልክትን ያመልኩ ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም እውነተኛ አምላክ አልነበሩም፡፡ ስለዚህም ጳውሎስ «ለማይታወቅ አምላክ»

የሚለውን ጽሑፋቸውን መነሻ በማድረግ ስለ ሕያው አምላክ አስተምሮአቸዋል (ሐዋ. 17:22-23)፡፡ ስለዚህም ሰው ሁሉ ይህንን ብቻውን ሕያው የሆነውን አምላክ እንዲያመልክ ማወጅ ትልቁ የወንጌል መልእክት ነው፡፡

## ሠ. እግዚአብሔር የቅርባችን የመሆኑን ምሥራች

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን የሩቅ አምላክ አድርገው ያዩታል፡፡ እርሱ እኛን በማይለወጠው ፍቅሩ የወደደንና ሕያው የሆነ የቅርብ አምላክ ነው፡፡ በዮሐ. 14 ጌታ ኢየሱስ «አባት» የሚለውን ቃል 20 ጊዜ ያህል ጠቅሶታል፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን የአባትነት ባሕሪይ ለመግለጽ ነው፡፡ በሮሜ 8:15 እንደምናነበው አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበልን፡፡ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና» ብሏቸዋል (ዮሐ. 15:14-15)፡፡ ወዳጅነት ቅርበት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ የቅርባችን ነው፡፡ በጸሎታችንና በቃሉ እናናግረዋለን፤ እርሱም ይሰማናል፤ ይመልስልናል፤ ያናግረናልም፡፡ ይህ ግን ለማያምኑት ሰዎች ያልተገለጠ ሚስጢር ነው፡፡ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ሊያውቁትና ሊነገራቸው የሚገባ መልእክት ነው፡፡



## ረ. የተረጋገጠልንን የዘላለም ሕይወት ምሥራች

የምሥራቹ ቃል ለሰዎች የዘላለምን ሕይወት ተስፋ ይሰጣቸዋል፡፡ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን ወደ ዓለም በሚልክበት ጊዜ ለሚያምኑት የዘላለምን ሕይወት ሊሰጣቸው ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ምሥራች አለ ማለት በሌላ በኩል የዘላለም ሞት ዜናም አለ ማለት ነው፡፡ እኛ በጌታ ኢየሱስ በምናምንበት ጊዜ ከዘላለም ሞት አምልጠን የዘላለምን ሕይወት አግኝተናል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው የሚወስነው ምርጫ ነው፡፡ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፡፡ እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው? ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?» (ሮሜ 10:13-15) ይላል፡፡ ያላመኑ ሰዎች ለሚያምኑት እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የዘላለምን ሕይወት ምሥራችና ላላመኑት የተዘጋጀውን የዘላለም ሞት መስማት አለባቸው፡፡ ይህ ወንጌልን የሚመሰክሩ ሁሉ ሊናገሩት የሚገባና ያላመኑት ደግሞ ሊሰሙት የሚገባ መልእክት ነው፡፡

በአንድ መዝገበ ቃላት የወንጌል መልእክት ይዘት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

የወንጌል ስርጭት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን ካለበት ይዘቱ መንፈሳዊ መሆን አለበት፡፡ ይህም የኃጢአትን ባሕርይና

የኃጢአተኛን ሰው ዋጋ (ሮሜ 3)፣ የእግዚአብሔርን ፍቅርና የጠፉ ሰዎች በዚህ ፍቅር ከእርሱ ጋር እንዲታረቁ እንደሚፈልግ (ዮሐ. 3:16፣ 2:ቆሮ. 5:17-20)፣በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ኢየሱስ ክርስቶስ የዕቅዱ ማዕከል እንደሆነ ማሰትም እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር እንደሚያስታርቅ፣ መጽሐፍ እንደሚል ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን መሞቱንና ከሞት መነሳቱን (1ቆሮ. 15፣ 2ቆሮ. 5፣ ሮሜ. 10) ማካተት አሰበት። የወንጌል መልእክት የኃጢአት ይቅርታን ተስፋና በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ንስሐ የሚገቡትን አዲስ ፍጥረት የሚያደርገውን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ማወጅ አለበት። በአጭር ቃል የወንጌል መልእክት መሠረት የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ቃል ሲሆን እግዚአብሔር ሰርቶ የጨረሰውን ታሪክ ለሰዎች መግለጥ ነው።

የወንጌል መልእክት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለበት፤ አቀራረቡ ግን ከቦታ ቦታ ሊለያይ ይችላል። ብዙ ጊዜ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ተብሎ የሚታወቀው የወንጌል መልእክት አቀራረብ ቀላልና ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙት ስለሆነ እዚህጋ መጥቀሱ ተገቢ ነው።

**ሕግ አንድ፡ *እግዚአብሔር እኛን ይወደናል፤ ስለዚህም ለሕይወታችን ዘለዓለማዊ ዕቅድ አለው።***

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3:16)። የእግዚአብሔር ፍቅር በሁኔታዎች የሚወሰን አይደለም። መጽሐፍ እንደሚናገር እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ሳለን



አስቀድሞ እርሱ ወደደን። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እንደጻፈው ደካሞች ሆነን ሳለን ክርስቶስ ስለ ኃጢአተኞች ሞተ (5:6)። ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ በዚህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያስረዳል (ቁ. 8)። ጠላቶች ሆነን ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን (ቁ. 10)። ደካሞች፤ ኃጢአተኞች፤ ጠላቶች የሚሉት ቃላት ምን ያህል የእግዚአብሔር ፍቅር የማይገባን ሰዎች መሆናችንን ሲያሳዩ እግዚአብሔር እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን በመውደድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሞት አሳልፎ መስጠቱ ፍቅሩ በሁኔታዎች የማይወሰን መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ያልዳኑ ሰዎች መጀመሪያ ሊያውቁት የሚገባ መልእክት ይህ ነው።

**ሕግ ሁለት፡ *ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ለይቶታል።***

ሰው የተገለጠለትን የእግዚአብሔርን ፍቅር ካወቀ በኋላ ሊያውቀው የሚገባ እውነት ኃጢአተኛ መሆኑንና በኃጢአቱም ምክንያት ከፍቅር አምላክ መለየቱን ነው። ሮሜ 3:23 «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» ይላል። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲያደርግ ነበር። ነገር ግን ሰው በአመጸኛነቱ የራሱን መንገድ መከተልን መረጠ። ስለዚህ እግዚአብሔር በፍቅሩ ያዘጋጀው ትልቁ ዓላማ ተበላሸ። እግዚአብሔር ያዘጋጀው መንገድ እያለ የራሱን መንገድ በመከተሉም በራሱ ጥረት መልካም ሥራ በመሥራት፤

በጥሩ ስነ-ምግባር፤ በጥሩ ሃይማኖታዊ ስርዓትና በመሳሰሉት ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ይፈልጋል። እነዚህ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቂያ መንገዶች አይደሉም። ስለዚህም ሰው ኃጢአተኛነቱን አውቆ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በኩል መታረቅ አለበት።

ሕግ ሦስት: *ከእግዚአብሔር ለተለየው ሰው ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የእርቅ መንገድ አዘጋጅቷል።* ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅርና ለሕይወቱ እግዚአብሔር ያለውን ዕቅድ ማወቅ የሚችለው በክርስቶስ ኢየሱስ ሲያምን ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር ለተለየው ሰው እግዚአብሔር መፍትሔ አድርጎ የሰጠው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። በእርሱ በኩል ካልሆነ በቀር ደኅንነት በሌላ በማንም ወይም በምንም አይገኝም። ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 14:6 «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሏልና። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለተፈጠረው መለያየት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት የኃጢአትን ዕዳ በመክፈል ድልድይ ሆኗል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር «የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የሞት ዕዳ ራሱ በመሞት በመክፈሉ በእርሱ የሚያምኑት ሁሉ ይህ ዕዳ አይኖርባቸውም። እርሱ የሞተው በምትካችን ነውና። 1ጴጥ. 2:24 «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ» ይላል። ስለዚህ ሰው ሁሉ ወደ



እግዚአብሔር ሊቀርብ የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ይህ ነው። ይህም ልናውጀው የሚገባን መልእክት ነው።

ሕግ አራት: *እያንዳንዱ ሰው በግሉ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኙና ጌታው አድርጎ በመቀበል መዳን አለበት።*
«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐ. 1:12)። ይህ ጥቅስ የሚያሳየው ሰው በግሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የመዳን ኃላፊነት እንዳለበት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ዕቅድና ፍቅር፤ የሰውን ኃጢአተኝነትና ከእግዚአብሔር መለየት፤ እግዚአብሔርም በኃጢአቱ ምክንያት ለተለየው ለሰው ልጅ መፍትሔ አድርጎ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መስጠቱን ማወቁ በቂ አይደለም። ይህን ያወቀ ሰው በዚህ በተዘጋጀለት የመዳን መንገድ በማመን የዘላለምን ሕይወት ማግኘት አለበት።

እንግዲህ አንድ የወንጌል መልእክት ተናጋሪ በቀላሉ እነዚህን አራት ሕጎች ደረጃ በደረጃ በመናገር ጌታ ኢየሱስን አዳኝ አድርጎ ላልተቀበለ ሰው መመስከር ይችላል ማለት ነው።

### 5. የወንጌል ስርጭት ዘዴ

የምሥራቹ ወንጌል በብዙ መንገድ ሊነገር ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ የሆነ ወንጌልን የመመስከር ዘዴን አይነግረንም። አዲስ ኪዳን ጌታ ኢየሱስ፤ ሐዋሪያው ጳውሎስና ሌሎችም ሐዋሪያት የተጠቀሟቸው በርካታ

ዘዴዎች እንዳሉ ይነግረናል። ወንጌልን ማሰራጨት ወይም መመስከር ማለት ማወጅ፣ መናገር፣ ማስታወቅ ማለት ነው። በዬትኛው ዘዴ ተመሰከረ የሚለው ዋነኛ ነገር አይደለም። ዋናው ነገር ዬትኛውም ዘዴ ቢሆን ሰዎች በሚሰሙት መንገድና ለአካባቢው በሚመች ሁኔታ የወንጌልን እውነት መናገር ነው። ወንጌላውያን ሲጠቀሙ ከሚገባቸው ዘዴዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### 5.1. የግል (ወዳጅነት) ምስክርነት

ከአዲስ ኪዳን እንደምንመለከተው አንድ ለአንድ ወይም የወዳጅነት ምስክርነት በመጀመሪዎቹ የአዲስ ኪዳን አማኞች ዘንድ በጣም የተለመደ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት ምናልባትም ዘዴው ትኩረት የሚያደርገው ምዕመናንን ሁሉ ስለሆነ አለዚያም በወቅቱ የነበረው የሮማ አገዛዝ ያስከተለው የቤተ ክርስቲያን ስደት ሌሎች ዘዴዎችን ለመጠቀም እስቸጋሪ ስላደረገው ሊሆን ይችላል።

አንድ ለአንድ ምስክርነት በጌታ ኢየሱስ አገልግሎትና በሐዋሪያት ሥራ በግልጽ ታይቷል። ኒቆዲሞስ በምሽት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ስለ አዲስ ልደት ጌታ አስተምሮት ነበር (ዮሐ. 3)።

በሚቀጥለው ምዕራፍ (ዮሐ. 4) ሰማሪያዊት ሴት ውሃ ልትቀዳ በጠራራ ፀሐይ በመጣች ጊዜም በሚጠጣ ውኃ ጀምሮ ስለ ሕይወት ውኃ ተናገሯት ለራሷ ተለውጣ



በከተማዋ ላሉ ብዙ ሰዎች መለወጥ ምክንያት የሆነችው በአንድ ለአንድ ምስክርነት ዘዴ ነበር (ዮሐ. 4)።

በኢያሪኮ ጌታ ኢየሱስ ወደ ዘኬዎስ ቤት ሊገባ ወደደ (ሉቃ. 19:5)፣ ወደ ጴጥሮስ ቤት (ማቴ. 8:14)፣ ወደነማርታ ቤት (ሉቃ. 10:38)ና ወደ ለምጻሙ ስምዖን ቤት (ማር. 14:3) ገብቶ አገልግሏል።

ጌታ ኢየሱስ ከግለሰቦች ጋር ብዙ ጊዜ እንዳሳለፈ ወንጌላት ይነግሩናል። የሕግ አዋቂው የጠየቀውን ጥያቄ በመመለስ (ሉቃ. 10:25-37)፣ በእግሩ ሥር የተቀመጠችውን የማርታን እህት ማሪያምን በማስተማር (ሉቃ. 10:38-42) በግል አገልግሏቸዋል።

በመስቀል ላይ በተሰቀለበትና በሥቃይና በጭንቅ በነበረበት ጊዜም አብሮት የተሰቀለው ወንበዴ «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» ባለ ጊዜ «እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ሲለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለግል አገልግሎት ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ ማየት እንችላለን (ሉቃ. 23:42)።

ከትንሣዔው በኋላም እንዲሁ በግል መጀመሪያ መቃብር አጠገብ የምታለቅሰውን መግደላዊት ማሪያምን፣ ቀጥሎም የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፣ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም ያለውን ተጠራጣሪ ቶማስን፣ በኋላም ከሦስት ዓመት በፊት

የጣሰውን መረብ አንስቶ ዓሣ ሲያጠምድ የሄደውን ጴጥሮስን አነጋግሯቸዋል:: በምሳሌውም ስለ ጠፋው ልጅ ታሪክ በማስተማር በግል የሚደረግ ምስክርነት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን አሳይቷል::

የጌታውን ምሳሌ በመከተል እንድሪያስ ለወንድሙ ጴጥሮስ ስለ መሲሑ ተናግሯል (ዮሐ. 1:41-43):: ከዓመታት በኋላም ጴጥሮስ በመቅደስ ደጅ ተቀምጦ የሚለምነውንና ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የነበረውን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የፈውስ መልእክት በማምጣት አገልግሏል (ሐዋ. 3:5)::

ፊልጶስ በሰማርያ ከነበረው ስኬታማ አገልግሎት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ በመምራት ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ያገለገለው በግል ምስክርነት ነበር (ሐዋ. 8)::

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክት በመጨረሻው ምዕራፍም እንዲሁ በወንጌል አገልግሎቱ የተለወጡ ብዙ ግለሰቦችን ጠቅሶአቸዋል (ሮሜ. 16)::

### 5.1.1. የግል ምስክርነት አስፈላጊነት

የግል ምስክርነት ዘዴ ለምን እንዳስፈለገ የሚከተሉት አራት ምክንያቶች ያስረዱናል::



ሀ. የግል ምስክርነት ወንጌልን ያልሰሙ ሰዎችን ለመድረስ በር ይከፍታል::

ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች ይገናኛሉ፤በና በሚጠጣባቸው፤ በሥራ ቦታ፤ በትምህርት ቤትና በመሳሰሉት:: እርስ በርስ ለመነጋገርና ለመጫወትም የጋራ የሆኑ ብዙ ምክንያቶች አሉ:: ጌታ ኢየሱስ ሰማሪያዊቱን ሴት በመጀመሪያ የሚጠጣ ውኃ ከጠየቀ በኋላ ውይይቱን ወደ ሕይወት ውኃ እንደቀየረው ሁሉ ተራና የጋራ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት ወንጌልን መመስከር ይቻላል:: ሰዎች ስለ ወንጌል ለመስማት ፍላጎቱ ላይኖራቸው ይችላል፤ ሊቃወሙትም ይችላሉ፤ ነገር ግን ለወዳጅነታቸው ሲሉ ወንጌልን ይሰማሉ:: የሰሙት ቃል ዘር ሆኖ አንድ ቀን እንዲበቅል ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ታማኝ ነው::

ለ. የግል ምስክርነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለውን ሰው በቀላሉ ለመከታተል ያስችላል::

አንድ ሰው በግል በተደረገው ምስክርነት በጌታ ኢየሱስ በሚያምንበት ጊዜ ያ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እስኪበስል ድረስ መከታተል የመሰከረው ሰው ኃላፊነት ይሆናል:: የደኅንነት፤ የክትትልና መሠረታዊ የክርስትና ሕይወት ትምህርቶችን ቤተ ክርስቲያን ብታስተምርም ያ ሰው ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ መምጣቱን፤ በሕይወቱ ለውጥ መታየቱንና እያደገ መሆኑን መከታተል የመስካሪው ድርሻ ይሆናል:: ምክንያቱም መስካሪው እንደ መንፈሳዊ አባት ልጁ ራሱን እስኪችል ድረስ ሊተወው ስለማይችል ነው:: ስለዚህ

ሰው ከመጋቢውና ከመሪዎች ይልቅ አብሮ በመመገብ፤ አብሮ በመጸለይ፤ ቤተሰቡን በመጎብኘትና የቅርብ ወዳጁ በመሆን የበለጠ የሚያውቀው እርሱ ስለሆነ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሐዋሪያው ጳውሎስ ነው። ሐዋሪያው ጢሞቴዎስ መንፈሳዊ ልጁ ስለሆነ «እንግዲህ ልጄ ሆይ፤ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ» (1ጢሞ. 2፡1-2) እያለ ያበረታታዋል። ከዚህ ክፍል የምንመለከተው ሐዋሪያው መንፈሳዊ ልጁን ጢሞቴዎስን አስተምሮ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ማስተማር እንዲችል ማዘጋጀቱን ነው። ከዚህም የተነሳ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አድርጎ ሾሞታል። በግል የነበረው ቅርበት ጢሞቴዎስን በቀላሉ እንዲከታተልና እንዲያሳድገው ረድቶታል።

ሐ. ሰው በተፈጥሮ ወዳጁ ከሆነ ሰው ለመስማት ይፈልጋል።

ሰዎች በተፈጥሮ ከማያውቋቸውና እንግዳ ከሆኑ ሰዎች ይልቅ ከሚያውቋቸውና ወዳጅ ከሆኑ ሰዎች መስማት ይፈልጋሉ። ርዕስ ጉዳዩ የማይጥም ቢሆንም እንኳ ወዳጅነቱን ላለማጣት ሲሉ ወይም በይሉኝታ ይሰማሉ። በመጀመሪያ ሊቆጡ፤ ሊናደዱና ሊቀየሙ ይችሉ ይሆናል። የኋላ ኋላ ግን እየለመዱ ሲሄዱ የመወያየት ፍላጎቱ እየጨመረላቸው ይሄዳል። በዚህ ጊዜ ወንጌልን መስካሪው ሰው ስለ ወዳጁ መጸለይ፤ ወንጌልን እንደ አውዱ መናገርና



የግለሰቡን የመለወጥ ጉዳይ ለመንፈስ ቅዱስ መተው አለበት።

መ. የግል ምስክርነት ለወንጌል ዝግ በሆኑ ቦታዎች ወንጌልን ለመናገር በር ይከፍታል።

ወንጌልን ለመስበክ ፈጽሞ ዝግ በሆኑና ምንም ቤተ ክርስቲያን በሌለባቸው ቦታዎች ወንጌልን ለመስበክ ብቸኛው መንገድ የግል ምስክርነት ነው። ትላልቅ ኮንፈራንሶችን ማካሄድ በማይቻልባቸው፤ በአደባባይ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት መናገር ወንጀል በሚሆንባቸውና ምናልባትም እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ ዋጋ ሊያስከፍል በሚችልባቸው አስቸጋሪ ቦታዎች፤ በራሪ ወረቀቶችን መበተንና ሌሎች የወንጌል ስብከት መሣሪያዎችን መጠቀም በተከለከሉባቸው ቦታዎች ውጤታማው የወንጌል ስርጭት ዘዴ የግል ምስክርነት ነው።

### 5.1.2. የግል ምስክርነት መርሖዎች

የምስክርነት ዘዴ ሁሉ የራሱ መንገድና መርሖ አለው። የግል ምስክርነትም እንዲሁ ልንከተላቸው የሚገቡ መርሖዎች አሉት። ፕራካሽ የሉዲያን የተባለ እንድ ሕንዳዊ የወንጌል ስርጭት አስተማሪ ጠቃሚና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መርሖዎችን በመጽሐፉ ጽፏል። ከእነዚህ ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ለወዳጅነትህ ቅድሚያ ስጥ

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፤ በፍጹም ነፍስህም፤ በፍጹም ኃይልህም፤ በፍጹም አሳብህም ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ» ሉቃ. 10:27

የግል ምስክርነት ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ ከሁሉም የተሻለ የምስክርነት ዘዴ ነው:: ለዚህ ደግሞ ሰውን አስቀድሞ ወዳጅ ማድረግ ያስፈልጋል:: ሰው ለወዳጁ የሚከፍለው መስዋዕትነት አለ:: ከእነዚህ አንዱ የማይፈልገውን ነገር ለወዳጅነቱ ሲል ማድረግ ነው:: በወላይታ ባህል ሲተረት «ለጓደኛ ሲባል ጠፍ (ለም ያልሆነ) መሬት፤ ለአማች ሲባል ለነፍ ሚስት» ይባላል:: ጥሩ ወዳጅነት ከተመሠረተ የሚሰማ ጆሮ አገኘን ማለት ነው:: ስለዚህ አስቀድሞ ወዳጅነትን መፍጠር ለግል ምስክርነት በር ከፋች ቁልፍ ነው::

ለ. ወንዙን ከመሻገርህ በፊት ድልድይ አብጅ

«ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች:: ኢየሱስም:- ውኃ አጠጪኝ አላት» ዮሐ. 4:7

ለአንድ ሰው ስለ ወንጌል ለመናገር መጀመሪያ ሁለቱን የሚያገናኝ ነገር መኖር አለበት:: ኢየሱስ ክርስቶስና ሰማርያዊቷ ሴት ተገናኝተው እንዳይነጋገሩ የሚያደርጉ በቂ ምክንያቶች ነበሩ::



አንደኛው ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዳዊ ሲሆን እርሷ ግን ሰማርያዊት ነበረች «አይሁድ ከሰማርያውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና» ቁ. 9::

ሁለተኛው ኢየሱስ ወንድ ነው፤ እርሷ ደግሞ ሴት ነች

ሦስተኛው ኢየሱስ ጻድቅ ሲሆን እርሷ ግን ኃጢአተኛ ሴት ነበረች «ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ» ቁ. 29

ነገር ግን ውኃ ሁለቱንም የሚያገናኝ ድልድይ ነበር:: ሴቲቱ የመጣችው ውኃ ልትቀዳ ነው፤ ኢየሱስ ደግሞ ስለደከመው ውኃ መጠጣት አስፈልጎታል:: ከዚህ በላይ ግን ለዚህች በሰው ለተናቀችና ኃጢአተኛ ለሆነች ሴት የሕይወት ውኃ መስጠት ፈልጓል:: ስለዚህም ውኃ ሁለቱንም ያገናኛቸው ድልድይ ሆነ::

የሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 17 ስንመለከት ጳውሎስ በአቴና ብዙ ጣዖታት እንዳሉ አየ:: ለእነዚህ ጣዖታት ደግሞ ስም ተሰጥቶአቸው ነበር:: ከእነዚህም አንዱ «ለማይታወቅ አምላክ» የሚል ነበር:: ይህ ለጳውሎስና ለአቴና ሰዎች የጋራ የሆነ ድልድይ ነበር:: የአቴና ሰዎች ለተለያዩና እነርሱ አምላክ ለሚሉአቸው ጣዖታት ስም ሲሰጡ ምናልባት የማያውቁት ነገር ግን ሊያድን የሚችል ካለ ብለው ለዚህኛው ደግሞ ይህን ስም ሰጡት:: «የሚያድን» የሚለው ቃል ሰውን ከነፍስ ኃጢአት ነጻ የሚያወጣ ሳይሆን ለምሳሌ ከብቶችን፤ ውኃን፤ ቤትን፤ ልጆችን፤ እህልንና የመሳሰሉትን የሚጠብቅ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ግብፃውያንን በአሥር መቅሰፍቶች በሚመታበት ጊዜ ዋና

ዒላማው ለተመቱ ነገሮች የተሰየሙ አማልክትን መምታት ነበር። የአቴና ሰዎችም እነርሱንና ያላቸውን የሚጠብቁ ብዛት ያላቸውን አማልክት አቁመው ስም ሰጥተዋቸው ስለነበር ከእነዚህም በተጨማሪ ሌላ የማያውቁት ካለ ብለው «ለማይታወቅ አምላክ» ብለው ሰየሙት። ሐዋሪያው ጳውሎስ «ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ» ሲላቸው በደስታ ነበር ጆሮአቸውን የሰጡት። ስለዚህ ለወንጌል ምስክርነት የጋራ የሆነ ድልድይ ማበጀት እጅግ ጠቃሚ መርሆ ነው።

ሐ. የምታገኛቸውን ዕድሎች ተጠቀም

«እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ» ኤፌሶን 5፤15-16

ዘመኑን መዋጀት ማለት በጊዜው መሠራት ያለበትን ነገር ጊዜው ሳያመልጥ መሥራት፤ የተገኘውን ዕድልና አጋጣሚ መጠቀም ማለት ነው። የተገኘውን ዕድል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋሪያው ጳውሎስ በሚገባ ተጠቅመውታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃ ልትቀዳ ለመጣችው ሴት የሕይወትን ውኃ ለመስጠት ድካሙ፤ የባሕል ተጽዕኖ (እርሱ ወንድ እርሷ ደግሞ ሴት መሆናቸው)፤ የሃይማኖት ተጽዕኖ (እርሱ አይሁዳዊ እርሷ ደግሞ ሰማርያዊት ሆነው የራሳቸው የሚከተሏቸው የእምነት ሥርዓቶች መኖራቸው) አላገደውም።



ሐዋርያው ጳውሎስም ለአቴና ሰዎች ከላይ እንደተጠቀሰው በተገኘው ዕድል በመጠቀም እነርሱ የማያውቁትን ነገር ግን የሚያድናቸውን የኢየሱስን ወንጌል ነገራቸው። ለጢሞቴዎስም «ቃሉን ስበክ፤ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና» 2ጢሞ. 4:2 ብሎ ይመክረዋል።

የቱንም ያህል «ጊዜ የለኝም» የምንል ሰዎች ብንሆን ከጌታ ኢየሱስና ከጳውሎስ የበለጠ ሥራ የበዛብን ሰዎች አይደለንም። ወንጌልን የምንመሰክርበት ዕድል ሲያጋጥመን ዕድሉን ልንጠቀም ያስፈልጋል። ጌታ ኢየሱስ «ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች» ብሏል (ዮሐ. 9:4)።

ቻይናውያን «ጊዜ ፀጉሩ መላጣ፤ ጢሙ ደግሞ ረጅም እንደሆነ ሰው ነው። ጊዜው ሳያልፍ (ጢሙን መያዝ) መሥራት ያስፈልጋል፤ ያለበለዚያ ካለፈ በኋላ ማግኘት (መላጣውን መያዝ) አይቻልም» ይላሉ። ማን ያውቃል? አንዳንዶቹን በሞት ደጃፍ ላይ ሆነው ለመጨረሻ ጊዜ ከመሰናበታቸው በፊት እግዚአብሔር በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶን ይሆናል።

በአንድ አገር አንድ እናትና ልጅ በየቀኑ እየወጡ ወንጌልን የሚመሰክሩ ነበሩ። አንድ ቀን ግን ኃይለኛ ዝናብ ዘንቦ መውጣት ስለከለከላቸው እናት ቤት መቅረትን ስትመርጥ ልጅ ግን በፍጹም አልቀርም ብሎ ለምስክርነት

የሚጠቀሙበትን በራሪ ወረቀት ይዞ ይወጣል:: ለረጅም ለዓታት ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ላይ ደክሞት ወደ ቤት ሊመለስ ሲል አንድ በር እንዲያንኳኳ መንፈስ ቅዱስ ይገፋፋዋል:: አላመነታም፤ ሄዶ አንኳኳ፤ የሚከፍት የለም:: መልሶ አንኳኳ፤ መልስ የለም:: ደጋግሞ ሲያንኳኳ አንዲት ሴት በትንሹ ሊከፍቱት በዝናብ ልብሱ የራሰ አንድ ትንሽ ልጅ በር ላይ ቆሟል:: ምን ፈልገህ ነው ልጅ በዚህ ዝናብ የመጣኸው? ሲሉት ከያዛቸው በዝናብ ከራሱ በራሪ ወረቀቶች አንዷን አውጥቶ ለጥቶ ተሰናብቶአቸው ይሄዳል:: ሴትዮዋም እየተገረሙ ከተቀበሉ በኋላ በሩን ዘግተው ለማንበብ ደስተኛ ባይሆኑም ይህ ትንሽ ልጅ በዚህ ዝናብ የመምጣቱ ውለታ ከብዶአቸው አነበቡት:: ያልታሰበ ነገር ሆነ፤ ለብቻቸው ቁጭ ብለው አለቀሱ:: ለካስ ሴትዮዋ ኑሮ መሮአቸው ራሳቸውን ለማጥፋት እየተዘጋጁ ስለነበር ለልጁ እንኳን በሩን ለመክፈት ስላልፈለጉ ነበር የዘገዩት:: ይህ አንድ ትንሽ ልጅ በዝናብ የራሰችውን በራሪ ወረቀት መስጠቱ እኚህን ሴት ከነፍስና ከሥጋ ሞት ታደጋቸው:: ምናልባት ልንታደጋቸው ስንችል የተገኘውን ዕድል ባለመጠቀማችን በነፍስና በሥጋ የሞቱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ጌታ ምሕረትን ያድርግልን:: ከዚህ በኋላ ግን ልንጠቀም ያስፈልጋል::

በሕይወቴ በጣም የተደሰትኩበትና በጣም የሚቆጨኝ ሁለት አጋጣሚዎች አሉ:: አንዱ አንዲት እህት ቀድሞ በጌታ



የነበረች በኋላ ግን ከጌታ ቤት ወጥታ ጭልጥ ባለ ዓለማዊ ኑሮ የምትኖር፤ አጋንንትም ንብረቲን ሁሉ አውድሞ በነፍስም በሥጋም ሊገድላት ሲል የንስሐን መልእክት ነግሬያት ዛሬ በነፍስም በሥጋም ተባርካ የምትኖረውን እህት ሳስብ ሁል ጊዜ ደስ ይለኛል:: ሌላው ሁል ጊዜም የሚቆጨኝ አንዱ ወንድሜ ሃይማኖተኝነቱን ብቻ ይዞ እውነተኛ አዳኙን ሳያውቅ የሚኖር አንድ ጥሩ ዕድል አጋጥሞኝ ላለ እንደሚገባ ሳልመሰክርለት ከአንድ ወር በኋላ መሞቱ ነው (እርሱ የሚኖረው ጎንደር እኔ ደግሞ ወላይታ ስለነበር በቅርበት አንገናኝም:: ስንገናኝ ስለ መንፈሳዊ ነገር ማውራታችን ባይቀርም በመጨረሻው ጊዜ ግን ጥሩ ዕድል አመለጠኝ):: ስለዚህም ጌታ የሰጠንን ዕድልና ጊዜ መጠቀም ያስፈልጋል::

መ. ምስክርነትን ሊያሰናክሉ የሚችሉ እንቅፋቶችን አስወግድ «አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ እንዴት መጠጥ ትለምናለህ?» ዮሐ. 4:9:: ይህ ለጌታ ኢየሱስ ትልቅ እንቅፋት ሊሆን ይችል ነበር:: ነገር ግን እንቅፋቱ ጌታን አላገደውም:: አንዳንድ እንቅፋቶች ጥሰን ልናልፍ የሚገቡን ናቸው:: አንዳንዶቹ ደግሞ እኛ ራሳችን ልናስወግዳቸው የሚገቡን ናቸው::

አንዱ ጥሰን እንድናልፍ የሚገባን እንቅፋት የሰዎች ማንነት ነው:: ለምሳሌ ኃይማኖተኛነታቸው፤ የጾታ ልዩነት፤ የሰዎች ማዕረግና የሃብት ልዩነት ተጠቃሽ ምክንያት ናቸው::

እነዚህን መጣስ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንዶቹ ራሳችን የምንፈጥራቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ጌታን እንደተቀበሉ ከጓደኞቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያቋርጣሉ፤ አብሮ ሻይና ቡና መጠጣት ያቆማሉ፤ አነጋገራቸው ይቀየርና እንግዳ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጓደኞቻቸው ክርስትና ሰውን ከሰው የሚያርቅ፤ ጓደኝነትን የማይደግፍ መጥፎ ሃይማኖት እንደሆነ ያስባሉ፡፡ ስለዚህም ለመመስከር ትልቅ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህ ልናስወግደው የሚገባ ራሳችን የምንፈጥረው እንቅፋት ነው፡፡ በጾም ወቅት ማኪያቶ መጠጣት ራሱ በሌሎች ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ አለው፡፡ ስለዚህም ለምስክርነት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

ሠ. ተገዳደረው፤ ነገር ግን አታስቀይመው

*«ጳውሎስ ግን እንዲህ አለ፤- ክቡር ፊስጦስ ሆይ፤ የእውነትንና የአእምሮን ነገር እናገራለሁ እንጂ እብደትስ የለብኝም፡፡ በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉሥ ይህን ነገር ያውቃል፤ ከዚህ ነገር አንዳች እንዳይሰወርበት ተረድቼአለሁና» የሐዋ. 26:25*

ጳውሎስ ለንጉሡ በአንድ በኩል የሚገባውን ክብር ሰጥቷል፤ ነገር ግን የእውነትን ቃል የተናገረው ያለ ፍርሃትና ንጉሡ ሊቃወመው በማይችለው መንገድ ነበር፡፡ ለዚህ ነበር ንጉሡ «በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ?» ያለው፡፡ ሰዎች ባላቸው ማዕረግና ቦታ ተገቢው ክብር ሊሰጣቸው ይገባል፡፡



ከሁሉም በፊት ግን ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ ሊከበር ይገባል፡፡ ነገር ግን ወንጌልን በድፍረትና በጥበብ መናገር ደግሞ ነፍስን የማዳን ጉዳይ ስለሆነ ሰሚውን ሳናስቀይም እውነትን መናገር ያስፈልጋል፡፡

«ተገዳደረው» የሚለው ቃል እውነትን ከመናገር ያልፋል፡፡ መገዳደር ሰዎች ልክ አይደለም ብለው መቃወም እስከማይችሉ ድረስ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ማስረዳት ነው፡፡ ለምሳሌ ስለ ስግደት ከተናገርን በዘጸዐት 20 ስግደት የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ፤ በማቴ. 2:11 ሰብዓ ሰገል መጥተው ኢየሱስን ከእናቱ ከማርያም ጋር አይተው ለኢየሱስ እንደ ሰገዱለትና ስጦታም እንደ ሰጡት እንጂ ለማርያም እንዳልሰገዱላት ወይም ስሁለቱ እንዳልሰገዱ (ቃሉ ሰገዱለት፤ አቀረቡለት ይላል)፤ በራዕይ 19:9-10ና 22:8-9 መልአኩ ዮሐንስን «እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ» ያለውን መጥቀስ እንችላለን፡፡

ሌላው ጥሩ ምሳሌ አንዳንዶች ኢሳ. 60:14 «የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ» የሚለውን ቃል ለማርያም እንደሆነ አድርገው ይጠቅሳሉ፡፡ ነገር ግን ቁ.10ን በመጥቀስ ማርያም በእግዚአብሔር ቁጣ ተቀስፋ ነበር ወይ? ቢባል መልስ አይኖራቸውም፡፡

አንድ ጊዜ አንዲት እስራኤላዊት አስተማሪ «ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን አንድ ናቸው። አሮጌ ኪዳን ብሎ ነገር የለም» አለች። በዚህ እምነትዋም በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያለውን «የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ ኪዳን» የሚለውን ገጽ ከመጽሐፍ ቅዱስዋ ውስጥ ቀድዳ አውጥታው ነበር። ከተማሪዎችዋ አንዱ አንድ ጥያቄ ጠየቃት። ዕብ. 7:18-19 «ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፤ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትዕዛዝ ተሽራለች፤ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል» የሚለውን ቃል እንዴት ትመለከቻለሽ? ሲላት የመለሰችው ነገር ቢኖር «ይህ ትልቅ ተግዳሮት ነው» ነበር። የስነ-መለኮት ትምህርት አስተማሪ ሆና ይህን ክፍል አላነበበችውም ይሁን? ወይስ ለራሷ በሚመች መንገድ ተረጎመችው? ሳታውቅ ብታስተምርም፤ ለራሷ በሚመች መንገድ ብትተረጉምም አደጋ ነው። ዋናው ነገር ከላይ እንደተጠቀሰው ሰዎችን ሳናስቀይም እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ልንገዳደራቸው (በምንለው ነገር መልስ ልናሳጣቸው) ያስፈልጋል።

### ረ. የሕይወት ምስክርነትህን ተናገር

*«ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች፤ ለሰዎችም፡- ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች። ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር» ዮሐ. 4:28-30*



ሰማርያዊት ሴት ወደ ከተማ ስትመለስ አራቱን መንፈሳዊ ሕጎች አልተናገረችም። ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገላት ለጓደኞቿና ለጎረቤቶቿ ስትናገር ግን ብዙዎች አመኑ። ይህም የሕይወት ምስክርነት የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ ምን ያህል ኃይል እንዳለው ያሳያል። ሐዋሪያው ጳውሎስም በተደጋጋሚ ቀድሞ የነበረውን ሕይወትና ጌታ እንዴት እንደ ለወጠው በተደጋጋሚ ይናገር ነበር (ሐዋ. 22:2-21፤26:9-23)።

ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ በሚመጡበት ጊዜ ውስብስብ ከሆነ ኑሮና ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለውጦአቸው ነው። ዘራፊ፤ ሌባ፤ ሴትኛ አዳሪ፤ ለብዙ ዓመታት የጫት፤ የሲጋራና የመጠጥ ሱሰኛ ከነበሩበት ጌታ ኢየሱስ ወደ ውስጣቸው ሲገባ በሥጋም በነፍስም የተለወጡት ብዙዎች ናቸው። ብዙዎችም በዚህ ሕይወት የሚኖሩት ለመውጣት እየፈለጉ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ባለማወቅ ወይም ጌታ እንደዚህ ዓይነት ሰው አንደማይወድ በማሰብ የጉስቁልና ኑሮ ይኖራሉ። ለእነዚህ ሰዎች የግል የሕይወት ምስክርነትን መናገር በጣም አስፈላጊ ነው።

### ሰ. ሥጋዊ ፍላጎቱን መረዳት ያስፈልጋል

በአንድ ወቅት ኢየሱስን የተከተሉ ሰዎች ተርበው ስለነበር ኢየሱስ አየና አዘነላቸው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ቦታው ምድረ በዳ ስለሆነ አሰናብት አሉት። ደቀ መዛሙርቱ አሰናብት ሲሉት ጌታ ግን አዘነላቸው (ማቴ.14:13-21)። ይህ

ትልቅ ልዩነት ነው። መፍትሔ የተገኘው ግን ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ በያዘው በአንድ ብላቴና እጅ ነበር።

የሰውን ፍላጎት ሁሉ ማሟላት አንችልም። መንግሥትም እንኳ የሚችለው ነገር አይደለም። አንድ ጊዜ ለአንድ ጓደኛዬ ስለ ተለያዩ ሰዎች ችግር ስነግረው «አባክህን አል አሙድንም እንኳ የሰውን ሁሉ ችግር ሊፈታው አይችልም» ብሎኝ ነበር። እውነት ነው፤ የሰውን ችግር ሁሉ ማቃለልና መፍትሔ ልንሰጥ አንችልም። ነገር ግን መጀመሪያ የኢየሱስ ልብ ሊኖረን ይገባል፤ ለሰዎች ልናዝንላቸውና ፍቅር ልናሳያቸው ይገባል። እንዳንዶቹ ተርበው ይሆናል፤ ከቻልን ዳቦና ሻይ ብንገዛላቸው፤ ልብስ እጥተው ከሆነ ባይኖረን ከክርስቲያን ወገኖች ወስደን ብናለብሳቸው ልባቸው ለወንጌል ይከፍታሉ።

ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ማየት ይፈልጋሉ፤ ማየት የሚችሉት ግን በእኛ ነው። ጌታ ኢየሱስ «ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት» (ማቴ. 25:40) ብሏቸዋል። እኛ የውስጣቸውን ፍላጎት የሚረዳ ልብ ሲኖረንና ስናዳምጣቸው በእኛ ውስጥ ኢየሱስን ያያሉ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ለመናገር መጀመሪያ ልባቸውን ልናገኝ ይገባል።

ፕራካሽ የግል ምስክርነት አሥርቱ ትዕዛዛት የሚላቸው የሚከተሉት ናቸው።



1. ዓሣዎች ወዳሉበት ሂድ፤ እነርሱ ወደ መረቡ አይዋኙም።
2. እንተነትህን ይዘህ በወዳጅነት ቅረብ፤ አታስመስል።
3. ጥያቄዎችን ጠይቅ፤ አለበለዚያ ስለ ሰውዬው የምታስበው በግምት ይሆናል።
4. በጥንቃቄ አድምጠው፤ ካልሆነ የምትናገረው ከንቱ ወሬ ይሆናል።
5. ክአጠገቡ ሁን፤ እትራቀው።
6. የግልህን ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶችን መልስ።
7. ለምትጠየቀው ጥያቄ መልሱን የማታውቅ ከሆነ አላውቅም በል።
8. ውስብስብ የሆኑ ነገሮችን ለሌላ ጊዜ አስተላልፍ።
9. ትኩረትህ የምትመሰክርለትን ሰው ወደ ክርስቶስ ማምጣት ብቻ መሆን አለበት።
10. ልባቸውን አግኝ፤ እንደዚያ ከሆነ የደኅንነትን ግማሽ መንገድ መጥተዋል ማለት ነው።

### 5.2. የጅማ ስብከተ ወንጌል

የጅማ ስብከት የምሥራቹን ቃል ለብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ ማወጅ ነው። ይህ በተለምዶው ክንፈራንስ ወይም በዘመንኛው ክሩሴድ የሚባለው ነው። በአዲስ ኪዳን ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ስብከት በተለያዩ ቦታዎች አድርገዋል።

የጌታ ኢየሱስ የተራራ ላይ ስብከቱ ለብዙ ሕዝብ ነበር። «ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ፤ በተቀመጠም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ አፉንም ከፍቶ አስተማረ» ማቴ. 5:1

በሌላም ጊዜ እንዲሁ ለብዙ ሕዝብ በምሳሌ አስተማራቸው። «. . . ሕዝቡም ሁሉ በወደቡ ቆመው ነበር። በምሳሌም ነገራቸው . . . » ማቴ. 13:2-3

ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ በሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ሰብኮ ሦስት ሺህ ሰዎች አመኑ (ሐዋ. 2)። በሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ በሽባው መፈወስ ምክንያት ለብዙ ሺህ ሰዎች ሰብኮ ከአምስት ሺህ በላይ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ።

በጲስዲያ አንጾኪያ ጳውሎስና ባርናባስ ከጥቂቶች በስተቀር የከተማው ሰው ሁሉ በተሰበሰበበት ወንጌልን ሰብከዋል (ሐዋ. 13:44)።

በ18ኛው ክፍለ ዘመን እነ ጆን ዊስሊ፤ ጆርጅ ዋይት ፊልድና ዲ ኤል ሙዲ የታወቁ የጅማ ሰባኪዎች ነበሩ። በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከተነሱት ሁሉ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው ዶ/ር ቢሊ ግራሃም ነው። ለዶ/ር ቢሊ ግራሃም ዮሐ. 3:16 ተወዳጅ የስብከት ጥቅሳቸው ሲሆን በዚህም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ጌታን የግል አዳኝ አድርገው ተቀብለዋል።



የጅማ ስብከት ብዙዎችን በአንድ ጊዜ በወንጌል ለመድረስ ቀላሉ መንገድ ቢሆንም የራሱ ደካማ ጎኖች አሉት። ዋነኛ የሆኑት ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የጅማ ስብከት በአብዛኛው ወንጌልን ላልሰሙት ከማሰማት ይልቅ የክርስቲያኖች መነቃቃት ነው።

ብዙ የጅማ ስብከቶች በብዙ የሙዚቃ መሣሪያ በመታጀብ፤ በፈውስ አገልግሎቶች፤ በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ሥጋዊ ችግር ላለባቸው በመጸለይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። እነዚህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊና በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ነገር ግን ወደ ሲዖል እየሄዱ ላሉ ሰዎች ትኩረት የሚሰጥ አይደለም። ይህም ማለት

የተሰበከላቸውን እንሰብካለን

በወንጌል የተደረሱትን እንደርሳለን

የተጽናኑትን እናጽናናለን

እርዳታ ላገኙት እርዳታ እንሰጣቸዋለን

የተገለሉትን እናገላቸዋለን

በሌላም አባባል ዋናውን ግብ እንረሳለን ማለት ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ብዙ ሰዎች በዚህ አገልግሎት ደስተኛ አይደሉም፤ ምክንያቱም ፕሮግራሙን በተካፈሉ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ እያዩም ወይም ብዙዎች በጌታ አምነው ሲድኑ አይታይም። የአንድ ጊዜ ሞቅታ ብቻ ሆኖ ፍሬ አልባ ስለሆነ ነው።

ለ. በጌታ አምነው ከዳኑት ውስጥ የሚጸኑትና ደቀ መዝሙር የሚሆኑት በጣም ጥቂቶች ናቸው:

የወንጌል ስርጭት ግቡ ደቀ መዝሙርነት ነው:: ጌታ ኢየሱስ በታላቁ ተልዕኮ ያለውም «ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» (ማቴ. 28:19-20) ነው:: ያመኑት ሰዎች ደቀ መዛሙርት ካልሆኑ የወንጌል ስርጭት ግቡን አልመታም ማለት ነው:: በጅማ ስብከት በሺዎች የሚቆጠሩት ወንጌልን የሚሰሙት በአንዴ ስለሆነ አምነው የዳኑትን ተከታትሎ ደቀ መዛሙርት ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው::

ሐ. ለአንዳንድ ሰባኪዎች የግል ዝናና ጥቅም መፈለግ ፈተና ይሆንባቸዋል::

የጅማ ስብከት በሚደረግበት ወቅት መሪዎችና ሰባኪዎች ትልቅ ዝና ይኖራቸዋል:: አንዳንዶችም ዝናቸው ወደ ጥቅም ፍለጋ ስለሚወስዳቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል:: ስለዚህ የጅማ ስብከት በሚታሰብበት ጊዜ ከቀደሙት ልምምዶች በመነሳት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ መዘጋጀት ያስፈልጋል::

- ለስብከቱ ምላሽ በመስጠት ወደ ፊት የመጡት ወይም የተነሱት የማያምኑት ናቸው ወይስ አማኝ ሆነው ለሌላ ጸሎት የመጡ ናቸው?
- ጌታን የተቀበሉት በቤተ ክርስቲያን በሥርዓት ተይዘዋል?
- አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ተሰጥቶአቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አድገውና ተጠምቀው የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነዋል?
- ከጅማ ስብከት የተነሳ በቤተ ክርስቲያን የምዕመናን ቁጥር ጨምሯል?
- በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምን ለውጥ እያመጣ ነው? በአንድ ዓመት? በአምስት ዓመት?

እነዚህን ጥያቄዎች በትክክል መመለስ የሚቻል ከሆነ የጅማ ስብከት ውጤታማ ነው ማለት ነው:: አሰበሰዚያ ብዙ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና እውቀት እየባከነ ነው::

## 5.3. ሚዲያ በወንጌል ስርጭት

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰዎች በሩቅ ካሉት ጓደኞቻቸውና ዘመዶቻቸው ጋር በቀላሉ እንዲገናኙ፣ ሥራዎች በፍጥነትና በቅልጥፍና እንዲከናወኑ ዘመኑ ያመጣቸው ቴክኖሎጂዎች ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ነው:: በቤተ ክርስቲያን አምልኮ እንኳን ብናይ ድምፅ ማጉያዎችና የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ደግሞ መዝሙሮችን ከዘመናዊ ስሌዳዎች ላይ እያነበቡ ለመዘመር ኮምፒተርና ፕሮጀክተር ትልቅ ሥራ እየሠሩ ነው:: ለወንጌል ስርጭትም በዘመናችን ብዙ መሣሪያዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ:: ሚዲያ በቀላል ዋጋና በአጭር ጊዜ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን በወንጌል ለመድረስ ስለሚያስችል ብዙዎች ይህንን ዘዴ

እየተጠቀሙ ነው:: ከእነዚህ ዋነኞቹ በራሪ ጽሑፎች፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና የኢየሱስ ፊልም ናቸው::

ሀ. በራሪ ጽሑፎች:- በራሪ ጽሑፎች የምሥራቹን ቃል ለማስተላለፍ እጅግ ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው:: በዓለም ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች ተጽፈው እየተሰራጩ ያሉ ብዙ ጽሑፎች አሉ:: ምንም እንኳ ጽሑፎቹ ክተበተኑ በኋላ ውጤቱን መገምገሙ እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም ከየአቅጣጫው የሚሰሙ ምስክርነቶች በራሪ ጽሑፎች ለወንጌል ስርጭት በጣም አስፈላጊ መሣሪያዎች እንደሆኑ ያመላክታል:: አንድ ወንጌላዊ ያሰራጨው የወንጌል ስርጭት በራሪ ወረቀት የአንድን ሰው ሕይወት እንዴት እንደለወጠው ከዚህ በታች የተመለከተው ታሪክ ያሳየናል::

አንድ ልጅ በሕይወቱ ካለበት ምሬት የተነሳ ተናዶና ተስፋ ቆርጦ ራሱን ሊያጠፋ ከቤት ወጥቶ ይሄዳል:: በአንድ መርከብ ተሳፍሮ ጉዞ እንደ ጀመረ አንድ ወንጌላዊ በራሪ ጽሑፍ ሲያሰራጭ ያያል:: በጣም ተናዶና ተስፋ ቆርጦ ስለ ነበር ክወንጌላዊው እንደ ተቀበለ ቀዳዶ ከተቀመጠበት ወንበር ሥር ይጥላል:: ምሽት ላይ ሰዎች ሁሉ እንቅልፋቸውን ሲተኙ እርሱ ግን እረፍት አጣ:: ወደ ታች ዝቅ ብሎም በንዴት ቀዳዶ ከጣላቸው ወረቀቶች አንዱን ያነሳል:: በወረቀቱም እንዲህ የሚል ጽሑፍ ያነባል:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ.3:16):: ይህ ጥቅስ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋ እንዲያደርግ ያበረታታዋል፣ ወዲያውም በዚህ ጌታ ለማመን ይወስናል፣ ከዚህም የተነሳ የወንጌል መልዕክተኛና ለወንጌል ተልዕኮ ሌሎችን የሚያነሳሳ መሪ እንደሆነ ይነገርለታል::

የኤስ አይ ኤም ሚስዮናዊያን መጀመሪያ በኢትዮጵያ ሲያገለግሉ በወቅቱ ሕዝቡ በሚረዱበት ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ጽሑፍ አልነበረም:: ስለዚህም ሚር እህማን የተባለ ሚስዮናዊ በ1924 ዓ.ም. የማርቆስን ወንጌልና አንዳንድ የወንጌል ክፍሎችን እያገለገለ በነበረበት በጎፋ ቋንቋ ይተረጉማል:: ይህ ትርጉም በተለይም የማርቆስ ወንጌል «ጎፋ ማርቆስ» እየተባለ ቋንቋው በሚመሳሰልባቸው በወላይታ፣ በጋሞና በዳውሮ ሁሉ ለብዙ ዓመታት ለወንጌል ስርጭት እንደ መሣሪያ አገልግሏል::

የበራሪ ጽሑፎች ችግር ጽሑፉን ለመረዳት ሰው ቢያንስ ማንበብ የሚችል መሆን አለበት፣ አለበለዚያ ሌላ ሰው ሊያነብለት ይገባል:: የተጻፈው ደግሞ ጽሑፉን የተቀበለው ሰው በሚረዳው ቋንቋ ካልሆነ ማንበብ ብቻ ሳይሆን መተርጎምም አለበት ማለት ነው::

ለ. ቴሌቪዥን:- ቴሌቪዥን በጆሮ የሚሰማና በዓይን የሚታይ መልእክት ይዞ ስለሚቀርብ የሰውን ልብ ለመሳብ ትልቅ ኃይል አለው:: ቴሌቪዥን ለማየት ዕድሉ ያላቸው

ሰዎች ብዙ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ። በውጭ አገር ብዙ መንፈሳዊ ፕሮግራሞች በቴሌቪዥን ስለሚተላለፉ ሰዎች በቀላሉ መከታተል ይችላሉ። በአገራችን በሳተላይት ዲሽ፤ በዲቪዲና በመሳሰሉት ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ በቴሌቪዥን የሚተላለፍ ፕሮግራም የለም። በአሁን ጊዜ ቲቪ ጆሹዋ፤ ኤልሻዳይና ሌሎችም ፕሮግራሞች የታወቁ ሲሆኑ ብዙ ሰዎችም ይከታተሉአቸዋል።

ሦስቱ ዋነኛ የቴሌቪዥን ድክመቶች

1. መልእክቱ የሚደርሳቸው ቴሌቪዥን መግዛትና ማየት ዕድሉ ያላቸውን ብቻ ነው። አገራችንን እንደ ምሳሌ ብንወስድ ካለው ሕዝብ አብዛኛው ቴሌቪዥን የለውም፤ ብዙዎቹ አቅሙም የላቸውም፤ አቅሙ ቢኖር እንኳን የኤሌክትሪክ መብራት ያስፈልጋል። ስለዚህም የመግዛት አቅሙና የኤሌክትሪክ መብራት ላላቸው ብቻ የተወሰነ ነው ማለት ነው።
2. በቴሌቪዥን ወንጌልን የሰሙ ሰዎችን መከታተልና ደቀ መዝሙር ማድረግ አይቻልም፤ ምክንያቱም እነርሱ ካልመሰከሩ በስተቀር ስለማይታወቁ ነው።
3. አንዳንድ አገልጋዮች የቴሌቪዥን አገልግሎትን ወደ ግል ጥቅም እያዞሩት ነው። አገልግሎቱ ብዙ ወጭ የማስወጣቱን ያህል ብዙ ገቢና ከፍተኛ ዝናን የሚያስገኝም ነው። በሚያሳዝን መልኩ አንዳንዶቹ ወደ



ንግድነት እየቀየሩትም ነው። አንድ ጸሐፊ እንዲህ ብሎ ጽፏል።

የታወቁ ታላላቅ ሰባኪዎች፤ ዘማሪያን፤ ገንዘብ አሰባሳቢዎች፤ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶችና የድርጅት አስተባባሪዎች ክርስትናን ከቤተ ክርስቲያን ወደ ንግድ፤ ከታሪካዊ እምነትነት ወደ ታዋቂ ሃይማኖትነት እየቀየሩት ነው። በአሁን ጊዜ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ንግድና አገልግሎት የቅርብ ዘመዳሞች ሆነዋል።

ሐ. ሬዲዮ፦ ከቴሌቪዥን በተቃራኒው ሬዲዮ ለመግዛት ርካሽና ለማዳመጥም ቀላል በመሆኑ (በባትሪ ድንጋይ የሚሠራ ስለሆነ) ብዙ ሰዎችን የመድረስ አቅም አለው። በሬዲዮ ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችንና የወንጌል መልእክትን በቀላሉ ማስተላለፍ ይቻላል። ከሬዲዮ ጥቅሞች ዋነኞቹ

- መልእክቱ ብዙ ሰዎችን በቀላሉ መድረስ ይችላል።
- የሬዲዮ ፕሮግራሞች ከአንድ ማሰራጫ ወደ ሌላ ለማዘዋወር አያስቸግሩም።
- በወንጌል ለመድረስ የማይቻሉ ቦታዎችን ለመድረስ እጅግ ጠቃሚ ነው።
- ሬዲዮ ማንበብና መጻፍ የማይችሉትንና መስማት የተሳናቸውን ለመድረስ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው።
- ሬዲዮ ብዙ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅፋቶችን ጥሶ የመግባት ኃይል አለው።

እንደ በራሪ ጽሑፎችና ቴሌቪዥን የሬዲዮ መልእክትም ቢሆን ከሰሙት ሰዎች ምን ያህል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝ አድርገው እንደ ተቀበሉና ደቀ መዛሙርት እንደሆኑ ለመከታተል ስለማይቻል የራሱ ድክመት አለው::

መ. የኢየሱስ ፊልም፡- በአሁን ጊዜ በዓለም ላይ ወንጌልን ለማሰራጨት የኢየሱስ ፊልም ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል:: ፊልሙ የተዘጋጀው የሉቃስ ወንጌልን መሠረት በማድረግ ነው:: ካምፓስ ክሩሴድ የተባለው አገልግሎት መስራች በሆነው በቢል ብራይት እንደ ተጀመረ የሚታወቀው የኢየሱስ ፊልም ከ220 በሚበልጡ አገሮች የታየ ሲሆን ከ700 በላይ በሆኑ አገልግሎቶችና የቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች አማካይነት ከአንድ ቢሊዮን በላይ ሰዎች ተደርሰዋል:: በ1989 ዓ.ም. የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው 50 ሚሊዮን የሚሆኑት በዚህ ፊልም አማካይነት ጌታን አግኝተዋል:: ይሁን እንጂ ቁጥሩ ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም::

የኢየሱስ ፊልም ብዙዎች በቀላሉ ወደ ጌታ እንዲመለሱ የሚያደርግበት አራት ምክንያቶች አሉት:: የመጀመሪያው ፊልሙ የተሠራው በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት በነበሩ በሜስጴጦማዊያን ባሕል በድራማ መልክ በመሆኑ ለብዙዎች የሚያውቁትና የሚኖሩበት ኑሮ መምሰሉ ነው:: ሁለተኛው ፊልሙ ማንበብና መጻፍ የማይችሉትን መድረስ መቻሉ



ነው:: ሦስተኛው ብዙ ሰዎች በሕይወታቸው ፊልም የሚባል ነገር አይተው ካለማወቃቸውም ሌላ በራሳቸው ቋንቋ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ይማርካቸዋል:: አራተኛው ብዙ ምዕራባዊያን ባልሆኑ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች እርቀ አሳቢዎች ናቸው:: ፊልሙን ሲያዩ ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኝ አድርገው የሚቀበሉት አዳኝ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ፤ በክፉ መንፈስ፤ በበሽታና በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው ስለሚያምኑ ነው::

እንደ ሌሎቹ ሚዲያዎች የኢየሱስ ፊልምም በወንጌል ስርጭት የራሱ የሆነ ድክመት አለው:: ዋነኛው ጌታን የተቀበሉትን ሰዎች አውቆ ደቀ መዝሙር ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ፊልሙ ከታየ በኋላ ብዙዎች ጌታን ለመቀበል ወስነው ወደ መድረኩ ይመጣሉ፤ ከፕሮግራሙ በኋላ ግን የሚከታተላቸው አይኖርም:: ለብዙ ዓመታት በዚህ አገልግሎት ከቆየ በኋላ የዶክትሬት ዲግሪውን የሠራ አንድ ጓደኛዬ የመመረቂያ ወረቀቱን የጻፈው ይህን ችግር ምክንያት ባደረገ ጥናት ላይ ነበር:: ቢሆንም ሚሊዮኖችን ወደ ጌታ ያመጣ ትልቅ የወንጌል ስርጭት መሣሪያ መሆኑ ሊካድ የማይችል እውነት ነው::

ምሁራን በሚዲያ ወንጌልን በማሰራጨት ዘዴ ላይ የተለያየ አመለካከት አላቸው:: በአሜሪካ ከቢሊ ግራሃም ቀጥሎ ታዋቂ ለሆነው ለሉዊስ ፓላአ ሚዲያ ከሁሉ የተሻለ የወንጌል ማሰራጫ ዘዴ ሲሆን፤ በአፍሪካ 38 ዓመታትን

ሲኖር በኬኒያ ዴይ ስታር ዩኒቨርሲቲን መሥርቶ ወደ አሜሪካ ሄዶ እሱም ባለቤቱም 80 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ተመልሶ ኬኒያ ሰመጣው ለዶ/ር ዶናልድ ሰሚዝ ግን ሚዲያ ደካማ የወንጌል ስርጭት ዘዴ ነው::

ሰዎች ሁሉ የራሳቸውን አገልግሎት፣ ጽሑፍ፣ የወንጌል ስርጭትና የመሳሰሉትን ብቸኛና ከሁሉ የተሻለ አድርገው ያስባሉ፣ ያስተዋውቃሉም:: ይህ ግን ስሕተት ነው:: በሚዲያ ወንጌልን ማሰራጨት ከሁሉ የተሻለ ነው የሚሉት እነ ሉዊስ ፓላኦም ሆኑ ደካማ ዘዴ ነው የሚሉ እነ ዶ/ር ስሚዝ የራሳቸው ምክንያቶች አላቸው:: ይሁን እንጂ እነርሱ እንደሚሉት ከሁሉ የተሻለና ብቸኛ ዘዴም አይደለም፣ የመጨረሻ ደካማ ዘዴም አይደለም:: ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በሌሎች ዘዴዎች መድረስ የማንችላቸውን ወገኖች ለመድረስ እጅግ ጠቃሚ ዘዴ ነው:: የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖችም አሉት:: ስለዚህ እንደየኅብረተሰቡ፣ እንደየዓቅምና እንደየሁኔታው ዘዴዎችን ልንጠቀም ያስፈልጋል::

### 6. የኢየሱስ ክርስቶስ ስልት

የወንጌላት ጸሐፊዎች በአራቱ ወንጌላት ውስጥ 77 ጊዜ «ኢየሱስን መከተል» የሚለውን ቃል ጽፈውታል:: ኢየሱስ «ተከተሉኝ» በሚልበት ጊዜ የሚጠራቸው ደቀ መዛሙርቱ እርሱን እንዲመስሉ ነው:: ከእርሱ ጋር በሚቆዩበት ጊዜ



እርሱ እንደሚያስበው እንዲያስቡ፣ እርሱ እንደተናገረ እንዲናገሩ፣ እርሱ እንዳደረገ እንዲያደርጉ፣ እርሱ እንደኖረ እንዲኖሩ፣ እርሱ አባቱን እንዳከበረ እነርሱም እንዲያከብሩ፣ እርሱ ሌሎችን እንደተንከባከባቸው እነርሱም እንድንከባከቡ ነው:: ይህንንም ለማድረግ አራት ነገሮችን አድርጓል::

#### ሀ. ደቀ መዛሙርቱን ጠራቸው::

በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፣ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ፣ ደግሞም ሐዋሪያት ብሎ ሰየማቸው» ሉቃ. 6:14

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ሥራ ስልት የሚያተኩረው ምን ላይ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል:: የእርሱ ትኩረት ብዙ ሰዎችን አንድ ጊዜ የሚደርስበትን ፕሮግራም ማዘጋጀት ሳይሆን ብዙ ሰዎች የሚከተሉአቸውን ሰዎች ማዘጋጀቱ ላይ ነበር:: ጌታ ደቀ መዛሙርቱን መሰብሰብ የጀመረው አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ነበር:: ዓለምን ለእግዚአብሔር መንግሥት ለመጥራት ሰዎችን ማዘጋጀት የእርሱ ቀዳሚ ስልት ነበር:: የእርሱ ዓላማ እርሱ ወደ አባቱ ካረገ በኋላ ሞቱንና ትንሣኤውን የሚመሰክሩና አገልግሎቱን የሚቀጥሉ ሰዎችን ማዘጋጀት ነበር::

የመረጣቸውን ሰዎች ስንመለከት ማናቸውም በምኩራብ ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበራቸው አልነበሩም፣ በሌዋውያን የክህነት ውስጥ የነበሩም አይደሉም፣ለኑሮአቸው የሚያስፈልገውን ከሚያሟሉበት እውቀት ውጭ የተማሩ

ባለ ሙያዎችም አልነበሩም፤ ከሀብታም ቤተሰብ መሆናቸውም አልተጠቀሰም፤ ምናልባት ከምኩራብ የሚሰጠውን ትምህርት ካልተማሩ በስተቀር የሚቆጠርላቸው ዲግሪ ያላቸውም አልነበሩም። አብዛኛዎቹ በገሊላ አካባቢ ደሃ ኅብረተሰብ ባሉበት ቦታ የኖሩ ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እነዚህን ሰዎች ወንጌልን ለዓለም ለማድረስ ጠራቸው። ይህም የሚያሳየን ዛሬም ማንንም ለሥራው ሊጠቀም እንደሚችል ነው።

በኢየሱስ አገልግሎት ሁለተኛው ዓመት ላይ የተከታዮቹ ቁጥር በጣም እየጨመረ ሲሄድ አሥራ ሁለቱን ለይቶ መረጣቸውና ደቀ መዛሙርት አላቸው (ሉቃ. 6:13-17)። ይህ ማለት ግን ጌታ ብዙ ሰዎች መከተላቸውን አልወደደም ማለት አይደለም። ለዚህ መረጃ የሚሆነው ደግሞ በኋላ ሰባ ሰዎችን መሾሙ ሲሆን (ሉቃ. 10:1) ከእነርሱ ውስጥ ወንጌልን የጻፈው ማርቆስና የኢየሱስ ወንድም የሆነው ያዕቆብ መገኘታቸው ነው (1 ቆሮ. 15:7፤ ገላ. 2፤9,12)። ከአሥራ ሁለቱም ጴጥሮስ፤ ያዕቆብና ዮሐንስ ከሌሎቹ ይልቅ ወደ ጌታ ሲቀርቡ እንመለከታለን። የኢያዕሮስ ልጅ ታማ ጌታ ወደዚያ ሲሄድ (ማር. 5:37፤ ሉቃ. 8:31)፤ ወደ መገለጥ ተራራ ሲወጡና የእግዚአብሔር ክብር እዚያ ሲገለጥ (ማር. 9:2፤ ማቴ. 17:1፤ ሉቃ. 9:28)፤ ጌታ ሊያዝ በቀረበ ጊዜ ሲጸልይ (ማር. 14:33፤ ማቴ. 26:37) እነዚህ ሦስቱ ከእርሱ ጋር ነበሩ።



ጌታ አሥራ ሁለቱን ብቻ ወስዶ ያሰለጠነበትና ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ ያደረገበት ምክንያት

1. ሰውጤታማ ሥልጠና የተማሪዎቹ ቁጥር የተወሰነ መሆን ስላለበት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፈው ከእነዚህ ሰዎች ጋር ነው። በዮሐ. 6:66 ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እውነት ባስተማራቸው ጊዜ ብዙዎች ትተውት ሲሄዱ የእርሱ ትኩረት በእነዚህ ጥቂቶች ላይ ነበር። ዓለም በወንጌል እውነት እንዲድን ከተፈለገ እነዚህ እውነቱን በደንብ መረዳት ነበረባቸው። ጌታ የተከተሉትን ሁሉ አስተምሮአቸዋል፤ ሰብኮአቸዋል፤ በሽተኞችን ፈውሶአል፤ ሲራቡ መግቦአቸዋል፤ አጋንንት የያዛቸውን ነጻ አውጥቶአቸዋል፤ ልጆቻቸውን ባርኮአል። ይህም ማለት ሕዝብን ሁሉ አገልግሏል። ትልቁ ትኩረት ግን ጥቂቶቹን ማስታጠቅ ነበር።

2. ጥቂቶቹን አሠልጥኖ ብዙኃኑን እንዲመሩ ማድረግ የኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ስርጭት ስልት ነበር። ኢየሱስ ዓለም እንዲድን ይፈልጋል፤ ነገር ግን ዓለምን ወደ ወንጌል እውነት የሚመሩ ሰዎች መዘጋጀት ነበረባቸው። ሕዝብ የሚመራውና የሚጠብቀው ከሌለ ለስሕተት ትምህርት ወዲያው ይጋለጣል (ማር. 6:34፤ ማቴ. 9:36፤ 14:14). የሚጠቅም ወዳጅ ይሁን የሚጎዳ ጠላት በጥሩ የተስፋ ቃል ከመጣ ሕዝብ በቀላሉ ይከተላል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ጌታ ተአምራትን ሲሠራ አይተው ተደንቀው

ይከተሉ የነበሩ ብዙ ሰዎች ባለ ሥልጣኖቻቸውን ሲያዩ ወዲያው ደግሞ መተዋቸው ነው። ስለዚህም ሰዎች የወንጌልን እውነት ከተቀበሉ በኋላ የሚመራቸው፣ የሚጠብቃቸውና የሚያሳድጋቸው ከሌለ ስለሚበተኑ ጌታ የሚመራቸውን ሰዎች ማዘጋጀትና ብዙውን ጊዜ ከእነርሱ ጋር ማሳለፍ ነበረበት። ከትንሣኤው በኋላ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት የሚሰጠው ለእነርሱ ነውና።

3. ውጤታማ የወንጌል ሥራ የሚሠራው በሠለጠኑ ጥቂት ሰዎች ነው። ጌታ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ጊዜ ወስዶ አሠለጠናቸው፤ እነርሱም ወንጌልን ዓለምን አደረሱ። ጌታ የተመለከተው ዘላቂና ቀጣይ የሆነ ሥራ መሥራትን ነው። ይህ በዘመናችን የወንጌል ስርጭት አገልግሎታችን የተረሳና ልናስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

**ሀ. ደቀ መዛሙርቱን ከራሱ ጋር አቆያቸው።**

ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው . . . አሥራ ሁለት አደረገ (ማር. 3:14-15)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለማሠልጠን ከወደደባቸው መንገዶች አንዱ ከእነርሱ ጋር በመቆየት የሕይወት ምሳሌነትን ማሳየት ነበር። እውቀትን እንዲገበዩ ጌታ የመረጠው ስልት ሕግንና ሥርዓትን «አድርጉ፤ አታድርጉ፤ ልክ ነው፤ ልክ አይደለም፤» በማለት ሳይሆን እርሱ የሚያደርገውንና የማያደርገውን በማየት እንዲማሩና እንዲለማመዱ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ከመስበካቸውና ከማስተማራቸው በፊት ከእርሱ ጋር መቆየት ነበረባቸው።



የጌታ አገልግሎት በምድር ላይ እየተገባደደ በሄደበት በሦስተኛው ዓመት ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የበለጠ ጊዜ ይሰጥ ነበር። በአደባባይ ያስተማረውን ወደ ቤት ሲመጡ በግል ይጠይቁት ነበር፤ ምስጢርን ሁሉ ይገልጥላቸው ነበር። ከእነርሱ ጋር በልቷል፤ የተለያዩ ቦታዎችን ተጉዟል፤ ተወያይቷል፤ በምድረ በዳና በተራራ አብረው ጸልየዋል፤ አጋንንትን ሲያስወጣ፤ ሙታንን ሲያስነሣ፤ ከጸፎችና ከፈሪሳውያን በሚመጣው ጥያቄና ተቃውሞ ውስጥ ሁሉ አብረው ነበሩ። ጌታ ወደ አባቱ ሲያርግም «እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28:20) ብሎ ተለያቸው። ስለዚህም ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር በመቆየታቸው ሕይወታቸው በኢየሱስ ትምህርትና ሥራ ተቀረጸ።

**ሐ. ደቀ መዛሙርቱን አሠለጠናቸው።**

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራቸው ወደ ፊት ከትንሣኤው በኋላ ወደ አባቱ ሲሄድ ሞቱንና ትንሣኤውን ለዓለም ሁሉ የሚያደርሱና ሕዝብን የሚመሩ ሰዎች እንዲሆኑ አይቶ እንጂ እርሱ በምድር ላይ በሚቆይበት ጊዜ ከእርሱ ጋር የሚያሳልፉበትን ጊዜ ዓላማ አድርጎ አልነበረም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ጴጥሮስ አንዴ ከእግዚአሔር አብ ዘንድ መገለጥን አግኝቶ «ሥጋና ደም አልገለጠልህም፤ በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ» ተብሎ ከተወደሰ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ስለ ሞቱ ሲናገር «አይሆንብህም» ብሎ የዲያብሎስን መልእክት ሲያስተናግድ፤ ከዚያ አልፎም ዶሮ እስኪጮህ

ሦስት ጊዜ ሊክደው እያለ፤ ቶማስ ተጠራጣሪ፤ የዘብዴዎስ ልጆች ጌታ ስለ ሞቱ ሲናገር እነርሱ ግን የሥልጣን ጥያቄ ሲያቀርቡ የተቀሩትም በእነርሱ ላይ ሲቆጡ፤ ይሁዳ እንደተጻፈው ቃል አሳልፎ ሊሰጥ እንዳለው እያወቀ ለሦስት ዓመት አሠለጠናቸው። አሠለጣጠኑ እኛ ከምናስበው ፈጽሞ የተለየ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ከሕይወቱና ከአገልግሎቱ እንዲማሩ ያደረጋቸውን ስድስት መንገዶች እንመልከት።

*1. በሕይወቱ ምሳሌነትን በማሳየት አሰለጠናቸው።*

የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ምድራዊ አገልግሎቱን እንደ ጀመረ ብዙ ወንዶችና ሴቶች እንዲከተሉት ማርኮአቸዋል። እርሱ ጎልማሳ ሲሆን ጠንካራና ብሩህ አዕምሮ ያለው ስለሆነ በካህናትና በአለቆች ይፈራል፤ ነገር ግን በትናንሽ ሕፃናት ይወደዳል። ቤተ መቅደስን የሚያረክሱትን በጅራፍ የሚያባርር ቆጡ ሲሆን ለተራቡትና ለተጎዱት የሚያዝን፤ ለነአልዓዛር የሚያለቅስ ርኅሩኅ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ለመከተል ከወሰኑበት ጊዜ አንስቶ በየቀኑ ለአባቱ ፈቃድ የሚታዘዝና ታማኝ መሆኑን ያዩ ነበር።

ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ኢየሱስ የተለያዩ ሰዎችን እንዴት ይቀርብ እንደነበረ አብረው በመቆየታቸው ተምረዋል። ጌታ በየቀኑ ከተማሩና ካልተማሩ፤ ከባለ ሥልጣናትና ከተራ ሰዎች፤ ከሽማግሌዎችና ከወጣቶች ጋር እንዴት ይነጋገር እንደነበር አይተዋል። ለተራቡት፤ ለታመሙት፤ ለተቸገሩትና ለሞቱትም ጭምር ጌታ እንደሚያዝን



ርኅራኄውን አይተዋል። በወቅቱ ለነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች የሚመልሰውን መልስ አዳምጠዋል። ራሳቸውን ጻድቅ የሚያደርጉ ፈሪሳውያንን፤ በገንዘብ ፍቅር የተነደፉትን ሰዱቃውያንን፤ ብልሹ አካሄድ ያላቸውን የሄሮድስ ወገን የሆኑትን ሁሉ እንዴት እንደገጠማቸው አሳይቶአቸዋል። ሰዎች የሙሴን ሕግ እንዴት ለራሳቸው ጥቅም እንደተረጎሙትና እንዳጣመሙት እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል።

አንድ ሚስዮናዊ ወደ ሕንድ አገር ሄዶ ሁለት ዓመታትን ከቆየ በኋላ ቋንቋቸውን መናገር ስላልቻለ የላከው ሚስዮን ድርጅት ወደ ቤቱ እንዲመለስ ደብዳቤ ይጽፍለታል። ሚስዮናዊው በተላከበት አገር ያሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ደብዳቤውን አሳይቶ ሊሰናበት ሲሄድ ሽማግሌዎቹ ደግሞ ሌላ ደብዳቤ አስከንጽፍ ቆይ ብለው «ይህ ሚስዮናዊ ምንም እንኳን የአፋችንን ቋንቋ ባይናገር የልባችንን ቋንቋ ስለሚናገር እንዲመለስ አንፈቅድም አሉ» ይባላል። ከሰው የአፍ ቋንቋ የተማረ ሰው ሊረሳ ይችላል፤ የልብን ቋንቋ የተማረ ሰው ግን ፈጽሞ ሊረሳ አይችልም።

*2. በማስተማር አሰለጠናቸው።*

ከኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቶች አንዱ ማስተማር እንደሆነ የወንጌላት ጸሐፊዎች በተደጋጋሚ ጠቅሰውታል። ኢየሱስ ከሚጠራባቸው ስሞች አንዱ «መምህር» የሚለው ነው ማቴ. 10፡ 24)። «ሊቅ» ተብሎም ተጠርቷል (ማቴ.

23:10)። በምኩራቦቻቸው አስተምሯል (ማቴ. 9:35)። ደቀ መዛሙርቱ እርሱን መስለው ክኖሩ በቂ እንደሆነ ሲገልጽም «ደቀ መዝሙር ክመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል» (ሉቃ. 6:40) አለ። ጌታ ኢየሱስ ራሱ «እኔ ጌታና መምህር ስሆን» ብሎ በዮሐ. 13:14 ማስተማር አገልግሎቱ እንደሆነ ገልጾላቸዋል።

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማረው በብዙ መንገድ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ስለ ኢየሱስ እንዲጠይቁት በላከ ጊዜ ስለ ራሱ ስለ መጥምቁ ዮሐንስና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተማራቸው (ማቴ. 11:7-19)።

ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ሲሆኑ በጉባዔ ያስተማራቸውን ነገር መልሰው ሲጠይቁትና ሲያስረዳቸው፤ ሲወያዩም ነበር። አንድ ባለጠጋ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ያለውን ሁሉ ሸጦ ለደሆች ሰጥቶ እንዲከተል ሲጠየቅ አዝኖ ትቶ ሲሄድ ስለ ብልጥግና፤ ስለ ደኅንነት፤ ስለ ዋጋ መክፈል፤ ስለሚመጣው መንግሥት፤ ስለ ፍርድና ስለ ዘላለማዊው ሕይወት አስተማራቸው (ማቴ. 19:22-30)።

የያዕቆብና የዮሐንስ እናት መጥታ በመንግሥቱ አንዱ ልጇ በቀኙ፤ አንዱ ደግሞ በግራው እንዲቀመጡ በጠየቀች ጊዜ ስለ መከራ፤ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ፤ ስለ ሚመጣው መንግሥት፤ ስለ መሪነት፤ ስለ ትህትና፤ አገልጋይ ስለ መሆንና ለብዙዎች ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ስለማቅረቡ አስተማራቸው (ማቴ. 20:20-28)።



አንዲት ደሀ መበለት ክአንድ ሳንቲም የማይበልጡ ሁለት ናሶችን በመባ ዕቃ በጣለች ጊዜ ስለ ቤተ መቅደስና አንድን ስጦታ ዋጋ እንዲኖረው የሚያደርገው ምን እንደሆነ አስተማራቸው (ማር. 12:41-13:2)።

ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ በምሳሌ ያስተምርና ለደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ደግሞ ምሳሌውንና ትርጉሙን ሁሉ ያስረዳቸዋል (ማር. 4:33-34)። ምክንያቱም እነርሱ ከትንሣኤው በኋላ አገልግሎቱን የሚሸከሙና ሕዝቡንም የሚመሩ ስለሆኑ በትክክል መረዳት ነበረባቸው።

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትምህርት መጀመሪያ በክፍል ውስጥ ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ ተማሪዎቹ በመስክ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። ኢየሱስ ግን መጀመሪያ እንዲለማመዱት ካደረገ በኋላ ትርጉሙንና ለምን እንደሚያደርጉት ያስረዳቸዋል።

*3. በጸሎት ሕይወት ምሳሌነት አስተማራቸው።*

ደቀ መዛሙርቱ በኢየሱስ ሕይወት ክሚያዩአቸው ነገሮች አንዱ የጸሎት ሕይወቱን ነበር። በእያንዳንዱ አገልግሎትና ሥራ የአባቱን ፈቃድ እየጠየቀና እየጸለየ እንደሚያከናውን አይተዋል። ለረጅም ሰዓታትና አንዳንድ ጊዜም ሌሊቱን ሙሉ ለደቀ መዛሙርቱና ክእነርሱ ጋር ላሉት ሰዎች እየጸለየና እያማለደ ሲያሳልፍ፤ (ሉቃ. 6:12) ለጸሎት ለብቻው ወደ ለዋራ ቦታዎች ሲሄድ (ማቴ. 6:6፤ ሉቃ. 5:16) ተመልክተዋል። እርሱ እንደ ጸለየ እነርሱም እንዲጸልዩ አስተምሮአቸዋል (ማቴ. 6:5-13)። የመከሩ ጌታ

ለመከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ እንዲጸልዩ (ማቴ. 9:37-38)፤ ለጠላቶቻቸውና ለሚያሳድዱአቸው እርሱ እንደ ጸለየ እንዲጸልዩ (ሉቃ. 6:28)፤ በድካማቸው ወቅት ወደ ፈተና እንዳይገቡ ተግተው መጸለይ እንዳለባቸው (ሉቃ. 22:40)፤ በጉድለታቸው ጊዜ «የዕለት እንጀራ እንዲሰጣቸው እንዲጸልዩ (ማቴ. 7:7-11) አስተምሮአቸዋል።

ጌታ በቃል ብቻ ሳይሆን በኑሮው ምሳሌነት ሳይታክቱ ሁል ጊዜ መጸለይ እንዳለባቸው (ሉቃ. 18:1) አሳይቶአቸዋል። የኢየሱስ ጸሎት እንዴት ይመስል እንደነበረና አገልግሎቱ እንዴት የተከናወነ እንደነበረ እይተዋል (ዮሐ. 11:22--42)። ከዚህ የጸሎት ልምምድ በኋላ በጸሎት መትጋት የአገልግሎታቸው ቁልፍ እንደነበረ የሐዋሪያት መጽሐፍ ይነግረናል።

*4. በዓላማው በመጽናት አለለጠናቸው።*

ዕብ. 4:15 «ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም» ይላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ስለሆነ እንደ ሰው በምድር ላይ በሁሉ መንገድ ተፈትኗል። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ረጅም መንገድ ተጉዟል፤ የፀሐይ ሙቀት፤ አውሎ ነፋስና ወጀብ፤ የሕዝብ ተቃውሞ፤ ጥማትና ድካም ሁሉ ተፈራርቀውበታል። በዚህ ሁሉ ግን በየቀኑ በመቅደስ ያስተምር እንደ ነበር ደቀ መዛሙርቱ እይተዋል (ሉቃ. 21:37)። እነርሱ በመጽናት መልካም ፍሬ ማፍራት እንዳለባቸው አስተምሮአቸዋል (ሉቃ. 8:15)።



*5. በፍቅር ኑሮ አለለጠናቸው።*

ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ሁሉ የመውደድ ፍቅሩ ከሰማይ እንዲመጣ አደረገው። በሕይወቱም ከሚያሳየው በሁኔታዎች ከማይወሰነው ፍቅሩ ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ተምረዋል። እነርሱ ራሳቸው የተለያየ ባሕርይ ነበራቸው። ለተጎዱት፤ ለታመሙት፤ ማየት ለተሣናቸው፤ መስማት ለተሣናቸው፤ ለሸባዎች፤ በአጋንንት ለተያዙ፤ ለ12 ዓመት ደም ለፈሰሳት፤ ለሞቱት ሳይቀር ፍቅሩን ሲገልጽ እይተዋል። በሰው ለተናቁ ለቀራጮችና ለአመንዝራዎች ጭምር ፍቅሩን አሳይቷል። ለዓይነ ስውሩ ቤርጤሜዎስ ቆሞ ጥሩት ሲል፤ አንድ ልጇ ለሞተባት መበለት ሴት ቆሞ ቃሪዛውን ነክቶ ሲያስነሳው እይተዋል። ተልዕኮው ኃጢአተኛ የሆነውን ዓለም ለማዳን ስለሆነ ሰውን ሁሉ ይወድ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ራሳቸው አንዳንድ ጊዜ ሲስቱ፤ እምነታቸው ሲፈተን ሁሉ ፍቅሩ ግን ያው ነበር። ሊይዙት ከመጡት የአንዱን ጆሮ ጴጥሮስ በሰይፍ ሲቆርጥ ጌታ ግን መልሶ ሲፈውሰው እይተዋል። ከዚህም የተነሳ ጴጥሮስ «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል» (1ጴጥ. 4:8) ብሎ ሲጽፍ ዮሐንስ ደግሞ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (1ዮሐ. 4:16) ብሏል። በመጨረሻ ሊያዝ በነበረ ጊዜ ሊክድ ያለውን ጴጥሮስን፤ አሳልፎ ሊሰጥ ያለውን ይሁዳን፤ ከሞት ሲነሣ «በችንካር የተወጋውን እጁንና ጎኑን ካላየሁ አላምንም» የሚለውን ቶማስን ጭምር እግራቸውን አጥቦ የመጨረሻ

ፍቅሩን ገለጠላቸው። በመጨረሻም ከዚህ ፍቅር የተነሳ ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሰጠ። ይህን የተመለከተው ዮሐንስ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» (ዮሐ. 15:13) አለ። የኢየሱስ ፍቅር አቻ የሌለው በሁኔታዎች ያልተወሰነ ነበር።

*6. ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ አስተማራቸው።*

ኢየሱስ የመጨረሻ ያደረገው ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለዓለም መዳን መስጠት ነበር። ጠራቸው፤ ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ አደረገ፤ አሰለጠናቸው፤ በመጨረሻም ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ያደረገውን ስለ ተመለከቱ እነርሱም መንፈስ ቅዱስ ከመጣ በኋላ በፍጹም መስጠት ሲያገለግሉና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየን ብዙዎቹ በወንጌል ምክንያት ሰማዕት እንደሆኑ እንመለከታለን።

መ. ላካቸው።

ታላቁ ተልዕኮ በአራቱም ወንጌላትና በሐዋሪያት ሥራ ተጽፎ እናገኛለን። «እንግዲህ ሂዱና . . . ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» (ማቴ. 28:18-20)፤ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» (ማር. 16:15)፤ «እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ» (ሉቃ. 24:48)፤ «አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» (ዮሐ. 20:21)፤ «. . . በኢየሩሳሌም፤ በይሁዳም፤ በሰማርያም፤ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋ. 1:8)። ይህ እንግዲህ



ለታላቁ ተልዕኮ ምን ያህል አጽንዖት እንደ ተሰጠው ያሳየናል።

ይህ ግን መጀመሪያ እየላካቸውና እያገለገሉ ከጌታ ጋር በቆዩባቸው ጊዜያት ከሦስት ዓመታት ሥልጠና በኋላ ኃላፊነትን ለመሸከም ብቁ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው። መጀመሪያ አሥራ ሁለቱን ላካቸው (ማቴ. 10:7)፤ ቀጥሎ ደግሞ ሰባዎቹን ላካቸው (ሉቃ. 10:1)። በሚሄዱበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን እንደሚያዘጋጅላቸው በመተማመን እንዲሄዱ አዘዛቸው። በነጻ የተቀበሉትንም በነጻ እንዲሰጡ ነገራቸው (ማቴ. 10:8)። አገልግለው ሲመለሱም ስላዩትና ስለነበራቸው ጊዜ እንዲያመሰግኑና እንዲጸልዩ፤ እንዲወያዩም ጸጥ ወዳለ ቦታ ይወስዳቸው ነበር።

ጌታ ሊያዝ በነበረበት በመጨረሻው ምሽት አሥራ ሁለቱን ለፋሲካ እራት ሰበሰባቸው። እዚያ ደቀ መዛሙርቱ በሕይወት ዘመናቸው ሊረሱ ያልቻሉትን አራት ነገሮችን አደረገ።

1. ሊረዱ የሚያስፈልጋቸውን እውነት አስረዳቸው። ስለ አገልጋይነት፤ ስለ አባቱ፤ ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለ ራሱ እምላክነት ነገራቸው። ስለ ሕይወት፤ ሞት፤ ጸሎት፤ ፍሬ ስለ ማፍራትና ስለ መጨረሻው ድል ሁሉ አስረዳቸው።
2. እውነተኛ በሆነ ኅብረት የልቡን አሳብ ገለጠላቸው። ስለ እውነተኛ ፍቅር፤ አልፎ ስለ መስጠቱ፤ ስለ

መስየት፤ ስለ ክብር፤ ስለ ክህደት፤ ስለ ስደት፤ ስለ ኃዘንና ደስታ ሁሉ የልቡን ገልጦ ነገራቸው።

3. ተራ በሚመስል ምግብ ነገር ግን ትልቅ ትርጉም ባለው ግብዣ አብሮአቸው አሳልፎአል። ለዓለም ሁሉ ኃጢአት የሚቆረሰው ሥጋ ምሳሌ የሆነውን እንጀራ አንስቶ፤ ለዓለም ኃጢአት የሚፈሰውን የደሙ ምሳሌ የሆነውን ወይን አንስቶ ሰጣቸው።
4. በጸሎት እነርሱንም አገልግሎታቸውንም ለአባቱ አሳልፎ ሰጠ። ደቀ መዛሙርቱ ደስታ እንዲኖራቸው፤ አብ አባቱ እንዲጠብቃቸው፤ እውነተኛ መረዳት እንዲኖራቸው፤ ስለ ቅድስና፤ ስለ አንድነትና እርስ በርስ መዋደድ፤ ለዓለም መስካሪዎች እንዲሆኑ ጸለየላቸው። ክዚያ በኋላ መዝሙር ዘምረው ወጡ።

ከላይ የተጠቀሱትንና በውስጡ የተካተቱትን ስንመለከት የኢየሱስን ስልት በሚከተለው ሁኔታ ልናጠቃልለው እንችላለን።

- የራሱ የሆኑትን በጥንቃቄ መረጣቸው።
- ተግባራዊ በሆነ ምሳሌነት አሰለጠናቸው።
- በግልጽ ሁሉንም ነገር ከእነርሱ ጋር ተወያየ።
- ለወንጌል ስርጭት አዘጋጃቸው።
- በእምነት እንዲኖሩ አስተማራቸው።
- ለአጭር ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ልኮ አለማመዳቸው።



- ክዚያ በኋላ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» አላቸው።

የኢየሱስ ክርስቶስ የአገልግሎት ስልት ልንከተለው የሚገባ፤ የጣልነውን ልናነሳ፤ ያልተስማመድነውን ልንለማመድና በሳትንበት ነገር ላይ ልናስተካክል የሚገባን ምሳሌያዊ ሕይወት ነው።

## 7. የጳውሎስ የወንጌል ስርጭት ስልት

በተልዕኮና በወንጌል ስርጭት አገልግሎት ሐዋሪያው ጳውሎስ ከጌታ ኢየሱስ ቀጥሎ ትልቁ ምሳሌያችን ነው። ሉቃስ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ እንደ ጠቀሰው ጳውሎስ ወንጌልንና ክርስቲናን ያስፋፋ ትልቅ ሐዋሪያ ሲሆን ለወንጌል አገልግሎትም ብዙ ርቀቶችን እንደ ተጓዘ ይነግረናል። በምኩራቦች፤ በገበያ ቦታዎች፤ በሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾችና በመሳሰሉት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወንጌልን ሰብኳል። እዚህጋ ግን ትልቁ ጥያቄ ጳውሎስ የወንጌል ስርጭት ዘዴ ነበረው ወይስ መንፈስ ቅዱስ እንደ መራው ይሰብክ ነበር? የሚለው ነው።

እንደ ማይክል ግሪን ያሉ ምሁራን ጳውሎስ ምንም ስልት አልነበረውም፤ቢኖርም በጣም ትንሽ ነው። ወንጌል የተሰራጨው ባልታቀደ መንገድ መንፈስ ቅዱስን በመታዘዝና ጌታም በር እንደ ከፈተለት ነው። እኛ ልንማር የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ መደገፍን ብቻ ነው ይላሉ። እንደ ዶናልድ ማክጋቭራን ያሉት ደግሞ ጳውሎስ በአንጾኪያ በነበረ ጊዜ የሜዲቴራኒያንን አካባቢ አገሮች በወንጌል

ለመድረስ ስልት አዘጋጅቶ ነበር:: ስለዚህም ጳውሎስ ወንጌልን ለማስራጨት ስልት ነበረው ይላሉ:: ሄርበርት ኬን የተባለ ጸሐፊ ደግሞ ጳውሎስ በአንድ በኩል በመንፈስ ቅዱስ የሚደገፍ ሲሆን በሌላ በኩል ግን የራሱ የሆነ ስልትም ነበረው በማለት ሁለቱን የሚያስታርቅ አሳብ እንዲህ በማለት ያቀርባል::

እኛ ራሳችንን ጳውሎስ የወንጌል ተልዕኮ ስልት ነበረውን? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን:: አንዳንዶቹ አዎን ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ አይ አልነበረውም ይላሉ:: በአብዛኛው የሚወስነው ስልት ለሚለው ቃል በምንሰጠው ትርጉም ነው:: ስልት ስንል አቅደ፤ በጽሑፍ አዘጋጅቶ፤ በጥናት ተመስርቶ ለተግባር የተዘጋጀ ማለት ከሆነ ጳውሎስ ስልት አልነበረውም ወይም በጣም ትንሽ ስልት ነበረው ማለት እንችላለን:: ነገር ግን ስልት ስንል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የታቀደ፤ በሁኔታዎች ሊለወጥ የሚችልና ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ተገዢ የሆነ ብለን ካሰብን ጳውሎስ ስልት ነበረው::

ሉቃስ በሐዋሪያት ሥራ እንደ ጠቀሰውና ጳውሎስ ራሱ በመልእክቶቹ እንደ ጻፈው ለወንጌል ስርጭታችን ከጳውሎስ የምንማራቸው አራት የወንጌል ስርጭት ስልቶች አሉ::

### 7.1. በመንፈስ ቅዱስ መመራት (ሐዋ. 16:6-10)

*«በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው በፍርግያና በገላቲያ አገር አለፉ፤ በሚስያም አንጻር በደረሱ ጊዜ ወደ ቢታኒያ ይሄዱ ዘንድ ሞከሩ፤ የኢየሱስ መንፈስም **አልፈቀደላቸውም**፤ በሚስያም አጠገብ አልፈው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ:: ራእይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው፤ አንድ የመቄዶኒያ ሰው፡- ወደ መቄዶኒያ ተሻገርና እርዳን እያለ ቆሞ ሲለምነው ነበር:: ራእዩንም ካየ በኋላ ወዲያው ወደ መቄዶኒያ ልንወጣ ፈለግን፤ ወንጌልን እንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራን መስሎናልና» (ሐዋ. ሥራ 16:6-10)::*



ጳውሎስና ባርናባስ በምዕ. 13 በመንፈስ ቅዱስ ጥሪ ለወንጌል ሥራ ተለይተው ወጥተው አብረው በብዙ ስደትና መከራ እግዚአብሔር ብዙ ምርኮ እየሰጣቸው ካገለገሉ በኋላ በ15:36-41 በማርቆስ ምክንያት ሳይግባቡ ሲቀሩ ባርናባስ ማርቆስን ሲመርጥ ጳውሎስ ሲላስን ይዞ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ሄዱ:: በምዕ. 16 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን አግኝቶ ጉዞውን በቀጠለበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ጣልቃ ገባ::

በዚህ ክፍል በግልጽ እንደምንመለከተው የጳውሎስ ዕቅድ በእስያ ቃሉን ሊሰብክ ነበር፤ ነገር ግን ተከለከሉ:: ወደ ቢታኒያም ሊያልፍ ሞከሮ አሁንም መንፈስ ቅዱስ አልፈቀደላቸውም:: በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ቆም ብሎ ያሰበና የጸለየ ይመስላል፤ ምክንያቱም ዕቅዱን መንፈስ ቅዱስ ከከለከለው አሁንም ፈቃዱንና ምሪቱን ማወቅ ነበረበት:: ለዚህ ነው በቆላስይስ 4:2-4 «. . . የክርስቶስን ምሥጢር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ» ያለው::

በዚህ ክፍል ሉቃስ ትኩረት ሰጥቶ የሚናገረው ነገር በወንጌል አገልጋዮች አገልግሎት ከራሳቸው ዕቅድ ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ቀዳሚ መሆኑን ነው:: መንፈስ

ቅዱስ እነ ጳውሎስን ወደ እስያና ቢታኒያ እንዳይሄዱ ከልክሎ ወደ መቄዶኒያ በሚመራበት ጊዜ ጳውሎስ በሙሉ ፈቃደኝነት ታዘዘ።

### 7.2. ሰዎች ካሉበት ሁኔታ መጀመር

ለጳውሎስ አገልግሎት ስኬት አንዱ የሰዎችን ሁኔታ ተመልክቶ በዚያ ሁኔታ መሠረት ወንጌልን መስበኩ ነው። የሐዋ. 17:22-31ን ስንመለከት ጳውሎስ ሲላስንና ጢሞቴዎስን በአቴና እየጠበቀ እያለ በከተማይቱ ጣዖት መሙላቱን አየ። ለተለያዩ ጣኦታት መቅደሶች፣ መሠዊያዎችና ምስሎች ቆመው ነበር። ከተተከሉት ውስጥ ግን የጳውሎስን ዓይን የሳበው በአንደኛው ላይ የተጻፈው «ለማይታወቅ አምላክ» የሚል ጽሑፍ ነበር። ጳውሎስ «እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ» ሲል እነርሱ የሠሩትን የጣዖት መሠዊያ ወይም አምላክ ብለው ያቆሙትን ማስተዋወቁ ወይም ማድነቁ አልነበረም። ይልቅስ እነርሱ «ለማይታወቅ» ያሉትን እንደ መነሻ በማድረግ እውነተኛውና የሚያድነው አምላክ ማን እንደሆነ ለመንገር እንደ መሣሪያ ተጠቀመው። በዮሐ. 4 ጌታ ኢየሱስ የሰማርያዊቷን ሴት ትኩረት ከሚጠጣው ምድራዊው ውኃ ወደ ሕይወት ውኃ እንደ ቀየረው ጳውሎስም የጣዖት እምልከ አስተሳሰባቸውን ወደ እውነተኛ ውና ሰማይንና ምድርን ወደ ፈጠረ አምላክ ሲያዞር እንመለከታለን። አቴናዊያን እውነተኛውን አምላክ ሳያውቁ



በጣዖት አምልኮ ይኖሩ ነበር። ይህ ጽሑፍ ግን ጳውሎስ አስተሳሰባቸውንና አመለካከታቸውን እንዲቀይሩ አስችሎታል። ጽሑፉ አቴናዊያን እውነተኛውን አምላክ አለማወቃቸውን ሲያሳይ ለጳውሎስ ግን ወንጌልን ለመስበክ በር ከፍቶለታል።

ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 4 ያደረገው ይህንኑ ነበር። ሴቲዮዋ ወደ ያዕቆብ ጉድጓድ የመጣችው ውኃ ልትቀዳ ነው። ጌታ ደግሞ ስለ ሕይወት ውኃ ለመናገር መነሻ ያደረገው ቀን በጠራራ ጸሐይ ወደ ጉድጓድ ያመጣትን ምድራዊ ውኃ ነው። ይህም ስለ ሕይወት ውኃ እንድትሰማ ልቧንና ጆሮዋን እንድትከፍት አደረገ።

### 7.3. የሕይወት ምስክርነትን መናገር

ጳውሎስ የተጠቀመው ሌላው ስልት የራሱን የሕይወት ምስክርነት መናገር ነበር። በግል ምስክርነት ወቅት የሕይወት ምስክርነትን መናገር ጠቃሚ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። ጳውሎስም በተደጋጋሚ ይህንን ያደርግ ነበር። ጳውሎስ በኢየሩሳሌም መቅደስ ወንጌልን ሲሰብክና በተለይም የአይሁድን ሥርዓት ከመጠበቅ ጋር በተያያዘ ያስተማረውን ትምህርት በስሕተት ተረድተው ስለነበር ለማስተማር ወደ መቅደስ ገብቶ እያለ ከእስያ የመጡ አይሁድ ሰደት አስነስተው ይደበድቡት ነበር። በዚህ ወቅት የጭፍራው ሻለቃ ከወታደሮቹ ጋር መጥቶ እስጣለው (21:15-40)። በ22:4-16 ሻለቃውን አስፈቅዶ የተናገረው

እርሱ ራሱ አይሁዳዊ ሆኖ ለሃይማኖት በመቅናቱ ቤተ ክርስቲያንን የሚያሳድድ ሰው እንደ ነበረና ጌታ እንዴት እንደ ለወጠው የራሱን ምስክርነት ነበር። በንጉሥ አግሪጳ ፊት በቀረበም ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነው (ም.26)።

በሐዋ. 18:1-4 ሉቃስ አንድ ታሪክ ያስነብበናል። አቂላና ጵርስቂላ የተባሉ ባልና ሚስት አይሁዳውያን ሁሉ ሮምን ለቀው እንዲወጡ ቄሣር ባዘዘው መሠረት ከሮም ወጥተው ወደ ቆሮንቶስ መጥተው ድንኳን እየሰፉ ይኖሩ ነበር። ጳውሎስም ሥራቸው አንድ ስለ ነበር ከእነርሱ ጋር በመሆን ድንኳን እየሰፋ ወንጌልን ይመሰክር ነበር። ይህንንም ሁኔታ አስመልክቶ አገልጋዮች ለሌላው ሸክም መሆን እንደ ሌለባቸውና መሥራት እንዳለባቸው ይመሰክር ነበር። በ1ተሰ. 2:9 «. . . ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን» ይልና በ2ተሰ. 3:8 በተመሳሳይ «ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም» ይላል። ይህ ምስክርነት አገልጋዮች በአገልግሎት ብቻ ሳይሆን በሥራም መልካም ምሳሌ መሆን እንዳለባቸው ያሳያል።

በ1ቆሮ. 9:14-15 ጳውሎስ ወንጌልን የሚያገለግል አገልጋይ ከወንጌል ቀለብ ማግኘት እንዳለበት መጽሐፍ እንደሚደነግግ ይናገራል፤ ነገር ግን ይህን መብት አልተጠቀምኩም ይላል።



ይህን መብት ያልተጠቀመባቸውን ሁለት ምክንያቶች ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ያብራራል።

የመጀመሪያው ለማንም ሸክም መሆን ስላልፈለገ ነው። «ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት . . . » 1ተሰ. 2:9፤2:ተሰ. 3:8
ሁለተኛው ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን ነው። «እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና . . . ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን . . . ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም» 2ተሰ. 3:7-9።

ጳውሎስ ጌታ እንዴት እንደ ለወጠውና በእጁም እንዴት በድካምና በጥረት እየሠራ እንዳገለገለ ብቻ ሳይሆን አገልግሎታቸው በብዙ ዋጋ መከፈል እንደነበረ በ1ተሰ. 2:1-12 እንዲህ ሲል ይናገራል።

- በብዙ ገድል የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ እንናገር ዘንድ በአምላካችን ደፈርን ቁ. 2
- እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን እንዲሁ እንናገራለን ቁ.4ሀ
- ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም ቁ. 4ለ
- እያቆላመጥን ከቶ አልተናገርንም ቁ. 5
- ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም ቁ. 6

- ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትከባከብ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን ቁ. 7
- እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ ቁ. 8
- ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን ቁ. 9
- በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ነቀፋ በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ ቁ.10
- እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደሆንን ታውቃላችሁና ቁ. 12

ከእነዚህ አባባሎች እንደምንረዳው ሐዋሪያው በምን ያህል መስዋዕትነትና ፍቅር እንዲሁም ወንጌልን ሳያመቻምች እንደ ሰበከ በግልጽ ያሳየናል፡፡ ጳውሎስ ይህንን ያደረገበት ምክንያት አገልግሎቱ ውጤታማ እንዲሆንና ምስክርነቱ ለሌሎች ትምህርት ስለሆነ ነው፡፡ ለተጻፈላቸው ለመጀመሪያ ተደራሲያን ብቻ ሳይሆን ዛሬ እኛም በተለይም በወንጌል አገልግሎት የተሰማሩ አገልጋዮች ራሳቸውን ሊያዩበት የሚገባ መስተዋት ነው፡፡



### 7.4. መልእክትን እውዳዊ ማድረግ

1ቆሮ. 9:19-23 ስንመለከት ጳውሎስ «. . . በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ» ይላል፡፡ እዚህጋ ሁሉ ሲል የጠቀሳቸው አይሁድ፤ ከሕግ በታች ያሉት፤ ሕግ የሌላቸውና ደካሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የራሳቸው የሆነ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ልምምድ አላቸው፡፡ ጳውሎስ ወንጌልን የሰበክሁት በእነርሱ አውድ ነው ይለናል፡፡ ይህ ማለት ጳውሎስ እያመቻመቸ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይልቅስ መልእክቱን እውዳዊ እያደረገው ነበር፡፡ ከአይሁድ ጋር እንደ አይሁድ ሆንሁ ሲል አይሁድ የሚያከብሩአቸውና የሚያደርጓቸው ሥርዓቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ መገረዝ (1ቆሮ. 7:19፤ገላ. 6:15)፤ የምግብ ሕጎች (1ቆሮ. 8:8፤ ገላ. 2:10-13፤ ሮሜ. 14:17፤ ቆላ. 2:16)፤ ሌሎችም ሥርዓቶች ነበሩ (ቆላ. 2:16)፡፡ ጳውሎስ እነዚህን ለማክበር ግዴታ የሰበትም፡፡ እርሱ በጌታ ነፃ ነው፡፡ ነገር ግን አይሁድን ለማዳን ሲል መብላት የሚፈልገውንም ባለመብላት፤ ቃሉ ያልከለከለውን ለእነርሱ ሲል በመከልከል ወንጌልን ሰብኳል፡፡

አሕዛብ ደግሞ ሕግን የሚጠብቁ አይደሉም፡፡ ጳውሎስ እነዚህን ለመማረክ ሲል ኃጢአት እስካልሆነ ድረስ እነርሱ የሚያደርጉትን እያደረገ ሰበከላቸው፡፡ ማመቻመችና እውዳዊነት የሚመሳሰሉ ግን ፍጹም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ማመቻመች በይሉኝታ የወንጌልን መልእክት

በማጣመም ሰውን ለማስደሰት የሚደረግ ስብከት ሲሆን አውዳዊነት ግን የወንጌል መልእክት ይዘት ሳይቀየር በኅብረተሰቡ ባሕልና አኗኗር እየኖሩ ወንጌልን መስበክ ነው። ስለዚህም ጳውሎስ እያመቻመቸ ሳይሆን እንደየባሕላቸው መልእክቱን ሳያዛባ ይሰብክላቸው ነበር።

## 8. የወንጌል ስርጭት ስሕተቶች

በአሁን ጊዜ ብዙ ወንጌል መስካሪዎች የሚጠቀሙአቸው ነገር ግን ትክክለኛ ያልሆኑና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌላቸው አቀራረቦች አሉ። እነዚህ የተለመዱ ስሕተቶች ሲሆኑ ብዙ ሰዎች ግን ስሕተት መሆናቸውን አይረዱም። ከእነዚህ ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው።

**8:1. የተሳሳተ ግብዣ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ና**

ለሰዎች ወንጌልን ስንመሰክር ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ና ማለት የተለመደ ግብዣ ነው። ይህ ግብዣ ሁለት ችግሮች አሉበት። የመጀመሪያው ሰዎችን ወደ ኢየሱስ እንዲመጡና ጌታን ለመቀበል ከወሰኑ ወይም ከተቀበሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ እንጋብዛቸዋለን። ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ኑ ስንላቸው የሚያድናቸው ቤተ ክርስቲያናችን መምጣታቸው እንደሆነ ያስባሉ፤ አባባሉም ይመስላል። ሐዋሪያው ጳውሎስም ሆነ ሌሎች በእግዚአብሔር ቃል የምንመለከታቸው ሰዎች እንደዚህ አልጋበዙም። ሁለተኛው ችግር ሰዎች በተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት ያለውን ችግር ስለሚያውቁ ወዲያው



የሚመልሱልን መልስ «የእናንተ ከእኛ በምን ይሻላል?» የሚል ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በሚገባ ያላወቁ ሰዎች መንፈሳዊ ጥማት አለባቸው። በጌታ ማረፍም ይፈልጋሉ። ነገር ግን ሰዎችን የሚያረካ የሕይወት ውኃ ያለውንና የሚያሳርፈውን ኢየሱስን ትተን ቤተ ክርስቲያናችንን ስለምናሳይ፤ አንዳንዴም «ወደ እኛ ኑ» ስለምንል እንቅፋት ይሆንባቸዋል።

**8.2. ትችት፡ የእናንተ ልክ አይደለም**

ሰዎች ሁሉ የያዙአቸውን ሃይማኖቶችና እምነቶች ትክክለኛ እንደሆነ ያምናሉ። ለማመን የራሳቸው መረጃም አላቸው። ይህን ስለማይረዱ ብዙ ሰዎች ሲመሰክሩ «የእናንተ ልክ አይደለም» በማለት ይጀምራሉ፤ይተቻሉ። ለምሳሌ ለሙስሊሞች ሲመሰክሩ መሐመድ የሞተ ስለሆነ ለሕይወታችሁ አስፈላጊ አይደለም ይላሉ። ነገሩ እውነት ነው፤ ነገር ግን ይህ እነርሱ መስማት የሚፈልጉት ነገር አይደለም። ለእነርሱ መሐመድ የአላህ መልእክተኛና የመጨረሻው ነቢይ ነው። ለኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችና ለካቶሊኮች ስለ ማርያምና ስለ መላእክት ባላቸው አመለካከት ላይ መተቸት ማስቆጣት ብቻ ሳይሆን የወንጌልን እውነት እንዳይሰሙ በር ይዘጋባቸዋል። ጌታ ኢየሱስ ፍጹም ሰው ሆኖ እያለ ኃጢአተኛ ከሆነች ሰማርያዊት ሴት ጋር ሲነጋገር ሕይወቷንና ኑሮዋን አልተቸም። ይልቅስ የተቸገረችበትን የውኃ ጥማት መነሻ በማድረግ የሕይወት ውኃን ሰጣት። ጳውሎስ በአቴና ጣዖት መሙላቱን ተመልክቶ መንፈሱ

ቢበሳጭበትም «ለማይታወቅ አምላክ» ብለው የጻፉትን ጽሑፍ ምክንያት በማድረግ እውነተኛውን አዳኝ አስተዋወቃቸው:: ስለዚህም ለሰዎች የወንጌልን እውነት ተናግረን ወደ ሕይወት መምራት እንጂ እምነታቸውን መተቸት አግባብ አለመሆን ብቻ ሳይሆን የወንጌልን እውነት እንዳይሰሙ ጆሮአቸውን የሚደፍንባቸው እንቅፋት ነው::

## 8.3. አላስፈላጊ ክርክር

በወንጌል ምስክርነት ሌላው ችግር አላስፈላጊ ክርክር ወይም ሙግት መግጠም ነው:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከእግዚአብሔር ቃል እውነትን በመግለጥ መሞገትና ዝም ማሰኘት ተገቢ ነው:: እንዳንድ ጊዜ ግን በማይመስል ጉዳይ አላስፈላጊ የሆነ ሙግትና ክርክር ይገጠምና ለወንጌል ስብከት በር ይዘጋል፡፡ ብዙ ጊዜ ወንጌልን ለመመስከር ስጀምር «እኔ ከእናንተ ጋር መከራከር አልፈልግም» ያሉኝን ሰዎች አውቃቸዋለሁ:: ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሌሎች ሰዎች እየተከራከሩ ስላሰለቹአቸው ነው:: ጌታ ኢየሱስና ጳውሎስ ከሰዎች ጋር በትምህርታቸው ምክንያት ጥያቄና መልስ ነበሩአቸው፤ ነገር ግን ጭፍን ሙግት አልነበረም:: ንግግራቸውና ትምህርታቸው ጥበብ የተሞላበትና እውነትን በመግለጥ ስለነበር ብዙዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ ምክንያት ሆነዋል::



## 8.4. መናገር ነገር ግን አለማዳመጥ

አንዳንድ ወንጌል መስካሪዎች ጥሩ የምስክርነት ጸጋ አላቸው፤ በሚገባም ይመሰክራሉ:: ነገር ግን የሚመሰክሩላቸውን ሰዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ወይም እንዲናገሩ ዕድል አይሰጡአቸውም:: ሰዎች እውነቱን ለማወቅ ከሚችሉባቸው መንገዶች አንዱ ጥያቄ በመጠየቅና የሚሰማቸውን በመናገር ነው:: አንዳንዶች ጌታን መቀበል እየፈለጉ ያልተረዱአቸው ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ በነጻነት እንዲናገሩ ማበረታታት ወዳጅነትን ከማጠንከርም ሌላ ያልገባቸው ነገር ግልጽ እንዲሆንላቸው ያደርጋል:: የንግግራችን ብዛት ክሰለቻቸው ወስነው ሳይሆን ስመለየት ሲሉ ብቻ ጌታን እቀበላለሁ ሲሉ ይችላሉ:: ከዚያ በኋላ ለወንጌል ጆሮአቸውንም ልባቸውንም ይዘጋሉ:: ያንን መልሶ ለማስከፈት ብዙ ዋጋ ያስከፍላል:: ጥቂት ደቂቃዎችን እነርሱን አለመስማት ለብዙ ጊዜያት ምናልባትም በሕይወት ዘመናቸው ወንጌልንና መልእክተኞቹን እንዳይሰሙ ያደርጋቸዋል::

## 8.5. የወንጌል መስካሪዎች ትዕግስት ማጣት

የወንጌል መልእክት ሦስት ዓይነት ምላሾች አሉት:: አንዳንድ ሰዎች መልእክቱን እንደሰሙ ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኛ ቸውና ጌታቸው አድርገው ለመቀበል ይወስናሉ:: እንዳንዶች ደግሞ የመልእክቱ እውነትነት ቢገባቸውም እንደ መጀመሪያዎቹ ቶሎ አይወስኑም:: ሌላ ጊዜ አያለሁ፤ እስቲ አስብበታለሁ የሚሉ መልሶችን በመመለስ ቀጠሮ ይሰጣሉ::

አንዳንዶቹ ደግሞ ወዲያው የእምቢታ መልስ ይሰጣሉ። ለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን በሚልክበት ጊዜ «በማናቸውም በምትገቡበት ቤት በዚያ ተቀመጡ፤ ከዚያም ውጡ፤ ማናቸውም የማይቀበሉአችሁ ቢሆኑ . . . » (ሉቃ. 9:4-5) ያለው። መመስከር የእኛ ድርሻ ነው፤ ሰዎችን ወደ ጌታ ማምጣት የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ነው። አንዳንድ ሰዎች ወንጌልን ከሰሙ በኋላ ዓመታትን ቆይተው ወደ ጌታ ሊመጡ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ከመስከርን በኋላ ጌታ የሚሠራውን በትዕግስት መጠበቅን ይፈልጋል። ዘርን መዝራት የእኛ ፋንታ ነው: የሚያበቅለው በጊዜው እስከሚያበቅል ድረስ መጠበቅ የጥበበኛ ገበሬ ምልክት ነው። ትዕግስት አጥቶ የተዘራው ዘር አሁኑኑ ካልበቀለ ማለት የተሳሳተ አቀራረብ ነው።

## 9. የወንጌል ስርጭት ቁልፎች

የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያውን ግማሽ ስንመለከት ለሐዋሪያት የወንጌል አገልግሎት ስኬት ቁልፍ የሆኑ አምስት ነገሮችን እናገኛለን።

### 9.1. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል

ጌታ ኢየሱስ በሉቃ. 24:49 ደቀ መዛሙርቱን «እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» አላቸው። በሐዋ. 1:8 ወደ አባቱ ሊያርግ ጥቂት ሲቀረው ደግሞ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ



ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፤ በይሁዳም ሁሉ፤ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» አላቸው። ወደ አባቱ ካረገ በኋላ ደግሞ ተስፋ እንደገባላቸው በሐዋ. 2 መንፈስ ቅዱስን ላከላቸውና በኢየሩሳሌም የነበሩ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልዩ ልሳኖች ተናገሩ።

የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ዋነኛ ዓላማ ሐዋሪያት የክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳዔ ምስክሮች እንዲሆኑ ነው። ሐዋሪያት ግን በደስታ ተሞልተው እየተሚሚቁ በኢየሩሳሌም መቀመጥን መረጡ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ያላሰቡት ስደት መጣባቸው። እስጢፋኖስ ተገደለ፤ በስደቱም ምክንያት የተበተኑት ወገኖች ያለ ውዴታቸው በዙሪያቸው ባሉት አካባቢዎች ሁሉ ወንጌልን እየሰበኩ ዞሩ። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እስመልክተው ነበር ወንጌላዊ አባባ ኤካሶ ባገኙት መድረክ ሁሉ «ኢየሩሳሌምን የበተነ እግዚአብሔር እናንተንም ይበትናችሁ፤ እናንተ እዚህ በሙዚቃ መሣሪያ ታጅባችሁ ትዘምራላችሁ፤ ታጨበጭባላችሁ፤ እዚያ ግን ሰዎች ወደ ሲዖል እየሄዱ ነው» ይሉ የነበረው።

ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት በፊት በማቴ. 26:69-74 እንደምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተናገረው ሦስት ጊዜ የካደው ጴጥሮስ፤ ጌታ ከሞተ በኋላ በዮሐ. 20:19 እንደምናነበው አይሁድን ፈርቶ ደጆቹ በተዘጉበት የተቀመጠው ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከተቀበለ

በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ግራ ስተጋቡ በሺዎች ለሚቆጠሩት ወንጌልን በመስበክ በመጀመሪያ ሦስት ሺህ ሰዎች ሲድኑ ቀጥሎ በሺባው መፈወስ ምክንያት ለተሰበሰቡት ሰዎች የተሰበከው ወንጌል ደግሞ አምስት ሺህ የሚሆኑት በጌታ ኢየሱስ አምነው የሚድኑበትን መንገድ ከፈተ።

በሐዋ. 4 የአይሁድ ሸንጎ በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ ባዘዙአቸው ጊዜ ከዮሐንስ ጋር «እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደሆነ ቁረጡ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም» ያሉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለተሞሉ ነበር።

በጴጥሮስና በዮሐንስ መታሰር ምክንያት ተግተው ይጸልዩ የነበሩ ደቀ መዛሙርት እነርሱ ተፈትተው ከመጡ በኋላ እንደ ገና እንደ ጸለዩ ም.4:23-31 ይነግረናል። ከጸለዩ በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

በመጽሐፉ ውስጥ የምንመለከታቸው ተአምራት ሁሉ የተደረጉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። ሽባዎች ዘለዋል፤ በሽተኞች ተፈውሰዋል፤ መንፈስ ቅዱስን የዋሹ ሐናንያና ሰጲራ በሞት ተቀጥተዋል፤ እጋንንቶች ታዘው ወጥተዋል። ሐዋ. 19:11-12 «እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፤ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፤ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር፤ ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር» ይላል። ይህን ያህል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሠራ ነበር። ይህ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ዓለምን ላጥለቀለቀው የወንጌል መስፋፋት የመጀመሪያው ቁልፍ ነበር።

## 9.2. አንድነት

የመጀሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት የሚያስገርም አንድነት እንደ ነበራቸው የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ይነግረናል። በም.1 ጌታ ኢየሱስ ካረገ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው «በአንድ ልብ» ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር። በም. 2 መንፈስ ቅዱስ የወረደበት በዓለ ኀምሳ በደረሰ ጊዜ ሁሉም «በአንድ ልብ ሆነው» አብረው ነበሩ። 2:46 ላይ «በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ ይተጉ ነበር» ይላል። 4:24 ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከእስር ተፈትተው መጥተው የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ያሉአቸውን በነገሩአቸው ጊዜ «በአንድ ልብ ሆነው» ወደ እግዚአብሔር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንደ ጸለዩ እናነባለን። ቁ. 32 «ያመኑትም ሁሉ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው» ይላል። ይህ እንግዲህ ደቀ መዛሙርት ወንጌልን ሲሰብኩ በውስጣቸው የጠነከረ የልብ አንድነት እንደነበረ በግልጽ ያሳየናል።

ዘፍ. 11:1-9 አንድ አስደናቂ ታሪክ ይነግረናል:: ቁ. 1 «ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች» ይላል:: ከዚህም የተነሳ ላይበተኑ ስማቸውን ለማስጠራት ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለመሥራት ተስማሙ:: ሰው ለራሱ ክብርና ዝና የሚያደርገው ነገር የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ ስለሆነ እግዚአብሔር ለማየት ወረደና አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን ደባለቀው፤ በምድር ሁሉ ላይም በተናቸው:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል አንድነት ምን ያህል ለታሰበለት ዓላማ ግብ መምታት ወሳኝ እንደሆነ የሚያሳይ ነው:: ቁ. 6 ላይ «እግዚአብሔርም አለ:- እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፤ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህንም ለማድረግ ጀመሩ፤ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም» ይላል:: እግዚአብሔር ይህንን ካለ ሰዎች በአንድ ልብ ሆነው ከተነሱ ያቀዱት ሁሉ ይከናወናል ማለት ነው:: ሥራዎች ታቅደው መከናወን ካቃተን መጀመሪያ ልንፈትሽ የሚገባን አንድነታችንን ነው::

አንድነት ለክርስቲያኖች እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው:: አንድነት ከሌለ የወንጌል ሥራ ሲሠራ አይችልም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሠራ ማንኛውም ሥራ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ለማምጣትና አማኞችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ነው:: መሪ ከመሪ ጋር፤ ወንጌላዊ ከወንጌላዊ ጋር፤ አገልጋይ ከአገልጋይ ጋር፤ ምዕመናን እርስ በርሳቸው አንድ ልብ ከሌላቸው ዩቱንም ያህል የተዘጋጀ ገንዘብና ዕቃ ቢኖር



የታሰበውና የታቀደው ዓላማ ሊከናወን አይችልም:: ስለዚህም የወንጌል ሥራ ሲታሰብ አንድነት ወሳኝ ነገር ነው::

## 9.3. ኅብረት

ኮይኖኒያ የሚለው የግሪኩ ቃል ትርጉሙ ኅብረት ማለት ሲሆን ሰዎች ያላቸውን እርስ በርስ መካፈልን ያመለክታል:: ኅብረት ማለት ለው ለአንድ ዓላማ መያያዝን ወይም መተባበርንም ያሳያል:: በዚህ አውድ ከአብ የተላከው መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው መኖሩ ስላስተሳሰራቸው ይህ ኅብረት ደቀ መዛሙርትንና የመጀመሪያዎቹን ምዕመናን በአስቸጋሪ ሁኔታና ስደት ውስጥ እያለፉም ወንጌልን በድፍረት እንዲናገሩና እንዲጠነክሩ አድርጎአቸዋል:: የሐዋሪያት ኅብረት ስጦታዎችን መሰብሰብንና ማከፋፈልንም ያካተተ ሲሆን ይህ ደግሞ ኅብረታቸውን በተግባር የሚገልጹበት የመጀመሪያ መንገድ ነበር (ሮሜ 15:26፤ 2ቆሮ.8:4፤9:13፤ዕብ. 13:16)

ሰዎች ብቻቸውን ከሚሠሩአቸው ነገሮች ይልቅ በኅብረት የሚያደርጓቸው ነገሮች የበለጠ ውጤታማ ከመሆናቸውም ሌላ በቀላሉ ይከናወናሉ:: መክብብ 4:9-12 «አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል:: ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፤ . . . ሁለቱ በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል» ይላል:: ብዙ ሰዎች ይህንን ለትዳር እንደተጻፈ አድርገው ይተረጉማሉ:: ይህ ክፍል የተጻፈው ትዳርን ጨምሮ ዬትኛ

ውንም ዓይነት ኅብረት የሚመለከት ነው:: ለትዳር እንዲሉ የሚያደርገው ዋናው አሳብ «ሁለቱ በአንድነት ቢተኙ» የሚለው ሐረግ ነው:: ይህ ማለት የግድ ባልና ሚስት ማለት አይደለም:: ወንድና ወንድ፤ ሴትና ሴት ቢተኙም አንድ ሰው ብቻውን ከሚተኛ ይሞቃቸዋል:: በዚህ ክፍል ሰሎሞን የመተባበርን አስፈላጊነት ለመግለጽ አባባሉን እንደተጠቀመው ይታመናል::

ኅብረት የሚመጣው አንድነት ሲኖር ነው:: ሰው አንድ አሳብ ከሌለው ሊተባበር አይችልም:: ሐዋሪያት የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና የጠነከረ አንድነት እንደ ነበራቸው ተመልክተናል:: ያ አንድነታቸው ደግሞ እንዲተባበሩ አድርጓቸዋል:: የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍን ስንመለከት፤-

- በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት፤ እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር (ሐዋ. 2:42) :
- ያመኑትም ሕዝብ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት አደረጉ (2:44)::
- ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ፤ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፤ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም (ሐዋ. 4:32)

በነህሚያ ዘመን እንዲሁ ሰዎች ቅጥሩን ለመሥራት ተባበሩ፤ ነህ. 4:15-20:: ይህ ትብብራቸው ቀንደኛ ባላንጣቸው የነበሩት እነ ጦቢያና ሰናባላጥ በአንድ በኩል



ሲያሾፉባቸው (ም.2) በሌላ በኩል ደግሞ የጦር መሣሪያ ይዘው ለውጊያና ለመግደል ሲመጡ (ም.4)፤ በአይሁድ መካከል ያሉ ታላላቅ የተባሉ አቅም፤ ጉልበት፤ ገንዘብና ዕውቀት ያላቸው ሌሎች ሲሠሩ ማስተባበርና ማበረታታት ሲገባቸው እነርሱ ግን ዳር ይዘው ሲቆሙ (ም.3:5)፤ ያም ብቻ ሳይሆን በም. 5 ሕዝቡ ሲራብና ግብር መክፈያ አጥቶ ሲቸገር ገንዘብ እያበደሩ መክፈል ሲያቅታቸው አንዳንዶቹን ባሪያ አድርገው ሲገዙአቸው በዚያ ሁሉ ሁከት መኻል ቅጥሩን እንዲሠሩና እንዲያጠናቅቁ አደረጋቸው::

ሰዎች ለበጎ ነገር ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማያስከብርና አፍራሽ ለሆነ ነገርም ይተባበራሉ::
በዘፍ. 11:1-9 የባቢሎንን ግንብ ሊሠሩ የተነሱ ሰዎች አንድ ቋንቋና አንድ ንግግር ነበራቸው:: ይህ አንድነታቸው ግንቡን ለመሥራት ወደ መተባበር አመጣቸው:: ትብብራቸው ግን እግዚአብሔር የሚከብርበት ሳይሆን ስማቸውን ለማስጠራት ነበር::
ሐዋ. 19:29 «በአንድ ልብ ሆነው ወደ ጨዋታ ስፍራ ሮጡ» ይህ ጳውሎስን ለመደብደብ ነበር:: ሰው ሰውን ለመደብደብና ለማጥፋትም ይተባበራል::

ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ መተባበር በ1ኛ ቆሮንቶስ ገንቢና አፍራሽ የሆኑ ሁለት ዓይነት ኅብረቶች እንዳሉ ይነግረናል::

በ1ቆሮ. 12 አንዱ ከሌላው ጋር ካልተባበረ ጸጋዎች ሙሉ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ በአካል ብልቶች ምሳሌ ሲያስተምር እጅ እግርን፤ ዓይን ጆሮን አታስፈልገኝም ሊሉ አይችሉም ብሎአል:: ለምሳሌ መነጽር የሚደረገው ለዓይን ነው፤ የሚሸከሙት ግን ጆሮና አፍንጫ ናቸው:: ጆሮና አፍንጫ እምቢ ያሉ ዕለት ዓይን አበቃለት ማለት ነው:: የጸጋ ስጦታም እንደዚሁ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዬትኛ ውም ጸጋ ከሌላው ጋር ካልተባበረ ሙሉ ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ መተባበር ግድ ነው::

በ1ቆሮ. 6:14-18 ከማያምኑት ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ብሎ አፍራሽ ስለ ሆነው መተባበርም ያስተምራል:: ከማያምን ሰው ጋር የሚደረግ ኅብረት መንፈሳዊ ሕይወትን ከመጉዳት አልፎ የጥፋት ተባባሪ ሊያደርግም ይችላል:: ይህ ሲባል ግን ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 17:15 «ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም» ያለውን ልናስብ ይገባል:: ክርስቲያኖች ከሌሎች ተለይተን ደሴት ውስጥ የምንኖር ላይሆን በዓለም እያለን በተግባራቸው ግን ላንተባበር ብርሃንና ጨው በመሆን እነርሱን ወደ ጌታ እንድናመጣቸው ተጠርተናል:: ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚለውም ይህንን ነው::

ሐዋሪያት የነበራቸው ኅብረት በማቴ. 28:18-20ና በሐዋ. 1:8 በታዘዙት መሠረት ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እስከ ምድር ዳር ድረስ ለመስበክ ሲሆን ጠላቶች በክፋት ተባብረው



በሚመጡበት ጊዜም ባላቸው አንድነትና ኅብረት ተግተው በመጸለይ ያፈርሱባቸው ነበር:: ይህ የሚያስተምረን ለወንጌል ስርጭት ኅብረት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው::

## 9.4. ትጉ ጸሎት

ሐዋሪያት ወንጌልን ለማስፋፋት ካገዙአቸው ነገሮች አንዱ የጸሎት ትጋት ነበር:: የሐዋሪያት ሥራ ይህንን በግልጽ ያስተምረናል::

በም.1:14 ጌታ ኢየሱስ ካረገ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር::

ም.በ2:5 «ከለማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር» ይላል::

በቁ.42 «በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት፤ እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር» ብሎ ሐዋሪያቱ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር አያይዘው ከሚያደርጓቸው ሥርዓቶች አንዱ ትጉ ጸሎት እንደሆነ ሉቃስ ይነግረናል::

በም.4 ጴጥሮስና ዮሐንስ ከእስራት ከተፈቱ በኋላ የመጡት ወደ ወገኖቻቸው ነበር:: እነርሱ በአንድነት እየጸለዩ ነበር:: እነ ጴጥሮስ መጥተው የሆነውን በተናገሩአቸው ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንደጸለዩ ቁ.24 ይነግረናል::

ለሐዋሪያት የወንጌል ሥራ ተግተው መጸለይ ወሳኝ ነበር። ሐዋሪያው ጳውሎስም በቆላ.4:2-4 ስለ ጸሎት ሲናገር

- ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ ቁ.2
- እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ ቁ.3
- ልናገር እንደሚገባኝ ያህል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ ቁ.3 ብሏል።

ስለዚህ ለስኬታማ የወንጌል አገልግሎት ትጉ ጸሎት አንዱ ቁልፍ ነው።

### 9.5. እንጀራን መቁረስ

ሐዋ. 2:42 «በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር» ይላል። እንጀራ መቁረስ ሁለት ትርጉም አለው። የመጀመሪያው ሰዎች በየቀኑ የሚመገቡትን የዕለት ተዕለት ምግብ አብሮ መብላት ሲሆን ሁለተኛው የጌታን እራት መካፈል ነው።
ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ወንዶች ብቻ ሲቆጠሩ አምስት ሺህ የሆኑትን በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ መገባቸው (ሉቀ. 9:12-17)። በዚህ ክፍል ቁልፍ ቃላት በቁ. 16 «ባረካቸው፤ ቆርሶም» የሚሉት ናቸው። ጌታን የተከተሉት ደቀ መዛሙርት ስለ ተራቡ ጌታ ስላዘነላቸው የሚበሉትን አዘጋጀላቸው። ይህ አብሮ መብላት መንፈስ



ቅዱስ ከወረደ በኋላም በሐዋሪያትም ሕይወት አንዱ ሥርዓት ሆኖ እናገኘዋለን።
ሁለተኛው የጌታ እራትን አብሮ መካፈል ነው። ደቀ መዛሙርቱን በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ የመገበው ጌታ በሉቃ. 22:14-23 የመሞቻው ጊዜ ሲቃረብ ደቀ መዛሙርትን ሰብስቦ ፋሲካን አብረው ሲበሉ እናያለን። ይህም የጌታ እራት የሚል ስያሜ ያገኘ ሲሆን ሐዋሪያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 11:23-34 ለቆሮንቶስ ሰዎች የጌታን እራት እንዴት መካፈል እንዳለባቸው አስተምሮአቸዋል። ይህ ሥርዓት በአዲስ ኪዳን «የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች» ተብለው ከተጠቀሱት አንዱ (ጥምቀት ሌላኛው ሲሆን) ሆኖ እናከብረዋለን። በሐዋ. 2 የምንመለከተው «እንጀራ መቁረስ» ሐዋሪያት ካደረጓቸው ነገሮች አንዱ ነበር።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደሚነግረን ከእነዚህ ቁልፎች የተነሳ

- ጌታ የሚድኑትን ዕለት በዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር (2:47)
- በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ (6:7)
- የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር (4:33)
- በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው (4:33)

- በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረም (4:34))
- በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ፤ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየበዙ ይሄዱ ነበር (9:31):: አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር፤ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር (16:5)
- በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር (5:12)
- ይናገሩበት የነበረውን ጥበብና መንፈስ ወደረኞቻቸው ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም (6:10)

ለወንጌል ስርጭት እነዚህ አምስቱ ለሐዋርያት ቁልፍ ነበሩ:: የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሌለ ወንጌልን የመመስከር ድፍረት ሊኖር አይችልም:: አንድ ልብ ከሌለ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይሠራም:: የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና አንድ ልብ ባለበት ኅብረት አለ:: ይህ ደግሞ አማኞች ተግተው እንዲጸልዩና ያላቸውንም ተካፍለው እንዲበሉ ያደርጋቸዋል:: እነዚህ አምስት ቁልፎች ሲኖሩ የወንጌል ስርጭት የተሳካ ይሆናል::



# ምዕራፍ ሁለት
# የወንጌል ተልዕኮና አውዳዊ አገልግሎት

## 1. ባሕል ምንድነው?

ባሕል ሰዎች የሚጋሩአቸውና አብረው የሚገለገሉባቸው ባሕሪያት፤ እሴቶችና ልምምዶች ናቸው:: የሚናገሩት ቋንቋ፤ የተለያዩ ሥርዓቶች ለምሳሌ የሠርግ፤ የቀብር፤ የእንግዳ አቀባበል፤ የአሰባበስ፤ የአነጋገርና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ባሕል ናቸው:: እንደ ዴቪድ ሄስልግረቭ አገላለጽ ባሕል ብዙ ነገሮችን ያካትታል፤ የቋንቋ፤ የፖለቲካ፤ የምጣኔ ሀብት፤ የማኅበረ ሰብ፤ የሃይማኖት፤ የዘር፤ የአስተሳሰብና የመሳሰሉት ልዩነቶች ሁሉ ባሕል የሚይዛቸው ነገሮች ናቸው:: ከሰዎች ጋር ለመግባባት ስናስብ እነዚህ ሁሉ እንደሚንጸባረቁ መታወቅ አለበት::

ፓውል ሂበርት የተባለ ጸሐፊ ባሕልን በሦስት ይከፍለዋል:: የቁስ (ንብረት) ባሕል (Material culture):- ሰዎች የተለያዩ ዕቃዎችንና ንብረቶችን ለራሳቸው ያበጃሉ:: ቤትን በእንጨትና በጭቃ፤ በሣር፤ በብሎኬትና በሲሚንቶ፤ ሌላም በአካባቢያቸው በተገኘው ነገር ይሠራሉ:: የበሬዎች ጋጣ ወይም የከብቶች በረት፤ የፈረስ ጋሪ፤ የአስክሬን ሣጥንና የመሳሰሉት ሁሉ የአካባቢውን ባሕል ያንጸባርቃሉ::

ስሜት የሚገለጽበት ባሕል (Expressive culture):- ሰዎች የራሳቸውን ስሜት የደስታም ሆነ የሐዘን የሚገልጹበት

- በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረም (4:34))
- በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ፤ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየበዙ ይሄዱ ነበር (9:31):: አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር፤ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር (16:5)
- በሐሪያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር (5:12)
- ይናገሩበት የነበረውን ጥበብና መንፈስ ወደረኞቻቸው ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም (6:10)

ለወንጌል ስርጭት እነዚህ አምስቱ ስሐዋርያት ቁልፍ ነበሩ:: የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሌለ ወንጌልን የመመስከር ድፍረት ሊኖር አይችልም:: አንድ ልብ ከሌለ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይሠራም:: የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና አንድ ልብ ባለበት ኅብረት አለ:: ይህ ደግሞ አማኞች ተግተው እንዲጸልዩና ያላቸውንም ተካፍለው እንዲበሉ ያደርጋቸዋል:: እነዚህ አምስት ቁልፎች ሲኖሩ የወንጌል ስርጭት የተሳካ ይሆናል::



# ምዕራፍ ሁለት
# የወንጌል ተልዕኮና አውዳዊ አገልግሎት

## 1. ባሕል ምንድነው?

ባሕል ሰዎች የሚኃሩአቸውና አብረው የሚገለገሉባቸው ባሕሪያት፤ እሴቶችና ልምምዶች ናቸው:: የሚናገሩት ቋንቋ፤ የተለያዩ ሥርዓቶች ለምሳሌ የሠርግ፤ የቀብር፤ የእንግዳ አቀባበል፤ የአለባበስ፤ የአነጋገርና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ባሕል ናቸው:: እንደ ዴቪድ ሄሰልግሬቭ አገላለጽ ባሕል ብዙ ነገሮችን ያካትታል፤ የቋንቋ፤ የፖለቲካ፤ የምጣኔ ሀብት፤ የማኅበረ ሰብ፤ የሃይማኖት፤ የዘር፤ የአስተሳሰብና የመሳሰሉት ልዩነቶች ሁሉ ባሕል የሚይዛቸው ነገሮች ናቸው:: ከሰዎች ጋር ለመግባባት ስናስብ እነዚህ ሁሉ እንደሚንጸባረቁ መታወቅ አለበት::

ፓውል ሂበርት የተባለ ጸሐፊ ባሕልን በሦስት ይከፍለዋል:: የቁስ (ንብረት) ባሕል (Material culture):- ሰዎች የተለያዩ ዕቃዎችንና ንብረቶችን ለራሳቸው ያበጃሉ:: ቤትን በእንጨትና በጭቃ፤ በሣር፤ በብሎኬትና በሲሚንቶ፤ ሌላም በአካባቢያቸው በተገኘው ነገር ይሠራሉ:: የበሬዎች ጋጣ ወይም የከብቶች በረት፤ የፈረስ ጋሪ፤ የአስከረን ሣጥንና የመሳሰሉት ሁሉ የአካባቢውን ባሕል ያንጸባርቃሉ::

ስሜት የሚገለጽበት ባሕል (Expressive culture):- ሰዎች የራሳቸውን ስሜት የደስታም ሆነ የሐዘን የሚገልጹበት

የራሳቸው መንገድ አላቸው። በተለያየ ባሕል ሰዎች የተለያየ የሠርግ ዝማሬ ወይም ሙዚቃ፤ የልቅሶን ሐዘን የሚገልጹበት መንገድ፤ በጣም የተደሰቱበት ወይም የደነገጡበት ነገር ቢኖር የሚገልጹበት የተለያየ መንገድ አላቸው። ለምሳሌ በአንድ ብሔረሰብ ባሕል ልቅሶ ሲደረስ በሐዘንተኞቹ ፊት ቆሞ ወይ አልቅሶ አሊያም «እግዚአብሔር ያጽናችሁ» ብሎ መቀመጥ የተለመደ ሲሆን ሌሎችጋ መቀመጫ አግኝቶ መቀመጥና ያ ቤተሰብ ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲያሳዩ መጠበቅ ባሕላቸው ይሆናል።

የሚከበሩ ሥርዓቶች (Rituals):- የተለያየ የኅብረተሰብ ክፍል የሚያከብሩአቸው የተለያዩ ሥርዓቶች አሉ። ልጅ ሲወለድ፤ ሠርግ ሲደገስ፤ በግርዛት ጊዜ፤ ሰው ሲሞት ወዘተ የሚያደርጓቸው ሥርዓቶች ከባሕል ባሕል ይለያያሉ። ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችም እንደየባሕሉ ይለያያሉ። በአንዱ አካባቢ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንዶችና ሴቶች በተለያየ መደዳ ሲቀመጡ በሌላ ቦታ ደግሞ ተቀላቅለው በአንድነት ይቀመጣሉ። አሜሪካውያን ልቅሶ ሲሄዱ ሙሉ ልብስ ከነክራባቱ ሲለብሱ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሴቶች ነጠላ ለብሰው (አብዛኞዎቹም አዘቅዝቀው) ወንዶች ቤተሰብ የሆኑት ጋቢ ሲለብሱ ሌሎች ደግሞ መደበኛ ልብሳቸውን ግን የተሻለውን ለብሰው ይመጣሉ።



ወንጌላዊያን በሚከተሉት አራት ምክንያቶች ስለሚሄዱበት ባሕል ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው።

*1. ለውጤታማ የወንጌል ስርጭት የአካባቢው ባሕል መታወቅ አለበት።*

በአንድ አካባቢ ያለው ኅብረተሰብ ምን ይወዳል? ምንስ ይበላል ወይም ይጠላል? የሚሉትን ነገሮች ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው። ወንጌላዊው የሚጠቀማቸውን ቃላቶች፤ አቀራረብ፤ አለባበስ፤ የአመጋገብ ሥርዓትና የመሳሰሉትን ጠንቅቆ ካላወቀ ተሳስቶ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሰዎች ወንጌልን እንዳይሰሙ በርን ሊዘጉ ይችላሉ። ሰው ቤት እንግድነት ቢጋበዝ ምን ማድረግ አለበት? በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ምን ይጠበቅበታል? ሰዎች ወንጌላዊውን እንደ ምን ያዩታል? እነዚህ መሠረታዊና መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው። ሌላው ቀርቶ ቋንቋውን ባያውቅም ሰላምታውን ብቻ ለምዶ በቋንቋቸው ሰላም ማለት ወንጌልን እንዲሰሙ በር ከፋች ነው። እዚህ ጋ በአንድ ወቅት በጨኮ (ሲዳማ) አካባቢ በተላከ የቅርብ ጓደኛዬና አብሮኝ አገልጋይ የነበረ ወንድም የተከሰተን ታሪክ መጥቀሱ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

ይህ ወጣት በመምህርነት ሙያ ተመድቦ ሲዳማ ውስጥ ጨኮ ወደሚባል ቦታ ይሄዳል። እዚያ ሲደርስ አቶ ማሞ በሰጠ የሚባሉ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አንጋፋ መሪ እንግዳ በመቀበልም የታወቁ ስለነበር እሳቸው ቤት ይመሩታል። የአቶ ማሞ ቤተሰብም አስተናግደውት 4 ኪሎ

ሜትር ያህል ከከተማ ርቃ ወደምትገኝ የገጠር ቀበሌ ወደ ተመደበበት ይሸኙታል። እዚያ ሲደርስ በመንግሥት የተመደበ የመጀመሪያ መምህር በመሆኑ ሰዎች ደስ ስላላቸው ምግብ አዘጋጅተው ይጠሩታል። መምህሩ ወደዚያ ሲሄድ የአካባቢው ሰዎች ወንድ ልጅን ይሰልባሉ፤ ደግሰውም ሊገድሉ ይችላሉ የሚል ወሬ ሰምቶ ስለነበር አእምሮው በጥርጣሬ ተሞልቷል። በዚህ ጊዜ ምግቡ ተዘጋጅቶ ክብ ሠርተው ከተቀመጡ በኋላ አንዱ በሲዳምኛ «ዲእፊኒ» አለ። ይህም «ተዘጋጅቷል» እንደ ማለት ነው። ምግቡ ስለተዘጋጀ ሽማግሌዎች የሚጸልይ ሰው እንዲመድቡና እሳባቸውን እንዲሰበስቡ ለማስታወስ ነበር። በዚህ ጊዜ መምህሩ በውስጡ «በእውነት አታፍኑኝም» ይልና ለጸሎት ባጎነበሱበት ሹልክ ብሎ ወጥቶ በኃይለኛ ዝናብ ውስጥ ወደ አቶ ማሞ ቤት ሮጦ ይደርሳል። ምን ሆንክ? ሲባል «ጌታ ከሞት አስመለጠኝ» ይላል። ሁኔታው ሲጣራ ለእርሱ ክብር የተደገሰ ድግስና ሰዎች አቀባበል ሊያደርጉ የተሰበሰቡበት ያውም ጸልየው የሚቀበሉና የሚበሉ ክርስቲያኖች ያሉበት እንጂ ሌላ ምንም ችግር አልነበረም። በሚቀጥለው ቀን ሌላ ሽማግሌ ወስዶ ከሰዎች ጋር አገናኝቶት እስከ ዛሬ ድረስ እንደ አገሬው ሰው ቋንቋቸውን ለምዶ ባሕሉን ባሕሉ አድርጎ እዚያው አግብቶና ወልዶ በጩኮ ከተማ ይኖራል። ቋንቋን አለማወቅ እንዲህ ዓይነት ስሕተት ውስጥም ይከታል።



እዚያው ጩኮ ከተማ ውስጥ የሚኖር ክርስቲያን ወዳጄ በማረፉ ምክንያት ልቅሶ ለመድረስ ሄጄ ነበር። በሲዳማ ባሕል ልቅሶ የደረሰ ሰው መጀመሪያ ተቀምጦ፤ አጎንብሶ፤ የሚያለቅሰው አልቅሶ፤ የማያለቅሰውም ኃዘኑን ገልጸ ከዚያ በኋላ እንግዳ ተቀባይ ሰው ማድረግ የሚገባውን ያሳያል። በወላይታ ባሕል ደግሞ ልቅሶ የደረሰ ሰው ወደሚመለከተው ሰው ፊት ደርሶ የሚያለቅሰው አልቅሶ፤ ክርስቲያኑም «እግዚአብሔር ያጽናችሁ» ብሎ መቀመጥ አለበት። ባሕሉን የማያውቅ ሰው ከሆነ ደርሶ ፊቱን አሳይቶ መቀመጥ ይችላል። በዚህ ሁለት የተለያየ ባሕል መኻል ነው እንግዲህ እኔ ልቅሶውን የሄድኩት። ልቅሶ ቤት ድንኳን ውስጥ ገብቼ የሟችን ባለቤት አፈልጋለሁ። ለካስ ስሕተት ነበር። ሴቶቹ በተቀመጡበት ሄጄ እፊታቸው ቆሜ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ብዬ ተመልሼ ተቀመጥኩኝ። ያደረኩት የወላይታን ባሕል እንጂ የሲዳማን ባሕል የልቅሶ ሥርዓት አልነበረም። ባሕልን አለማወቅ እንደዚህ ላለ ስሕተትም ይዳርጋል።

*2. ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው በሚቀበሉበት ጊዜ ኅብረተሰቡ ሊሰጣቸው የሚችለውን ምላሽ በማወቅ ተገቢውን ስልት ለመጠቀም ያስችላል።* ሰዎች ሁሉ የራሳቸው የሆነ ማኅበራዊ ግንኙነት አላቸው። ቤተ ሰቦች፤ ዘመዶች፤ ጓደኞች፤ የሥራ ባልደረቦች ሁሉ በተለያየ መንገድ አንዱ ከሌላው ጋር የተሳሰሩ ናቸው። አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ በሚድንበት ጊዜ ከተጠቀሉና ከመሳሰሉት ሰዎች ምን ዓይነት ምላሽ ያገኛል? በአንዳንድ

ቦታዎች ሊገለል ይችላል፤ በሌሎች ቦታዎች ብዙም ትኩረት የማይሰጠው ነገር ሊሆን ይችላል፤ በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ባያወግዙትም ግትኝነታቸውን ሊያሳሉ ይችላሉ:: ወንጌላዊው ባሕሉን ጠንቅቆ ካወቀ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ይችላል::

*3. በምንሰብከው ወንጌልና በኅብረተሰቡ ባሕል መካከል ያለውን ክፍተት በመሙላትና የተለያየ ባሕል ላለው የዓለም ኅብረተሰብም እንደየባሕሉ ወንጌልን ለመመስከር ያስችላል::*

መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረው ባሕልና አሁን ያለው ባሕል በጣም የተለያየ ነው:: ይህንን ክፍተት በመሙላት ወንጌልን በተገቢው መንገድ ለመመስከር መለኮታዊ መገለጥ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በአውዱ መሠረት መረዳትና የምንመሰክርላቸውን ሰዎች ባሕልና አኗኗር ጠንቅቆ ማወቅ ምስክርነቱን ሰዎች እንዲረዱትና ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል::

*እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላሉ አገልግሎቶች ኅብረተሰቡ የሚጠቀሟቸውን ቃላቶችና አባባሎች ለመጠቀም ያስችላል::* መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቋንቋ ሲተረጎም የተጻፈበትን ዋናውን መልእክት ሳያዛንፍ ሰዎች በሚረዱት መንገድ እንዲተረጉም ይረዳል:: ለዚህ ደግሞ የኅብረተሰቡን ቋንቋና የአነጋገር ዘይቤ ማወቅ የግድ ይላል::



## 2. ኢየሱስ ክርስቶስና ባሕል

መላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ባሉበት ባሕል እንደሚገናኛቸው ይመሰክራል:: ከአዳምና ሔዋን ጋር በኤዴን ገነት አብሮ ተጉዟል:: አብርሃምን፤ ሙሴን፤ ዳዊትንና እስራኤላውያንን በነበሩበት በዕብራይስጥ ባሕል መሠረት አነጋግሯቸዋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የተለያዩ ሰዎች ከተለያየ አመለካከትና ባሕላዊ አስተሳሰብ ጋር ወደ እርሱ ይመጡ ነበር:: ፈሪሳውያን፤ ሰዱቃውያንና የሄሮድስ ወገን ሦስቱ ዋነኛ የሆኑ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና አስተምህሮ የተፈታተኑ ወገኖች ነበሩ::

በአዲስ ኪዳን ዘመን ትልቁን ተጽእኖ ሲፈጥር የነበረውም የፈሪሳውያን ወገን ነው:: የዚህ ወገን አባላት በቃልና በጽሑፍ የተገለጡ ሕጎችን በመጠበቅና ከክፉ ሁሉ በመራቅ ራሳቸውን በንጽሕና ለመጠበቅ የሚሞክሩ ነበሩ:: አስተምህሮአቸው የተመሠረተው በብሉይ ኪዳን ላይ ነው:: በመላእክትና በመንፈስ መኖር፤ ነፍስ ለዘላለም እንደምትኖርና በአካል ትንሣኤ ያምናሉ:: ኢየሱስ ክርስቶስ በግብዝነታቸውና በአስመሳይነታቸው ወቅሷቸዋል:: «ወዮላችሁ» እያለም አስጠንቅቋቸዋል:: «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን . . . ወዮላችሁ» (ማቴ.23:13-39):: ኢየሱስ ክርስቶስ የተቸው ማንነታቸውን ሳይሆን ትምህርታቸውንና ልምምዳቸውን ነበር:: ባሕላቸውንና

ሥርዓታቸውን ለመጠበቅ ሲሉ የእግዚአብሔርን ሕግ ስለሚተላለፉም ወቀሳቸው (ማቴ.15:3፤ ማር. 7:9):: ፈሪሳውያን የጽዋውና የወጭቱ (የኩባያውና የሳህኑ) ውስጥ ቆሽሾ እያለ ላዩን ለማጽዳት የሚጥሩ ነበሩ:: በሌላም አባባል ለታይታ የሚሠሩ ነበሩ:: እነዚህ ኢየሱስ «ለሌላው ይሰብካሉ፤ ለራሳቸው ግን አያደርጉትም» ያላቸው ወገኖች ናቸው::

በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ሌሎች ወገኖች ደግሞ ሰዱቃውያን ናቸው:: ሰዱቃውያን ስማቸውን ያገኙት በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ካህናት ከነበሩት ከሳዶቅ ልጆች ነው:: የሳዶቅ ልጆች በእስራኤል ምርኮ ዘመን ካህናት ነበሩ (2ዜና 31:10፤ ሕዝ. 40:46፤ 44:15፤48:11):: በክርስቶስ ዘመንም ይህ ስም እንደ ማኅበረግ አገልግሏቸዋል:: ከፈሪሳውያን በቁጥር አነስተኞች ቢሆኑም በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን የፖለቲካውን ሥልጣን የያዙ ሲሆን በአይሁድ ማኅበራዊ ኑሮ የመሪነትን ሥፍራ የያዙ ነበሩ::

ሰዱቃውያን በአስተምህሮአቸው ለሙሴ መጻሕፍት (ለሕግ) ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ሲሆን ከታሪክና ከነቢያት መጻሕፍት ይልቅ የበለጠ ሥልጣን እንዳላቸውም ያምናሉ:: ፈሪሳውያን የሚያምኑአቸውንና ትኩረት ሰጥተው የሚያከብሩአቸውን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን አፈ ታሪክ ሰዱቃውያን አይቀበሉም:: በመላእክትና በመንፈስ መኖር አያምኑም፤ የሙታን ትንሣኤ እንዳለም አይቀበሉም:: ለዚህ ነው



ሐዋሪያው ጳውሎስ ከፈሪሳውያን ጋር ሆነው ሲይዙት በመጡ ጊዜ ስለ ሙታን ትንሣኤ በመናገር በመካከላቸው መከፋፈል እንዲፈጠር ያደረገው (ሐዋ. 23:6-8):: የኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ላይ አገልግሎቱ ሊጠናቀቅ በቀረበ ጊዜ በኢየሩሳሌም ሊያጠምዱት ፈልገው ስለ ሙታን ትንሣኤ በጠየቁት ጊዜ ዘጸአት 3:6ን በመጥቀስ መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁም ሲል ወቀሳቸው (ማቴ.22:23-33)::

የሄሮድስ ወገን የተባሉት በሁለት ወንጌላት ማለትም በማቴዎስና በማርቆስ የተጠቀሱ ሲሆን በሁለት በተለያዩ ጊዜያት ከፈሪሳውያን ጋር በመሆን ኢየሱስን በመቃወም ቀርበዋል (ማር. 3:6፤ 12:13):: የሄሮድስ ወገኖች እንደ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ከእምነት ክፍል ሳይሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው:: ትኩረታቸውም ለሄሮድስ ዘር በወገንተኝነት መቆም ነው:: ማቴዎስና ማርቆስ እንደሚነግሩን ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩት በገሊላ ከፈሪሳውያን ጋር በመሆን ኢየሱስን ለማጥፋት ሲሞክሩ ነው (ማቴ.12:14፤ ማር. 3:6):: በኢየሱስ የመከራ ሳምንትም እንደገና ከፈሪሳውያን ጋር በመሆን በንግግር ለማጥመድ ለቄሣር ግብር መስጠት መፈቀድ አለመፈቀዱን ጠይቀው ነበር (ማቴ.22:17፤ ማር.12፤13)::

ከላይ የተጠቀሱት ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያጋጠሙት የተለያየ ባሕልና ወግ ያላቸው ወገኖች ሁሉ

ሲገናኙ ኢየሱስ ባሕላቸውን እንዳለ አልተቀበላቸውም፤ ሁሉንም አልተቃወመም። ነገር ግን ባሕላቸውና ወጋቸው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የማይጻረር ሆኖ ሲገኝ ሰዎችን ከነማንነታቸው የተቀበለ ሲሆን ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ጋር የሚጋጭ ሆኖ ሲገኝ ግን ይቃወማቸው ነበር። ይህንንም በሦስት መንገድ ልናስቀምጠው እንችላለን።

ኢየሱስ በአይሁድ ባሕል ተወልዶ ያደገ ስለሆነ ባሕሉን ተቀብሎታል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፤ ራሱ አምላክ የሆነው ሰው ሆኖ ወደ ምድር መጥቶ በአይሁድ ማኅረሰብ መካከል በጊዜና በቦታ ተወስኖ ኖረ። ዮሐ. 1:14 «ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ» ይላል። ዓለምን ለማዳን የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆነ። ሰው እንደ መሆኑ አይሁዳዊ ሆኖ ተወለደ። ገላ. 4:4-5 «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ። እንደ ልጆቹ እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» ይላል። የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ ከወላጆቹ ጋር የፋሲካ በዓል ወደሚደረግበት ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ (ሉቃ. 2:41-42)። በቃና ዘገሊላ ለሠርግ በታደመበት የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ ውኃን ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ (ዮሐ.2)። ፈሪሳዊና የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነ ኒቆዲሞስ በሌሊት በመጣ ጊዜ ከነባሕሉና ከነማንነቱ ተቀበለው (ዮሐ. 3:1-2)። በገሊላ እንደተወለደ ልጅ



አለባበሱና አነጋገሩ የአይሁድ ነበር፤ በየሰንበቱም ወደ ምኩራብ ይሄድ ነበር (ሉቃ. 4:16)። እንደ አይሁዳዊ ልጅ የሙሴን ትዕዛዛት ተከትሎአቸዋል (ማቴ. 5:17-20)። የቤተ መቅደስን ግብር ከፍሏል (ማቴ. 17:27)። በዚህ መሠረት ባሕሉን ተቀብሏል ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ግን ባሕሉን ንቆት አልፏል። የአይሁድን ባሕልና ወግ በመጣስ ኃጢአተኛ የሆነችውን ሰማርያዊት ሴት ለማዳን (እርሱ አይሁዳዊ እርሷ ሰማርያዊት፤ እርሱ ወንድ እርሷ ሴት፤ እርሱ ጻድቅ እርሷ ኃጢአተኛ)፤ በእርሷ አማካይነትም የሰማርያን ሕዝብ ለማዳን በያዕቆብ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ አነጋገራት (ዮሐ. 4)። ፈሪሳውያን ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር በመሆን ለቄሣር ግብር መክፈል መፈቀድ አለመፈቀዱን በጠየቁት ጊዜ «የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ» (ማቴ.22:21) አላቸው። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቀራጩ ማቴዎስ ቤት እራት በሚበሉበት ጊዜ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጥተው ከእነርሱ ጋር በሉ። ፈሪሳውያን የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት «መምህራችሁ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር አብሮ ስለ ምን ይበላል?» ብለው በጠየቁት ጊዜ «ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» አላቸው (ማቴ. 9:9-13)። ሌሎች ሁሉ በሚጾሙበት ወቅት እርሱና ደቀ መዛሙርቱ አልጾሙም ነበር (ማር. 2:18-19)። የአይሁድ ልማድ የሆነውን ከምግብ

በፊት እጅ መታጠብን ባለማድረጉ ተደንቀዋል (ሉቃ. 11:38)፤ ለምጻሞችን ነክቷል፤ የሞተችውን ልጅ እጅ ይዞ አስነስቷል፤ ከሰማርያዊት ሴት ጋር ተነጋግሯል፡፡ እነዚህ ሁሉ በአይሁዳውያን ባሕል ንጹሕ ያልሆነ የሚባሉና የማይነኩ ነበሩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባሕልን የናቀበት ምክንያት እያንዳንዱ ሰው ሊቀበለው የሚገባ ከባሕላቸው የተሻለ እውነት ስላለ ያንን እንዲቀበሉት ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜም ባሕሉን ሲቃወምና ሲያፈርስ እንመለከታለን፡፡ ባሕልን ንቆ መተው ለዎችን ሊያስገርማቸው ይችላል፤ መቃወምና ማፍረስ ግን ያናድዳል፤ ያበሳጫል፤ ተቃውሞም ያስነሳል፡፡ ለምሳሌ ከቤተ መቅደስ ውስጥ ነጋዴዎችን በጅራፍ አባረራቸው (ማር. 11:15)፤ ደቀ መዛሙርቱ በሰንበት ዕለት ፍሬ ቀጥፈው እንዲበሉ ፈቀደላቸው (ሉቃ. 6:1)፤ እርሱ ራሱ በሰንበት ቀን የታመሙትን ፈውሷል፤እንዲያውም ብዙዎችን የፈወሰው ከሌሎች ቀናት ይልቅ በሰንበት ቀን ነበር (ሉቃ. 6:7)፤ አመንዝራ ሴት እንድትወገር አልፈቀደም (ዮሐ. 8:11)፤ ኃጢአተኛ ሴት በፀጉሯ እግሩን ሲታብስ አልከለከላትም (ሉቃ. 7:38)፡፡ ፈሪሳውያንን ግብዞች ብሎአቸዋል (ማቴ. 23:13)፡፡ በኮራዚን፤ በቤተ ሳይዳና በኢየሩሳሌም የፍርድን ነገር ተናግሯል (ሉቃ. 10:13፤ 21:24)፡፡ ፍቺን፤ መሐላንና በሙሴ ሕግ የተጻፈውን በቀል ሁሉ ተቃውሟል (ማቴ. 5:31-32፤ 34-- 40)፡፡ በዚህ ሁሉ ኢየሱስ ለምን ባሕሉን



አፈረሰው? ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት ባሕሎች ሕዝቡን አንቀው የያዙ በመሆናቸው ነጻ መውጣት ስላለባቸው ነው፡፡

እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕል ጋር በተያያዘ አንዳንዶቹን ተቀብሏቸዋል፤ አንዳንዶቹን ግን ንቋቸዋል፤ አንዳንዶቹን ደግሞ ተቃውሟቸዋል፤ አፍርሷቸዋልም፡፡ እነዚህ ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዋነኛ ነገሮች አልነበሩም፡፡ ለእርሱ ዋነኛ ነገር አዲሱን ባሕል የወንጌሉን እውነት ማስተዋወቅ ነበር፡፡

### 3. ወንጌልና ባሕል

ባሕል የተለያዩ ሰዎች የሚያስቧቸው፤ የሚያደርጓቸውና የሚሰማቸው ስሜት ከሆነ ወንጌል የቱጋ ይመደባል? ወንጌል በራሱ የአንድ ባሕል አካል አይደለም? መልሱ አዎን ከሆነ ክርስቲያን ለመሆን የትኛውን ባሕል እንቀበላለን?

በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ብዙ አሕዛብ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲጨመሩ ትልቅ ጥያቄ በሐዋሪያት መካከል ተነሳ፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ይሁዲነት ተመልሰው የአይሁድን ባሕል መገረዝንና የመሳሰሉትን መተግበር አለባቸው? ካልሆነ የትኛውን የብሉይ ኪዳን አስተምህሮ ተቀብለው የትኛውን መተው አለባቸው?

የመጀመሪያው ትልቁ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ (ሐዋ. 15) የተሰበሰበው ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ነበር፡፡ አሕዛብ

ክርስቲያን ለመሆን አይሁዳውያን መሆን አለባቸው? ይህ የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ያታገለ መሠረታዊ ጥያቄ ነበር። የመጨረሻ መልሳቸው ግን አይደለም የሚል ነበር። ምንም እንኳን ወንጌል ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ የተሰበከው በአይሁድ አውድ የነበረና አሁንም በዚያው አውድ መነገር ቢኖርበትም የምሥራቹ ቃል የእግዚአብሔር መለኮታዊ መልእክት ስለሆነ በዚያ ባሕል የተወሰነ አይደለም። ስለዚህ አሕዛብ አምነው ሲድኑ ክርስቲያን ለመሆን አይሁዳዊ መሆን የለባቸውም።

እንደዚህ ከሆነ ወንጌል ምንድነው? እንዴትስ ከሰው ባሕል ጋር ይገናኛል? ወንጌል እግዚአብሔር በታሪክና በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰው በመሆን ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ መገለጥ ነው። ይህም መገለጥ በቅዱስ ቃሉ ተጽፎ ይገኛል። ይህ በቃሉ የተጻፈው የእግዚአብሔር መገለጥ በሰው ባሕል ውስጥ ገብቶ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያገናኝበት መንገድ የተወሳሰበ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በልጁ በኩል ከሰው ጋር ያደረገው ግንኙነት ወንጌልንም በተለያየ ባሕል ውስጥ ገብቶ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ምክንያት ሆኖናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ሆኖ እያለ አምላክነቱን ሳያጣ ፍጹም ሰው እንደሆነ ሁሉ ወንጌልም መለኮታዊ መልእክቱን ሳይቀይር በተለያየ ባሕል ውስጥ ገብቶ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ይችላል።



የወንጌልን መልእክት ይዘን ወደ ተለያየ ባሕል ስንሄድ ለሚያጋጥሙን ችግሮች ፓውል ሂበርት ሦስት መሠረታዊ መመሪያዎችን አስቀምጦልናል።

የመጀመሪያው ወንጌል ከሰው ባሕል ሁሉ መለየት አለበት። ወንጌል የሰው ታሪክና ዜና ሳይሆን የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። ወንጌል ለማንም ባሕል ለብቻው የተሰጠ ስላይደለ ለሰው ሁሉ እንደየባሕሉ መረዳት አለበት። አንዳንድ ሚስዮናውያንና ወንጌላውያን የምሥራቹን ቃል ከመጡበት ባሕል ጋር ያያይዙታል። ይህ አመለካከታቸው ወንጌልን የሚሰብኩበትን ኅብረተሰብ ባሕል እንዲክዱና ወንጌልን ሰምተው ባመኑት ላይ የራሳቸውን ባሕል እንዲቀበሉ እንዲጫኑ አድርጎአቸዋል። ከዚህም የተነሳ ወንጌልን የሚሰሙ ሰዎች ወንጌል እንግዳ ባሕልና በተለይም የምዕራባውያን አስተምህሮ እንደሆነ እንዲያምኑ አድርጎአቸዋል። ይህም ሰዎች የኢየሱስን አዳኝነት ሳይጠሉ ነገር ግን በወንጌል አምኖ መዳን ማለት የራሳቸውን ባሕል ጥለው እንግዳ ባሕል መቀበል እንደሆነ አድርገው ስለተቀበሉ የወንጌልን እውነት እንዲጠሉ አድርጎአቸዋል።

ሁለተኛው ወንጌል ለየትኛውም ባሕል ለብቻው የተሰጠ አይደለም፤ ስለሆነም በእያንዳንዱ ባሕል አውድ መገለጥ አለበት። ሰዎች የወንጌልን መልእክት ከራሳቸው ቋንቋ፤ ከሚግባቡበት ምልክትና ሥርዓት ውጭ ሊረዱ አይችሉም። ጌታን ያላወቁ ሰዎች ወንጌልን እንዲሰሙና እንዲያምኑ

ከተፈለገ ወንጌል በባሕላቸው ውስጥ አልፎ መነገር አለበት፡፡ ከሰዎች ጋር ለመግባባት የሚደረገው ሂደትም በሰዎች በራሳቸው ባሕል አውድ ውስጥ እንዲሁም መረዳት በሚችሉበት መንገድ መሆን አለበት፡፡

ሦስተኛው ወንጌል ሁሉንም ባሕል እንዲለወጡ ጥሪ ያደርጋል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ ሕይወት የሰውን ኃጢአተኝነት እንደሚኮንነው ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌልም ባሕሎችን ሁሉ በጽድቅ ለመኮነን የቆመ ነው፡፡ ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው፡፡ ይህ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው ደግሞ ለራሱ የሚመቸውን ባሕል ፈጥሯል፡፡ በጌታ አምነው የዳኑ ሁሉም በዚህ በተፈጠረው ባሕል ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ ባሕሉም ከዚህ የጸዳ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ጦርነት፤ አንዱ ሌላውን መጨቆን፤ አንዱ በሌላው ላይ የሚፈጽመው ግፍና በደል፤ የጣዖት አምልኮና የመሳሰሉት ሁሉ ሰው የፈጠራቸው ክፉ ነገሮች ናቸው፡፡ ወንጌል ግለሰቦችን እንዲለወጡ እንደሚጠራ ሁሉ እነዚህን መጥፎ ተግባራትንም እንዲለወጡ ይጠራል፡፡

ወንጌል የሰው ልጅ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ይኖር ዘንድ መንገድ ያሳያል፡፡ ሕይወታችንና ባሕላችንም በዚህ መንገድ እንዲቀረጽ ይፈልጋል፡፡ የወንጌል መልእክት ይህንን የማያውጅና በባሕል ተጽዕኖ ሥር የሚወድቅ ከሆነ ግን እውነተኛ ወንጌል መሆኑ ይቀራል፡፡ ስለዚህ ባሕልና ወንጌል



አንድ ላይ ሲመጡ ሁል ጊዜም ባሕል በወንጌል እውነት ሲገመገምና ሲፈተሽ ይገባል፡፡

### 4. የሌላውን ባሕል መልመድ

ባሕል በሁለት መንገድ ይለመዳል፡፡ አንዱ በመወለድ ሲሆን ሁለተኛው በመማር ነው፡፡ አንድ ልጅ ከተወለደ በኋላ እዚያው ሲያድግ ያለ አስተማሪ የሚናገረውና የሚያደርገው ሁሉ የቤተሰቡንና የዚያን ኅብረተሰብ ባህል ይሆናል፡፡ ይህ በመወለድ የሚለምደውና የሚያገኘው ዕውቀት ኢን-ካልቸረሽን (Enculturation) ይባላል፡፡ ሌላው ሰዎች ከአንድ ባሕል ወደ ሌላ ባሕል ሲሄዱ ያንን የራሳቸው ያልሆነን ባሕል የሚለማመዱበት ሂደት ነው፡፡ በተለይ ልጆች አዕምሮአቸው ብሩህ ስለሆነና ከሌሎች ልጆች ጋር ስለሚውሉ ወዲያው የዚያ ማህበረሰብ ባሕል አካል ይሆናሉ፡፡ ይህም በመማር የሚገኝ ዕውቀት አ-ካልቸረሽን (Acculturation) ይባላል፡፡ በዚህ ቦታ የሌላውን ባሕል መልመድ ሲባል አንድ ሰው ከተወለደበት፤ ካደገበትና ከለመደው ባሕል ወጥቶ ወደ ሌላ እንግዳ ባሕል ሲገባ የሚለምደው ሁኔታ ነው፡፡ የወንጌል መልእክተኞች ለአገልግሎት ወደ ሌላ ኅብረተሰብና ባሕል ሲሄዱ ይህ ዕውቀት እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ክፍል መዳሰሱ አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ ሰው የሌላው ሰው ወይም ማህበረሰብ ባሕልና ዕውቀት እንዲኖረው ከዚያ ማህበረሰብ ጋር የቀረበ ግንኙት

ሲኖረው ይገባል:: ቀላል ከሆነው ሰላምታ በመጀመር ለመገበያየት በሚደረገው ንግግር፣ በለቅሶ፣ በሠርግና በበዓል ጊዜያት ስለሚደረጉ ሥርዓቶችና ቋንቋዎች ማወቅ ባሕሉን እንዲያውቅ ያደርጉታል:: ይህ ደግሞ ፍላጎትን፣ ጊዜን መስጠትንና ከዚያው ኅብረተሰብ ጋር መላመድን ይጠይቃል:: ይህ ሲሆን እንግዳው ሰው የማህበረሰቡን አመለካከት፣ አስተሳሰብና አኗኗር ማወቅ ይጀምራል:: ማህበረሰቡም እንግዳውን ሰው ማወቅ ይጀምራሉ::

አንድ መዝገበ ቃላት እንዳስቀመጠው ወደ ሌላ ባሕል የሄደ እንግዳ ሰው ማወቅና ማለፍ የሚገባቸው ሰባት ደረጃዎች አሉ::

**4.1.** ቋንቋን መማር፡- የሌላውን ባሕል ለማወቅ የመጀመሪያ ደረጃ ቋንቋን ማወቅ ወይም መማር ነው:: በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከናወኑ አንዳንድ ነገሮች በማየትና አስተውሎ በመመልከት ሲታወቁ ይችላሉ፡ ትርጉማቸው የሚታወቀው ግን ያ ኅብረተሰብ የሚናገረው ቋንቋ ሲታወቅ ነው:: በሌላው ባሕል ውስጥ ወንጌልን ለማገልገል የሚፈልግ የወንጌል አገልጋይ ቋንቋቸውን መማርና ማወቅ ካልቻለ ከኅብረተሰቡና ጥልቅ ከሆነ ባሕላቸውና አኗኗራቸው ተገልሎ ይኖራል::

**4.2.** የገንዘብ አጠቃቀማቸውን ማወቅ፡- በሌላ ባሕል ውስጥ የሚያገለግል የወንጌል አገልጋይ የኅብረተሰቡን የግብይት፣ የንብረት አያያዝ፣ የብድር፣ የልውውጥና የመሳሰሉትን



ከገንዘብና ከንብረት ጋር የተያያዙ ነገሮችን ማወቅ ለውጤታማ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ኑሮውን ለመግፋትም ወሳኝ ነው:: ይህ ደግሞ የሚታወቀው በኅብረተሰቡ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ በቀጥታ በመሳተፍና የሚያደርጓቸውንም ነገሮች ለምንና እንዴት እንደሚያደርጉ አስተውሎ በመከታተል ነው::

**4.3.** ማኅበራዊ ግንኙነቶች፡- ሰዎች ሁሉ እንደየባሕላቸው እርስ በርስ የሚገናኙበት የጋብቻ፣ የዕድር፣ የቤተ ዘመድ፣ የልቅሶ፣ የዳኝነትና የመሳሰሉት ግንኙነት አላቸው:: አንዱ ለሌላው ያለው ክብርና ቦታ፣ የመሪነትና የሥልጣን ደረጃ፣ በወንዶችና በሴቶች፣ በሽማግሌዎችና በወጣቶች መካከል ያለው ቦታና የመሳሰሉት ሁሉ የወንጌል አገልጋይ ሊያውቅ የሚገባቸው ለአገልግሎቱ ውጤታማነት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው::

**4.4.** የችግር አፈታት ባሕል፡- በሌላ ባሕል ውስጥ ችግሮች እንዴት እንደሚከሰቱና ኅብረተሰቡ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ ማወቅ ሌላው አስፈላጊ ነገር ነው:: የኢትዮጵያን ባሕል ከሌላው ዓለም ልዩ ከሚያደርጋቸው ነገሮች አንዱ የሽምግልና ዳኝነት ነው:: ብዙ ብሔሮች የራሳቸው የሆነ የሽምግልና አስተዳደር አላቸው:: እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ አሠራር፣ ሕግና ደንብ አላቸው:: አንዳንዶቹ ደግሞ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ይተዳደራሉ:: ለምሳሌ ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ቃል

በወንድሞች፤ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና በአዋቂ ሰዎች፤ ሙስሊሞች በሸርዓ ሕግ፤ ሌሎች ይህንን የማይፈልጉት ደግሞ በአገሪቱ ሕግ መሠረት በፍርድ ቤት ሊሆን ይችላል። ችግሮች እንዴት እንደሚከሰቱና ኅብረተሰቡ እንዴት እንደሚፈታቸው አገልጋዩ ማወቅ አለበት።

**4.5. የልጆች አስተዳደግ፡-** አንድ አገልጋይ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ሌላ ባሕል ሲሄድ ከኅብረተሰቡ ጋር ቀድመው የሚላመዱት ልጆች ናቸው። ልጆች ወዲያው ከልጆች ጋር መጫወትና መግባባት ይጀምራሉ። ለእነርሱ የሃይማኖት፤ የብሔርና የማንነት ልዩነት ጥያቄ ውስጥ አይገባም። አብረው መጫወትና መግባባት እስከቻሉ ድረስ ሌሎች ልጆች እንግዳውን ልጅ በደስታ ይቀበሉታል። ልጆች እንደ አዋቂዎቹ ማን ነው? ለምን መጣ? የየትኛው ሃይማኖት ተከታይ ነው? የሚሉ ነገሮችን አያውቁም። ይህ ደግሞ ለተለያዩ ነገሮች ይጠቅማል። አንደኛው ልጆች ባሕሉን ቶሎ ስለሚለምዱ ብቸኛ አይሆኑም። ሁለተኛው ለወላጆቻቸው የባህሉን አንዳንድ ስርዓቶች ያስለምዱአቸዋል። ሦስተኛው በጣም አስፈላጊ መረጃዎችን በልጆች አማካይነት ማግኘት ይችላሉ። ከዚህም ባሻገር አገልጋዩ ልጆቹን በቤት ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሲመራቸው በኅብረተሰቡ መካከል ደግሞ እንዴት ማሳደግ እንደሚችል ከኅብረተሰቡ ይማራል ማለት ነው።



**4.6. የኅብረተሰቡን አስተሳሰብና አመለካከት፡-** የወንጌል አገልጋዮች ወንጌልን ሲመሰክሩ ሰዎች ሦስት ዓይነት ምላሽ አላቸው፤ አንዳንዶቹ ይቀበላሉ፤ ሌሎቹ «ሌላ ጊዜ እናያለን» ይላሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ይቃወማሉ። ለምላሻቸው ያደጉበት፤ የኖሩበትና የተቀረጹበት አስተሳሰብና አመለካከት ትልቅ ተጽዕኖ ያደርጋል። ሰዎች ሁሉ ያደጉበት ባሕል ልክ ነው የሚሉአቸውን ልክ ነው ብለው ልክ አይደለም የሚሉአቸውን ደግሞ ልክ አይደለም ብለው ለዘመናት ስለኖሩ ያንን አስተሳሰብ መቀየር ከባድ ነው። የወንጌል መልእክት ሲነገር ነፍስን የሚያድን ቃል እንደሆነ ሳይሆን ሌላ ባሕል አድርገው ስለሚያስቡ እንቅፋት ይሆናል። ከዚህም ሌላ የወንጌል መልእክተኛው ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ ስለሚኖር የሚወዱአቸውንና የሚጠሉአቸውን ነገሮች ለይቶ በማወቅ መልእክቱን በአስተሳሰባቸው አውድ ለማስተላለፍ ያስችለዋል።

**4.7. የወንጌል መልእክት ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ፡-** የወንጌል መልእክተኛው የሚያገለግልበትን ባሕል እንዲያውቅ የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት የወንጌልን መልእክት በአውዱ መሠረት ለማስተላለፍ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሁሉ ካወቀ በኋላ አገልጋዩ ራሱን መጠየቅ ያለበት ጥያቄ «እንዴት የወንጌልን መልእክት ማስተላለፍ እችላለሁ?» የሚለውን ነው። ተግባራዊነቱን ካላወቀ ባሕሉን ማወቅ የእዕምሮ እውቀት ብቻ ይሆናል።

ለተለማሪ-በት ዋነኛ ተልዕኮም የሚፈይደው ምንም ነገር አይኖረውም።

### 5. በባሕል ተጽዕኖ መጨነቅ

የወንጌል መልእክተኛው ወንጌልን የራሱ ባልሆነ እንግዳ ባሕል ውስጥ ለማገልገል ሲሄድ ራሱን በሁለት ባሕሎች መካከል ያገኛል። አንዱ ያደገበትና የኖረበት የራሱ ባሕል ሲሆን ሁለተኛው የሄደበት አካባቢ እንግዳ (አዲስ) ባሕል ነው። መልእክተኛው የሚያገለግለውን መልእክት ማወቅ አንድ ነገር ሲሆን የሚያገለግልበትን ባሕል ማወቅ ሌላው ነገር ነው። ወንጌላውያን የወንጌልን መልእክት ይዘው ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዘው ይሆናል። መልእክቶቻቸውንም ጠንቅቀው ያውቁ ይሆናል። ተሸኝተው ሲሄዱ በትልቅ ድፍረትና መተማመን ሄደው ይሆናል። ወደሚሄዱበት ቦታ ደርሰው ከእንግዳ ባሕል ጋር ፊት ለፊት ሲጋጠሙ ግን መደንገጥና መሸበር (Culture Shock) ይከሰታል።

አገልጋዩ ተሸኝቶ ሲሄድ ዲል ያለ ድግስ ተደግሶ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እሱና ቤተሰቡ የክብር እንግዳ ሆነው ለሚሸኙአቸው ሰዎች እንደ ትልቅ ዕድለኞች ተቆጥረው በደስታ ይሸኛሉ። ጓደኞች፣ ዘመዶች፣ አብረው ያገለገሉ ሰዎች ሁሉ በጸሎትና በቡራኬ ሲሸኙ እነርሱም ሲሄዱ በትልቅ ተስፋ፣ ጉጉትና ወኔ ይሰማራሉ። ወደሚሄዱበት ቦታ ሲደርሱም የሞቀ አቀባበል ይደረግላቸዋል። ከደረሱ



በኋላ በነጋታው ቋንቋቸው ስለማይታወቅ በምልክት መነጋገር ይጀመራል። ምግቡ የተለመደ አይደለም። የሕዝቡም ባሕርይ እንግዳ ነው። በዚህ ጊዜ ያ ሁሉ ደስታና ስሜት ይጠፋና ድንጋጤና ፍርሃት ይሆናል። አንዳንዶቹ የመሄድ ፍላጎት እንጂ ሄደው ምን እንደሚያደርጉም በውል የማያውቁ ወንጌላውያን አሉ። አንዲት ወጣት ሴት ሚሲዮናዊት ሆና ከአሜሪካ ወደ አፍሪካ ለመሄድ የሸኙት ፕሮግራም ከተደረገና ከተጸለየላት በኋላ ሄዳ ምን እንደምታደርግ ስጠይቃት በአጭር ቃል «አላውቅም፣ ሄጄ አያለሁ» አለችኝ። ነገር ግን ደስታዋ ወደር አልነበረውም። እንደዚህ ዓይነቶቹ ከደረሱ በኋላ ሁሉ ነገር እንግዳ ሲሆንባቸው መረበሽና መደንገጥ አንዳንዶቹም ወደ ቤት ለመመለስ ይወስናሉ።

አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት በሌላ ባሕል ለማገልገል የሚሄዱ አገልጋዮች አራት ደረጃዎችን ያልፋሉ። የመጀመሪያው ደረጃ የደስታ፣ የጉጉት፣ አጭርና የጫጉላ ጊዜ ነው። ሁሉም ነገር የተሳካበት ጊዜ ነው። ሁለተኛው ደረጃ ሁሉም ነገር እንደ ተጠበቀውና ተስፋ እንደ ተደረገው ላይሆን እንግዳ ሆኖ መረበሽና መደንገጥ የሚሆንበት ጊዜ ነው። ሦስተኛው ደረጃ ባሕሉን የሚለማመድበት፣ በትንሹም ቢሆን በቋንቋቸው መግባባት የሚሞክሩበት፣ ምግቡንና ሕዝቡን መልመድ የሚጀምሩበትና ተረጋግተው መኖር የሚችሉበት ጊዜ ነው። አራተኛው ደረጃ ከባሕሉ ጋር ቤተኛ የሚሆኑበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ሁሉንም ነገር ለምደው

የኖሩበትንና ያደጉበትን ባሕል ረስተው የሚኖሩበትን ባሕል ባሕላቸው፤ ሕዝቡን ሕዝባቸው አድርገው የሚኖሩበት ጊዜ ነው። በተለይ ልጆቹ ከወላጆቹ ባሕል ይልቅ የእንግዳው አካባቢ ባሕል ባሕላቸው ሆኖ የነበሩበትን ጨርሶ የሚረሱበት ጊዜ ነው።

የወንጌል አገልጋዮች ወደ ሌላ አካባቢ ባሕል ሲሄዱ እንዲረበሹና እንዲደነግጡ የሚያደርጉ አምስት አበይት ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፦

የመጀመሪያው ምክንያት ከኅብረተሰቡ ጋር ለመግባባት ዘለመቻል ነው። የወንጌል አገልጋይ ከኖረበት ባሕል ወጥቶ ሲሄድ ቋንቋው፤ የሰው ባሕርይ፤ ምግቡ፤ አስተሳሰቡ ሁሉ እንግዳ በሚሆነበት ጊዜ መልመድና ከሰዎች ጋር መግባባት ካቃተው ፍርሃት፤ ድንጋጤና መረበሽ ይሆንበታል።

ሁለተኛው ምክንያት የዕለት ተዕለት ኑሮ ሁኔታ መለወጡ ነው። አገልጋዩ በኖረበት ባሕል ሚስት ትገበያያለች፤ ምግብ ታበስላለች፤ ልብስ ታጥባለች፤ የባል ኃላፊነት አገልግሎትና ውጫዊ ግንኙነት ብቻ ይሆናል። በእንግዳው ባሕል ግን ሚስት ብቻዋን ገበያ መሄድ ስለማትችል ከእርስዋ ጋር ገበያ ሄዶ መሸማመት፤ ልብስ አጥቦ መርዳት፤ በልጆች አያያዝም ዘመድ አዝማድ ተንከባክቦ የለመደው በእንግዳው አካባቢ ዘመድና የለመዱት ጎረቤት ስለሌለ የልጆችን ኃላፊነት መውሰድ፤ በኖረበት አካባቢ በቀላሉ የሚከናወኑ ነገሮች



ባንክ፤ ሱቅና የመሳሰሉት በአቅራቢያ ከሌሉ እነዚህንና የመሳሰሉትን ከተለመደው ኑሮ ወጣ ያሉ ነገሮች ለማከናወን ረጅም ጊዜ ስለሚፈጅ ፍርሃት፤ ድንጋጤና መረበሽ፤ አልፎም ተስፋ መቁረጥ ይመጣል።

ሦስተኛው ምክንያት ከግንኙነት አንጻር የተደረገ ለውጥ ነው። ሰው ሁሉ በኑሮው የሚገናኛቸው ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ፤ ወዳጆች፤ ጎረቤቶች፤ ጓደኞች፤ የሱቅ ደንበኞች፤ በችግር ጊዜ ፈጥኖ የሚደርስ ዕድርና የመሳሰሉት ሁሉ አሁን የሉም። እነዚህ ሁሉ የሰው ማንነት የሚገለጥባቸውና የሚተማመኑባቸው ግንኙነቶች ሲቀሩ ነገሮች ይለወጣሉ። ልጆች የራሳቸው ችግር ስላለባቸው መጥተው ይጮሃሉ፤ ሚስት በራስዋ የባልን ዕርዳታ ትፈልጋለች። ባል ደግሞ የራሱ ችግር ስላለበት የሌላውን ዕርዳታ ይፈልጋል። ችግሮቹ የተለመዱ ስላልሆኑ ቀድሞ በችግርና በብቸኝነት ጊዜ የሚረዱ ሰዎችና ሁኔታዎች ባለመኖራቸው ድንጋጤና መረበሽ ይሆናል።

አራተኛው ምክንያት አለመረዳት ነው። ሰው ከሌላ ሰው ጋር ለመኖር ባሕሉን፤ አኗኗሩንና እየተከናወኑ ያሉትን ነገሮች በትክክል መረዳት ያስፈልጋል። የወንጌል አገልጋዩ ከኅብረተሰቡ ምን ይጠብቃል? ኅብረተሰቡስ ከእርሱ ምን ይጠብቃል? ይህንን በትክክል ካልተረዳ የራሱ ዕውቀት ብቻውን ትርጉም አይኖረውም። ለምሳሌ ያህል በአንዳንድ ባሕል በአመልካች ጣት መጠቆም ነውር ሊሆን ይችላል።

በሌላው ባሕል ደግሞ አትኩሮ ማየት የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል። የሌላውን ባሕል በትክክል አለመረዳት ትችትና ሰዎች ከአገልጋዩ እንዲርቁ ስለሚያደርጉ ድንጋጤንና መረበሽን ይፈጥራል።

**አምስተኛው የአገልጋዩ ስሜትና ድምዳሜ የተሳሳተ ሲሆን** ነው። የሚሰማው ሙዚቃ፣ የሚበላው ምግብ፣ የሰው አለባበስ፣ የኅብረተሰቡ እንቅስቃሴ ሁሉ እንግዳ ሲሆን በቀላሉ መቆጣትና መናደድ ይጀምራል። ይህ ባሕሉን በትክክል አለመረዳት የተለየ ስሜት ይፈጥርና ባሕሉ መጥፎ እንደሆነ በማሰብ ድምዳሜ ላይ ይደርሳል። በዚህ መጥፎ ባሕል ውስጥ መኖር ደግሞ የማይቻል እንደሆነ ይታሰብና መረበሽና መደንገጥ ይጀመራል።

እነዚህ ሁኔታዎች ሲደራረቡ የመጡበትን አካባቢና ቤተሰብ መናፈቅ ይመጣል። ከዚህ የተነሳ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱን ራሳቸውን ያጠፉ ሚስዮናውያን አሉ። አንዳንዶቹ ለአገልግሎት ራሳቸውን ለእግዚአብሔርና ለቤተ ክርስቲያን ሰጥተው ከሄዱበት ጊዜ አስቀድመው እንዲመለሱ ሚስቶቻቸው ወይም ልጆቻቸው ምክንያት ይሆናሉ። ስለዚህ ከባሕላቸው ወጥተው ወደ ሌላ ባሕል የሚሄዱ የወንጌል መልእክተኞች የእግዚአብሔርን ቃልና የወንጌሉን መልእክት ይዘት ብቻ ሳይሆን የሚሄዱበትንም ባሕል ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው።



አንዳንድ የወንጌል አገልጋዮች በሌላ ባሕል ብዙ ዓመት ካገለገሉ በኋላ ወደ ተወለዱበት አካባቢና ባሕል ሲመለሱ የተወለዱበትና ያደጉበት ባሕልና ቋንቋ ራሱ እንግዳ ይሆንባቸውና ይቸገራሉ። በተለይ ልጆች ብዙ ዓመት ቆይተው ከተመለሱ ለመልመድ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። አንድ ወንጌላዊ ከወላይታ ወደ ትግራይ ሄዶ ለአሥር ዓመታት ያህል ቆይቶ ትምህርት ለመማር ሲመለስ ልጆቹ ጨርሶ የትግራይ ተወላጅ መስለው ነበር የመጡት። የወላይታን ባሕልና ቋንቋ ለመልመድም በጣም ተቸግረዋል። ስለዚህ ቀድሞ የኖሩበትና ያደጉበት ባሕል ራሱ ከዓመታት በኋላ ሲመለሱ መረበሽንና ድንጋጤን ሊፈጥር እንደሚችል (Reverse Culture Shock) የወንጌል መልእክተኞች ማወቅ አለባቸው።

### 6. በባሕል ተጽዕኖ መጨነቅን ማስቀረት

በባሕል ተጽዕኖ መረበሽና መደንገጥ መቅረት የሚችል ነገር ነው። ለዚህ ደግሞ መሠረቱ የሌላውን ባሕል በመልካም አመለካከት መመልከትና ማድነቅ ነው። አገልጋዮች አመለካከታቸው ጥሩ ካልሆነና አዲሱን ባህል ማድነቅ ካልቻሉ ከኅብረተሰቡ ጋር ሳይዋሃዱ እንግዳ ሆነው ይኖራሉ። መልካም አመለካከት ካለ ግን ቋንቋቸውንና ባሕላቸውን ለመማርና ለመልመድ ፍላጎቱ ይኖራል። ሰዎችን፣ አመጋገባቸውንና የኑሮ ዘይቤአቸውን ሊወዱላቸው ይችላሉ ነገር ግን እንዴት እንደሚኖሩ ካልተማሩና ካላወቁ

አገልግሎታቸው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። እነርሱን መውደድና እንደ እነርሱ መኖር የተለያዩ ነገሮች ናቸውና።

አንድ ሚስዮናዊ ወደ ሕንድ አገር ሄዶ ለሁለት ዓመታት ቋንቋቸውን ማወቅ አልቻለም። ስለዚህ የላከው የሚስዮን ድርጅት ወደ አገሩ እንዲመለስ ደብዳቤ ላከለት። በዚህ ጊዜ ሚስዮናዊው ደብዳቤውን ይዞ በኃዘን ወደ መሪዎች መጥቶ ስንብት ጠየቃቸው፤ መሪዎቹ ደብዳቤውን ካነበቡ በኋላ ቆይ ቁጭ በል ብለው እንዲህ የሚል ደብዳቤ ለላከው ድርጅት ጻፉ። «ይህ ሚስዮናዊ ከእኛ ጋር በኖረባቸው ሁለት ዓመታት የአፋችንን ቋንቋ መናገር አለመቻሉ እውነት ነው። ነገር ግን የልባችንን ቋንቋ ስለሚናገር እንዲሄድብን አንፈልግም» አሉ። ማወቅና መኖር የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አገልጋዩ በባሕላቸው ሲኖር ፍርሃትና ድንጋጤውም ይጠፋል።

ሌላው ግለኝነትንና ብሔርተኝነትን ማስወገድ ጠቃሚ ዘዴ ነው። የወንጌል መልእክተኛው «የእኔ ይሻላል» (ግለኝነት)፤ «የእኛ ይሻላል» (ብሔርተኝነት) የሚል ጠባብ አመለካከት ካለው የሄደበትን ባሕልና ቋንቋ ሊለምድ አይችልም። ይህንን ማስወገድ በሌላ ባሕል ተረጋግቶ ለማገልገል ይረዳል።



ዕውቁ የስነ-ሰብ ጥናት ምሁር ፓውል ሂበርት በሌላ ባሕል ተጽዕኖ መረበሽንና መደናገጥን ማስቀረት የሚቻልባቸውን አራት መንገዶች አገልጋዮች ሁሉ እንዲጠቀሙ ይመክራል።

የመጀመሪያው አገልጋዮች የጭንቀቶቻቸውን መንስዔ ማወቅ አለባቸው። ሰው እንደ መሆናቸው ሁኔታዎች ሲለወጡ በአገልጋዮችም ዘንድ መጨነቅ ያለ ነገር ነው። ፍርሃትና ድንጋጤ የጤነኛ ሰው ስሜት መገለጫ ናቸው። የጭንቀቱ መንስዔ ካልታወቀ ግን መፍትሔ ለማግኘት ስለሚቸግር አደጋ ነው። መንስዔው ከታወቀ አገልጋዩ ከአቅሙ በላይ የሆነበትን ጉዳይ እንኳን ለሌላ ሰው ወይም ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አካፍሎ መፍትሔ ማግኘት ስለሚችል መጀመሪያ የጭንቀቱን መንስዔ ማወቅ ቀዳሚ ጉዳይ ነው።

ሁለተኛው ባሕላቸውን ማወቅ ነው። አገልጋዮች በሚያገለግሉበት ባህል ውስጥ ገብተው በመማርና በመኖር ጭንቀቶቻቸውን ማስወገድ ይችላሉ።

ሦስተኛው መተማመንን መፍጠር ነው። የኅብረተሰቡን ባሕል ማወቅና ማድነቅ በቂ አይደለም። አገልጋዮች የሚያገለግሉባቸውን ባህልና ቋንቋ ካወቁ በኋላም እንግዳ ሆነው ሊኖሩ ይችላሉ። የሚቀረው መተማመንን መፍጠር ነው። የወንጌል መልእክት ይዘን እንደ ጠላት እያዩን እንዴት ሊተማመኑን ይችላሉ? የሚል አሳብ ሊነሳ ይችላል፤ ሰዎች የወንጌል አገልጋዮች ክፉ ነገር እንደሌለባቸውና የማይጎዱ መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው። የሰላም ሰዎች መሆናቸው

ከታወቀ መተማመን ይፈጠራል:: ወደ ባሕላቸው የሄድነው እኛ ነን እንጂ እነርሱ አይደሉም፤ ስለዚህ በተቻለ መጠን ጥሩ ግንኙነትን በማዳበር መተማመንን መፍጠር የአገልጋዮች ኃላፊነት ነው::

መተማመንን ለመፍጠር ሌላው ጠቃሚው ነገር ግልጽ መሆን ነው:: መተማመን የሁለት ወገኖች ይሁንታን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው:: እነርሱ ልባቸውን ለእኛ እንዲከፍቱልን ከፈለግን መጀመሪያ እኛ ልባችንን ለእነርሱ መክፈት አለብን:: እንደ አገልጋዮች መተማመንን ለመፍጠር የማይለዋወጥ ባሕርይ እንዲኖረን ያስፈልጋል:: ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆንን ካወቁ ሊተማመኑብን አይከብዳቸውም:: ለዚህም በግል ከሰዎች ጋሮ የምንነጋገረውና በአደባባይ ከሌሎች ጋር የምንነጋገረው አንድ ዓይነት መሆን አለበት::

ሌላው መተማመንን በየጊዜው በምናደርጋቸው ግንኙነቶች ማሳደግ አለብን:: መተማመን ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ነገር ስለሆነ በጥንቃቄ ካልተያዘና በዕለት ተዕለት ግንኙነቶች ካልዳበረ ሊሰበር ይችላል:: ያ ደግሞ ለወንጌል አገልግሎት እንቅፋት ይሆናል::

አራተኛው ጭንቀትን መጋፈጥ ነው:: ጭንቀት ከክርስቲያኖች ዋና ጠላት ከሰይጣንና ከሁኔታዎች መነሻ በማድረግ አገልግሎት እንዳይሳካ የሚመጣ ውጊያ ነው:: ይህንን ውጊያ ለማሸነፍ ደግሞ በድፍረት መጋፈጥ ያስፈልጋል:: ለመጋፈጥ መሣሪያ የሚሆኑት 1) ብርቱ የተቃውሞ ጸሎት 2) መንስዔ የሆነውን ነገር ለይቶ ማወቅና ማስወገድ 3) ያስጨነቀንን ነገር ለሌሎች ማካፈል 4) የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ማስታወስ 5) የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ማሰላሰል ጠቃሚ ስልቶች ናቸው::



ለማጠቃለል ወንጌል የማይለወጥና የማይሻር መለኮታዊ መልእክት ነው:: መልእክቱ ደግሞ በየትኛውም ባሕልና ቋንቋ ሊቀየርና ሊመቻመች አይችልም:: ይሁን እንጂ ይህ የማይለወጥ መለኮታዊ መልእክት ለሰዎች የሚቀርበው በሚለዋወጠው የሰው ባሕልና ቋንቋ ውስጥ አልፎ ነው:: ባሕል ደግሞ የራሱ ኃይል አለው:: ሰዎች ላመኑባቸውና ለኖሩባቸው ነገሮች ዋጋ ይከፍላሉ:: ስለዚህ ወንጌልና ባሕል አንድ ላይ በሚመጡበት ጊዜ የትኛውም ባሕል በማይለወጠውና ባለ ሥልጣን በሆነው በእግዚአብሔር ቃል መፈተሽ አለበት:: ባሕሉ የእግዚአብሔርን ቃል የማይጻረር ከሆነ ልንቀበለውና ልናስተናግደው፤ የሚጻረር ከሆነ ደግሞ ጥበብና ጥንቃቄ በተሞላበት አገልግሎት ወንጌል እንዲለውጠው ማድረግ የወንጌል ምስክርነትን ውጤታማ ያደርጋል::

### 7. አውዳዊነት (Contextualization)

አውዳዊነት ማለት በዚህ ጽሑፍ መሠረት የማይለወጠውን የወንጌልን መልእክት ሳይሸቃቅጡና ሳያመቻምቹ

በሚለዋወጠው በለው ባሕል ውስጥ መናገር ወይም ማስተላለፍ ማለት ነው። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ቀጥታ የሚነሳው ጥያቄ ወንጌልን እንዴት አውዳዊ እናደርጋለን? የሚል ነው። አንድ የወንጌል መልእክተኛ ወደ ሌላ አካባቢ ሲሄድ የሚሄደው ባሕልና ሃይማኖት ወደ ሌለበት ባዶ ቦታ አይደለም። የሚሄደው ኅብረተሰቡ የራሱ የሆነና ትክክል ነው ብሎ የተቀበለው ኑሮ፣ የራሱ ያደረገው ሃይማኖት፣የአመጋገብ፣ የአነጋገር፣ የአለባበስ፣ የደስታ፣ የሐዘን ወዘተ ባሕል ይኖረዋል። አንድ ሰው ወንጌል ተመስክሮለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል እነዚህን ባሕሎች ምን ማድረግ አለበት? አዲስ ወንጌላዊ አዲስ የምትተከለውን ቤተ ክርስቲያን ከእነዚህ ባሕሎች አንጻር እንዴት ያያል? ወንጌል ዘላለማዊ መልእክቱን ሳይቀይር በአዲሱ ባህል ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? ሰዎች የተለማመዱትን ጎጂ ባህል በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ውሳኔ የሚሰጠው ማነው? እነዚህ ጥያቄዎች አንድ ወንጌላዊ ወንጌልን ይዞ ወደ ሌላ ባሕል ሲሄድ ሊታሰቡ የሚገቡ ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው።

ፖውል ሂበርት አውዳዊነትን በሦስት መንገድ ያስቀምጠዋል።

1. አሮጌውን ባሕል መጣል፡ አውዳዊነትን አለመቀበል

እንዳንድ ወንጌላውያን ወንጌልን ይዘው ወደ ሌላ ባህል ሲሄዱ ኅብረተሰቡ የተለማመዳቸውን እንደ አለባበስ፣ ጌጣ ጌጥ፣ የሠርግና የልቅሶ ስርዓቶች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎችንና የመሳሰሉትን ከባዕድ አምልኮና ከአሮጌው ሃይማኖታቸው ጋር በማገናኘት ሰዎች ክርስትናን ሲቀበሉ ለአማኝ የማይገባ ነው በማለት እንዲጥሉ ያደርጉአቸዋል። ከዚህም የተነሳ ሰዎች ከወንጌሉ ጋር የወንጌላዊውን ባሕልም እንደ ወንጌል ክፍል በመውሰድ ይለማመዱታል። ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ከተለመዱ ምግቦች አንዱ ጥሬ ሥጋ መብላት ነው። ምዕራባውያን ከጤና ጋር በማያያዝ ጥሬ ሥጋ የኮሶ ትል ስለሚያስከትል አማኞች እንዳይበሉ ይመክሩአቸዋል። ያ አስተምህሮ ለብዙ ዓመታት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተከብሮ ጥሬ ሥጋ የሚበሉት ከአገልግሎትና ከጌታ እራት ሁሉ እንዲታገዱ የሚደረግበት ሁኔታ ነበር። ይህ አንግዲህ አሮጌውን ባሕል መጣልና አውዳዊነትን አለመቀበል ነው። አንዳንዶች ደግሞ ይህንን የሚያደርጉት ሥር ከሰደደ የብሔርተኝነት ስሜት ወይም አመለካከት የተነሳ ነው። ባለማወቅ የራሳቸውን ባሕል ከወንጌል ጋር ይቀላቅሉና የሌላውን ባሕል መጥፎ በማለት ይኮንናሉ። ይህም አመለካከት በወንጌል አገልግሎት ላይ የተለያዩ ችግሮችን ይፈጥራል።

የመጀመሪያው ሰዎችን ባሕል አልባ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። የራሳቸውን ባሕል መጥፎ እንደሆነ ይቆጥሩና ይተውታል፣ ሌላ የራሴ ነው የሚሉት ባህል ደግሞ አልያዙም። ስለዚህም ከሁለት የወጣና ማንነቱን ያጣ ባህል አልባ ይሆናሉ።

ሁለተኛው ችግር ሰዎች በአንድ በኩል ባህላቸውን መጣል አይፈልጉም፤ በሌላ በኩል ደግሞ አገልጋዮች ያስተማሩአቸውን ትምህርት መተግበር ይፈልጋሉ:: ስለዚህም አማራጭ አድርገው የሚወስዱት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሳያውቁ ባህላቸውን በድብቅ መለማመድን ነው:: ይህ ደግሞ እውነተኛ መለወጥ ሳይኖር ተደብቀው እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል::

ሦስተኛው ሰዎች ክርስትናን ሌላው ሃይማኖትና ባሕላቸውን የሚያጠፋ አዲስ ትምህርት አድርገው እንዲያዩ ስለሚያደርግ ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኛቸው አድርጎ መቀበል የሕይወት ለውጥ ሳይሆን የሃይማኖትና የባሕል ለውጥ አድርገው እንዲያዩት ያደርጋል:: ይህ ደግሞ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ አምነናል ቢሉም ሳይለወጡ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል::

2. አሮጌውን ባሕል መቀበል: ሳይፈትሹ አውዳዊ ማድረግ

ይኸኛው ደግሞ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ በሚያምኑበት ጊዜ አሮጌ ባሕላቸውን ምናልባት ጥቂት ነገሮችን ብቻ ጥለው ወይም ለውጠው በአዲሱ መንገድ እንዲጓዙ ማድረግ ነው:: የዚህ አመለካከት ያላቸው ወንጌላውያን ለሌሎች ሰዎችና ለባሕላቸው ትልቅ አክብሮት ያላቸው ሲሆን ከፍ ያለ ቦታም ይሰጣሉ:: በእነርሱ አባባል አሮጌውን ባሕል መጣል ሰዎች ወንጌልን እንዳይሰሙ እንቅፋትን ማኖር ነው::



እንደ መጀመሪያው ይኸኛውም የራሱ ችግር አለበት:: የመጀመሪያው ችግር በባሕል ውስጥ ያሉ አንዳንድ ነገሮች ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑና እግዚአብሔር የማይከብርባቸው ሊኖሩ እንደሚችሉ አይገነዘቡም:: ሰዎች የሚለማመዱአቸው ነገሮች በእግዚአብሔር ቃል ካልተፈተሹ በግልም ሆነ በጋራ ኃጢአት በሚሆኑ ነገሮች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ:: ወንጌል ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰብንም በወንጌል አምነው እንዲለወጡ ይጋብዛል:: አውዳውነት ማለት ሰዎች የወንጌልን እውነት በሚረዱበት መንገድ መግለጽ ሲሆን ግለሰቦችም ሆነ ማኅበረሰብ ከክፉ ሥራቸው እንዲመለሱ ይጠራል:: ስለዚህ ባሕልን ሁሉ እንዳለ መቀበል ተገቢ አይደለም::

ሁለተኛው ችግር ሰዎች ሕይወታቸው ሳይለወጥ ሁለት ዓይነት ኑሮ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል:: አንደኛው በወንጌል ማመን ሲሆን ሁለተኛው ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ በቀድሞ ባሕላቸው መመላለስ ነው:: ይህ መቀላቀል ደግሞ መወገድ የሚገባው ነገር ሳይወገድ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል::

3. አሮጌውን ባሕል መግጠም: ፈትሾ አውዳዊ ማድረግ

አሮጌውን ባሕል መጣልም ሆነ ሳይፈትሹ መቀበል ለወንጌል ሥራ ትክክለኛ አካሄድ ካልሆኑ ወንጌላዊያንም ሆነ ጌታን የተቀበሉ ሰዎች አሮጌውን ባሕል ምን ማድረግ አለባቸው? ሦስተኛው አካሄድ አሮጌውን ባሕል በእግዚአብሔር ቃል እውነት ፈትኖና ፈትሾ መቀበል ነው::

መጀመሪያ ባሕሎቹ ራሳቸው ያሉበት ሁኔታ ከተጠና በኋላ በቃሉ እውነት መገምገም ያስፈልጋል። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ሀ. ግለሰብም ሆነ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ሁሉንም ዓይነት የማኅበረሰቡን ሕይወት እንዲፈትሽ መፍቀድ ነው። ይህ በተለይ በሠርግ ሥርዓት፤ በቀብር ሥርዓት፤ በወንዶች ግርዛት፤ በልጆች መወለድ ጊዜና በመሳሰሉት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አንድ ሊረሳ የማይገባ ነገር ቢኖር ወንጌላችን ሰዎችን ወደ አዲስ እምነትና የተለወጠ ኑሮ እንደሚጠራ ነው።

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ወንጌላዊያን የሰዎችን ባሕል ሳይተቹና ሳይኮንኑ መጋበዝና ወደ ጌታ ሲመጡ የሚያጋጥማቸውን ችግር በቃሉ መሠረት ፈትሸው መወሰን አለባቸው። ለምሳሌ በሠርግ ወይም በልቅሶ የሚደረጉ ሥርዓቶች እንደ አዘፋፈንና አለቃቀስ ዓይነቶች፤ የአመጋገብና የእንግዳ አቀባበል ሥርዓቶች ከቃሉ አንጻር እንዴት ይታያሉ? የዚህ ዋና ዓላማ ልንተቻቸው ወይም ልንኮንናቸው ሳይሆን ባሕሉን ተረድተን ክርስትያኖች ቃሉን ከሚጻረሩ ልምምዶች እንዴት ዘወር ማለት እንደሚችሉ ለማስተማር ነው።

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም ወንጌላዊ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን ለውይይት በማቅረብ ሰዎች በቃሉ እንዲፈትሹና ራሳቸው እንዲወስኑ



ማድረግ ነው። ሰዎች ዘመናቸውን ትክክል ነው ብለው የኖሩባቸውን ባሕልና አኗኗር አታድርጉ፤ ተው፤ በሚል መመሪያ ልናስተው አንችልም። ራሳቸው ከቃሉ አይተው ሲረዱት ራሳቸው ይወስናሉ።

መ. አራተኛው ደረጃ ምዕመናን ራሳቸው አሮጌውን ባሕላቸውን በቃሉ ገምግመው መሆን የሚገባውን እንዲወስኑ ማድረግ ነው። እንዲህ ከሆነ የወንጌል መልእክት ሳይለወጥና ሰዎችም ባሕላቸው ከቃሉ እውነት ሳያሸሻቸው ወንጌልን መስበክ ይቻላል። ይህ አውዳዊነት ይባላል።

## 8. ተግባቦት

ተግባቦት ማለት አንዱ ሌላውን መረዳት ማለት ነው። ዶ/ር ዶናልድ ስሚዝ በአጭሩ ተግባቦት ማለት መረዳዳትን መፍጠር ማለት ነው ይላል። ራሽ ማይሮን የተባለ ጸሐፊ ደግሞ ተግባቦት አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ከሌላው ጋር ለመግባባት የሚያደርገው ሂደት ነው። መረዳዳት ካልተፈጠረ ሰዎች አልተግባቡም። ስለዚህም አንዳንድ ሰዎች ስለ ደካማ መግባባት የሚያጉረመርሙ ከሆነ ችግሩ ውይይቱ ወይም ንግግሩ ሳይሆን መረዳዳት አለመቻሉ ነው ይላል። ተግባቦት የሚከተሉትን ነገሮች ያካትታል።

ሀ. ተግባቦት ያሳትፋል።

ሰዎች ለመግባባት በሚሞክሩበት ጊዜ አንዱ የተናገረውን ሌላው በመጠየቅ፤ አሳቡን በመደገፍ ወይም በመቃወም፤ መረዳት አለመረዳቱን በምልክት ቋንቋ እንኳን ቢሆን

ካልገለጸው በትክክል መረዳቱን እርግጠኛ ልንሆን አንችልም። ስለዚህ አድማጭ ተናጋሪው ሲናገር በውይይቱ መሳተፍ አለበት።

ለ. ተግባቦት ሂደት ነው።

አንዱ ከሌላው ጋር የሚያደርገው ውይይት ወይም ንግግር ትንሽም ቢሆን ጊዜ መፍጀቱ አይቀርም። ምክንያቱም የተባለው ነገር ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ከላይ እንደተጠቀሰው ሁለቱም ወገኖች ስለሚሳተፉበት ነው። ይህ ሂደት አራት ነገሮችን ያካትታል።

1. ተናጋሪ፡- በአንድ የተግባቦት ሂደት ውስጥ መጀመሪያ ውይይቱን ወይም ንግግሩን የሚጀምረው ተናጋሪው ነው። የምናገርበትን ቋንቋና የምናገረውን መልእክት አድማጩ በምረዳበት ሁኔታ በአዕምሮው አስቦ ይናገራል። በዚህ ወቅት ወሳኝ የሚሆነው የሚናገርበት ቋንቋ ቢሆንም ለማስረዳት የሚጠቀማቸው ምልክቶችም ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። ምክንያቱም የተናጋሪውና የአድማጭ ባሕል የተለያየ ከሆነና ተናጋሪው ሳያውቅ ሊያስቀይም የሚችል ምልክት ቢጠቀም ግንኙነታቸውን ያበላሻል።

2. አድማጭ፡- ተናጋሪው በሚናገርበት ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ አድማጭ መስማት አለበት። ከሰማ በኋላ የሰማውን መልእክት በተረዳበት መንገድ ይተረጉማል፤ ምላሽም ይሰጣል። የሁለቱ ቋንቋ የተለያየ ከሆነ መግባባት አይችሉም፤ ቋንቋቸው አንድ ሆኖ አነጋገራቸው የተለያየ



ከሆነም አስቸጋሪ ይሆናል። አንዳንድ የዚህ ባለ ሙያ ሰዎች እንደሚሉት የአለመግባባት ዋነኛው ምክንያት የማዳመጥ ችግር ነው። ይህ ደግሞ በብዙ ጥናት የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ አድማጭ ለተናጋሪው ምላሽ ከመስጠቱ ወይም የሰማውን ነገር ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መልእክቱን በትክክል መረዳቱን እርግጠኛ መሆን አለበት። ስለዚህ በትክክል ማዳመጥና ተናጋሪው ምን እንደምል ማወቅ ወሳኝ ነው።

3. መልእክት፡- ተናጋሪው ሲናገር ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ይኖራል። ይህ መልእክት በተናጋሪውና በአድማጭ እኩል መተርጎምና መረዳት አለበት። ቋንቋው አንድ ሆኖ፤ ተናጋሪው ያለውን አድማጭ በደንብ ከሰማ በኋላም አድማጭ ተናጋሪው ከሚለው በተለየ መንገድ ከተረዳው አልተግባቡም ማለት ነው። አንድ ጊዜ ወንድሜ ከብቶችን ሲጠብቅ ለራሱ ልጫወት ስለፈለገ አንድ ቦታ እየሰበሰባቸው በትክክል ሣር እንዳይበሉ ያደርጋቸዋል። በዚህ ድርጊቱ የተናደደችው እናቴ «በል አንግዲህ ገመድ ውሰድና እሰራቸው» አለችው። ትንሽ ቆይቶ ሮጦ ወደ ቤት መጣና እማዬ ገመዱ ዬት አለ? ይላታል። ገመድ ምን ያደርግልሃል? ስትለው «ሰብስበህ እሰራቸው አላልሽኝም ወይ?» ብሎ እርፍ። ሁለቱ የተነጋገሩት ግልጽ የሆነ ነገር ነው ግን መልእክቱ በወንድሜ አዕምሮ በተለየ መንገድ ነው የተተረጎመው። ይህ ምናልባት ገጠር ለሚኖሩት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። በከተማ ለሚኖሩት ሌላ ምሳሌ ልስጥ!

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ልጅ እናቱን ካልፈለጥኩ ሲል የሰማች እናት ብዙ ተረብሻ፤ ብዙ ነገር ከሆነ በኋላ ሲጣራ ልጁ የሚለው ገንዘብ ካልተቀበልኩ ማለቱ እንጂ እናቱን ለመጉዳት አለማሰቡን በኋላ መረዳታቸውን «ቤቶች» በተሰኘ ው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ አይቻለሁ:: የዚህ ችግር ምክንያቱ ልጁ የሚለውን እናት የተረጎመችው በሌላ መንገድ ስለሆነ ነው:: ስለዚህ የተነገረና የተሰማ መልእክት ሁሉ ተግባቦትን ፈጥሯል ማለት አንችልም::

4. የማስተሳለፊያ መንገድ፡- ሁለቱ ሰዎች ወይም ቡድኖች በሚነጋገሩበት ጊዜ የሚግባቡባቸው መንገዶች አሉ:: በንግግር፤ በጽሑፍ፤ በምልክትና በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል:: ዶ/ር ዶናልድ አሥራ ሁለት መልእክትን የማስተሳለፊያ መንገዶች እንዳሉ ጽፏል:: እነርሱም፡-

4.1. ንግግር፡- ሰዎች በቃል ንግግር እርስ በርስ ይግባባሉ::

4.2. ጽሑፍ፡- ሰዎች መልእክቶቻቸውን በመጻጻፍ ያስተሳልፋሉ፤ ይግባባሉም::

4.3. ቁጥር፡- አንድ የተጻፈ ቁጥር የራሱ መልእክት አለው:: ለምሳሌ 7 በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ቁጥር እንደሆነ ይወሰዳል:: መኪና መንገድ ላይ 200 የሚል በድንጋይ የተጻፈ ቁጥር ብናይ ወይ 200 ኪሎ ሜትር ተጉዘናል፤ አሊያም 200 ኪሎ ሜትር ይቀራል ማለት ነው::

4.4. ሥዕል፡- አንድ የተሳለ ሥዕል የራሱ የሚያስተላልፈው መልእክት አለው:: አንድ ቤት ውስጥ የተሰጠፉ ሥዕሎች ቤተሰቡ ምን ሃይማኖት እንደሚከተል በቀላሉ ይነግሩናል::



4.5. ድምፅ፡- አንድ የምንሰማው ድምፅ በጆሮአችን ሲገባ የምንረዳው ነገር አለ:: መኪና ጥሩንባ ቢነፋ ዞር በል ይሳል፤ ጩኸት ቢሰማ ችግር አለ ማለት ነው:: እልልታ ቢሰማ ሠርግ፤ አምልኮ ወይም የመሳሰለ ጥሩ ነገር አለ ማለት ነው::

4.6. የሰውነት እንቅስቃሴ፡- አንድ ተናጋሪ ሲናገር ሌላኛው የሚያሳየው የሰውነት እንቅስቃሴ ጥሩም መጥፎም የሆነ መልእክት ያስተላልፋል:: አድማጭ የሚቁነጠነጥ ከሆነ ሰልችቶታል ማለት ነው፤ የበለጠ እየቀረበ ከመጣ ደግሞ ነገሩ ጥሞታል ማለት ነው::

4.7. ቀለሞች፡- ቀለሞች የራሳቸው መልእክት አላቸው:: የአገራችን ባንዲራ ቀለማት፤ የትራፊክ መብራት፤ የምንለብሳቸው ልብሶች ሁሉ መልእክት ያስተላልፋሉ:: ጥቁር ልብስ የለበሰች ሴት ብናይ ምን ሆንሽ? እንላለን:: ልብሷ መልእክት አስተላልፏልና:: ያለ ወትሮው ዝንጥ ብሎ ለብሶ የወጣውን ሰው ስናይ «ዛሬ ደግሞ ምን አገኘህ?» እንላለን::

4.8. ዕቃዎች፡- አንዳንድ ዕቃዎች መልእክት አላቸው:: አንድ ሳጤ ማግባቱን ያሳወቀ ዘመዱ ወይም ጓደኛው የጣቱን ቀለበት ሲያይ የኩርፊያቸው መነሻ ይሆናል፤ ሳትጠራኝ አግብተህ ይባላልና:: ሲያነብ መነጽር የሚያደርግ ሰው ዓይኑ ያለ መነጽር ለማንበብ እንደሚቸገር ይነግረናል::

**4.9.** መነካካት፡- ሁለት ሰዎች የሚያደርጉት ንኪኪ መልእክት ያስተላልፋል:: መተቃቀፍ መነፋፈቅን፤ እጅ ጨብጦ መነቅነቅ ጎበዝ ነህ ማለትን ይገልጻሉ::

**4.10.** የሰዓት አጠቃቀም፡- የአበሻ ቀጠሮ ተብሎ መለያችን የሆነው የሰዓት አጠቃቀማችን ነው:: ከፈረንጆች ጋር ስንቀጣጠር «በጊዜ መድረስ አለብኝ» እንላለን:: የሚወዳትን እጮኛውን የቀጠረ ወጣት ቀደም ብሎ ይገኛል፤ ምክንያቱም መውደዱን የሚገልጽበት አንዱ መንገድ ነውና:: ክዘገየ ወዲያው እንደማይወዳት ወይም ግድ የለሽ ሰው ተደርጎ ይተረጎማልና::

**4.11.** የቦታ ክፍተት፡- በሁለት ሰዎች መካከል ያለው የቦታ ርቀት ምን ያህል እንደሚቀራረቡ ይገልጻል:: ጥሩ መግባባት የሌላቸው ሰዎች በጣም ተቀራርበው አይነጋገሩም፤ በጣም የሚዋደዱ ከሆነ በጣም ተቀራርበው ይነጋገራሉ:: በጣም መቀራረብ ጉዳዩ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው መሆኑንም ጭምር ተመልካች ይረዳል::

**4.12.** ሽታና ጣዕም፡- እነዚህ ሁለቱ የራሳቸው የሆነ መልእክት አላቸው:: ሽታ ጥሩም መጥፎም ሊሆን ይችላል፤ ያን አፍንጫ ይቀበልና መልእክት ያስተላልፋል:: መኪና ውስጥ ዓይኑን ጨፍኖ አዲስ አበባ ቄራ የደረሰ ሰው ቄራ መድረሱን የሚያውቀው በሽታ ነው:: ምላስም እንደዚሁ መልእክት ያስተላልፋል:: የሚቀመስ ነገር ምን ያህል ጣፋጭ፤ በርበሬ ወይም ጨው የበዛበት፤ ያልበሰለ ወይም ሌላም መሆኑ የሚታወቀው በጣዕም ነው::



እነዚህ ሁሉ መልእክትን የማስተላለፊያ መንገዶች ስለሆኑ በተግባቦት ወቅት ተናጋሪም አድማጭም መንገዶቹን በትክክል መጠቀማቸውን እርግጠኞች መሆን አለባቸው:: አለበለዚያ ሳይግባቡ ይቀራሉ::

ሐ. መልእክቱን ሁለቱም እኩል መተርጎም አለባቸው::

ሰው ሁሉ የሚሰማውን መልእክት በራሱ መንገድና አረዳድ ይተረጉማል:: ተናጋሪው መልእክቱን ሲያስተላልፍ ለራሱ በተረጎመው መንገድ ነው::አድማጭ ያንን ትርጉም ሳይረዳው በራሱ መንገድ ከተረጎመው ግንኙነታቸው እንደሚበላሽ ክላይ በሁለት ምሳሌዎች ተብራርቷል:: ስለዚህ በተግባቦት ወቅት ሁለቱም ሰዎች ወይም ቡድኖች መልእክቱን እኩል መተርጎም አለባቸው::

መ. ለውጤታማ ተግባቦት የመልእክቱን ዓላማ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል::

መልእክት በሚተላለፍበት ጊዜ የራሱ ዓላማና ግብ አለው:: ተናጋሪው ያንን ዓላማ ግልጽ ሲያደርግ አድማጭም በዚያው መንገድ ይረዳል፤ ምላሽ የሚሰጥበት ጉዳይ ክሆነም ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል::

ሠ. ተናጋሪው ለአድማጭ ያለው ቅርበትና አመለካከት ለውጤታማ ተግባቦት በጣም ይጠቅማል

አድማጭ ሁሉንም ሰው እኩል ቦታ ሰጥቶ አያዳምጥም:: በጣም ለሚቀርበውና ለማይቀርበው የሚሰጠው ቦታ እኩል

አይደለም። ይህ ማለት ለውጤታማ ተግባቦት መጀመሪያ ጥሩ መቀራረብ መኖር አለበት ማለት ነው።

ረ. ለውጤታማ ተግባቦት ደረጃን መጠበቅ ያስፈልጋል።
በተግባቦት ወቅት ሊጠበቁ የሚገቡ ደረጃዎች አሉ። እነርሱም:-

*ደረጃ 1. ተናጋሪው ሊተላለፍ የሚገባውን አሳብ ወይም ጉዳይ በአዕምሮው በትክክል መቅረጽ አለበት።* ለውጤታማ ተግባቦት የመጀመሪያውን ኃላፊነት የሚወስደው ተናጋሪው ነው። ተናጋሪው በትክክል ካላስተላለፈው አድማጭ ወደ በተሳሳተ መንገድ ይተረጉመዋል፤ አሊያም ሳይረዳው ይቀራል።

ደረጃ 2. ተናጋሪው አሳቡን የሚገልጽበትን ተገቢ ቃልና ቋንቋ መምረጥ አለበት። የሁለቱ ሰዎች ወይም ቡድኖች ደረጃ በዕድሜ፤ በእውቀት፤ በባሕል፤ በጾታና በሌላም ሊለያይ ይችላል። ስለዚህ ተናጋሪው አድማጭን የሚመጥን ተገቢ የማስተላለፊያ መንገድ መምረጥ አለበት።

*ደረጃ 3. ተናጋሪው ተግባቦትን የሚያደናቅፉ ነገሮች ካሉ ማስተዋልና ማስወገድ አለበት።*
አንዳንድ ጊዜ ጥቃቅን ነገሮች ተግባቦትን ሊያደናቅፉ ይችላሉ። አንድ ትንሽ ልጇን አጠገቧ ያስቀመጠች እናት የሚነገረውን በትክክል ለማዳመጥ አሳቧ ስለሚከፈል



የሚተኛ ከሆነ ማስተኛት፤ የሚጫወት ከሆነ ደግሞ እንዲጫወት ማድረግ አለባት።

*ደረጃ 4. አድማጭ የተላለፈለትን መልእክት በትክክል መስማቱን እርግጠኛ መሆን አለበት።*
ለተግባቦት የአድማጭ የመስማት ሁኔታ ወሳኝ ነው። በትክክል ለመስማቱ እርግጠኛ ካልሆነ እንደገና እንዲናገር ማድረግ ያስፈልጋል። በትክክል ካልተሰማ በደንብ አልሰማሁም፤ እስቲ ድገምልኝ ማለት ችግሩን ያስወግደዋል።

*ደረጃ 5. አድማጭ የሰማውን መልእክት ተናጋሪው ባስተላለፈለት መንገድ መተርጎም አለበት።*
መልእክቱ በሁለቱም ሰዎች አዕምሮ በተመሳሳይ መንገድ በትክክል ከተተረጎመ ተግባብተዋል ማለት ነው። ተናጋሪው በመናገሩና አድማጭ በመስማቱ ብቻ ተግባቦት አይፈጠርም።

*ደረጃ 6. አድማጭ የሰማውንና የተረጎመውን መልእክት በማሰላሰል ማዳበር አለበት።*
በአእምሮ ውስጥ የዳበረ መልእክት ለተግባር አያስቸግርም። እነዚህ ሂደቶች ከተጠበቁ የሚወያዩ ሰዎች ወይም ቡድኖች ተጋባቦትን ይፈጥራሉ፤ ስለዚህ ተግባቦትን ለመፍጠር ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው። ያ ሳይሆን ሲቀር አንዱ ሌላውን መተቸት ይመጣል።

# ምዕራፍ ሦስት
# ምዕመናን በወንጌል ምስክርነት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው» ማቴ. 9:37 አለ:: እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ለወንጌል ስርጭት በከፈተው ሰፊ በር ምክንያት ከምን ጊዜም በላይ የበዛ መከር ስላለ ያንን ለመሰብሰብ ወንጌላዊያንን በመላክ ብቻ እንፈጽማለን ማለት የማይሆን ነገር ነው:: በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያን በመላ ሀገሪቱ ወንጌላዊያንን ለማሰማራት የሚያስችል አቅም የላትም:: በሌላ በኩል ወንጌላዊያንን በመላ ሀገሪቱ የመላክ አቅም ቢኖርም እንኳን ብቻቸውን የወንጌልን ተልዕኮ ሊፈጽሙ አይችሉም:: ከዚህ ሁሉ በላይ ግን የወንጌል ተልዕኮ የወንጌላዊያን ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው የዳኑ ሁሉ መሥራት የሚገባቸው የሁሉ ኃላፊነት ስለሆነ ምዕመናንን ለወንጌል ምስክርነት ማነሳሳት ለውጤታማ የወንጌል አገልግሎት ወሳኝ ነው::

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በ87 ዓመታት ወደ 8 ሚሊዮን ያደገችው በዋናነት አማኞች ሁሉ ስለሚመሰክሩ ነበር:: ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ ምሳሌዎችን በ ገጽ 185 «ሸ» (ቤተ ክርስቲያን ያደገችው በአማኞች ምስክርነት ነው) በሚለው ርዕስ ሥር ይመልከቱ::



## 1. ምዕመናን ማን ናቸው?

ምዕመን የሚለው ቃል ላኦስ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ሕዝብ ማለት ነው:: ብዙ ጊዜ የተጠቀሰው «የእግዚአብሔር ሕዝብ በመባል» ነው:: ቃሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትና አዳኝነት በማመን ለእርሱ የተሰጡትን ሁሉ ያጠቃልላል::

እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠራል፤ ሕዝቡም ይመልሳል:: ይህ መሠረታዊ እውነት በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት የሚገለጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው:: በክርስቶስ አምኖ የዳነ ሁሉ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ተልዕኮና ጥሪ አለው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ እንዲሠሩ ይጠራቸዋል:: ዮሐ. 15:5 «በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል» ይላል:: ስለዚህም ምዕመን ስንል በክርስቶስ አምኖ የዳነ ብቻ ሳይሆን ያዳነውን ጌታ እንዲያገለግል የተጠራ ማለትም ነው:: ለምዕመናን ጌታን ማገልገል

ሀ. ኃላፊነትም ዕድልም ነው::
ለ. ውስጣዊ ደስታ ይሰጣቸዋል::
ሐ. የተሰጣቸውን መክሊት የሚነግዱበት መንገድ ነው::
መ. በእውቀትና በጸጋ ያሳድጋቸዋል::
ሠ. መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ያጠነክራል::

ረ. የጠራውን ጌታ መታዘዝና ለጥሪውም ምላሽ መስጠት ነው።

ሰ. መሠረታዊ የክርስትና ልምምድ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጠራውና ስጦታን የሚሰጠው ዘለዓለማዊ ዕቅዱ የሆነውን ዓለምን የማዳን ተልዕኮ እንዲፈጽሙ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል» ይላል (1 ቆሮ. 12:7)። ይህ እያንዳንዱ አማኝ ጌታን ለማገልገል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደተሰጠው ያሳያል። ሐዋሪያው ጴጥሮስም አማኞች ሁሉ ካህናት መሆናቸውን በመልእክቱ ጽፏል (1 ጴጥ. 2:9)። በዓለማችን ላይ ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ ማርቲን ሉተር የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትን ሉዓላዊ ሥልጣን በመቃወም የአማኞችን ሁሉ ክህነትና የማስታረቅ አገልግሎት አጥብቆ ያስተምር ነበር። የብሉይ ኪዳን ካህናት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የማስታረቅ ኃላፊነት እንደነበረባቸው የአዲስ ኪዳን ካህናትም እንዲሁ ተሰጥቶአቸዋል።

ሪክ ዋረን «ዓላማ መር ቤተ ክርስቲያን» በተባለ መጽሐፉ እንዲህ ሲል ጽፏል።

አንድ ጊዜ ናፖሊዮን ወደ ቻይና ካርታ በማመልከት እንዲህ አለ። እዚህጋ አንድ እንቅልፉን የተኛ ግዙፍ አያለሁ (የቻይናን ሕዝብ ማለቱ ነው)። የነቃ ዕለት ማንም ሊያቆመው አይችልም አለ። እኔ እንደማምነው ይላል ሪክ



ዋረን፤ ቤተ ክርስቲያን የተኛ ግዙፍ ነው። በየእሁዱ የቤተ ክርስቲያን ወንበሮች ምንም አገልግሎት ሳይኖራቸው እምነታቸውን ብቻ ጠብቀው በሚኖሩ አማኞች የተሞሉ ናቸው። በንቃት የሚሳተፉ አማኞች የሚባሉትም ከቤተ ክርስቲያን ሳይቀሩ ሁል ጊዜ የሚመጡና አገልግሎቱን በገንዘብ የሚደግፉ ናቸው። ከዚህ የበለጠ ነገር አይጠበቅባቸውም። ነገር ግን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ከመምጣትና ገንዘብ ከመስጠት የበለጠ ትልቅ ነገር እንዲያደርጉ ከእያንዳንዱ አማኝ ይጠብቃል። እያንዳንዱ አማኝ በስጦታውና በጸጋው እንዲያገለግል ይፈልጋል። እኛ ይህን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተኛውን ግዙፍ ኃይል ብናነቃውና ጸጋቸውን፤ ስጦታቸውንና እውቀታቸውን ብንጠቀም ወንጌል በማይቆም ፍጥነት አድጎ ዓለምን በፍጥነት ይደርሳል።

ምዕመናን የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲያውቁ ማድረግ የመሪዎች ኃላፊነት ነው። ቤንጃሚን ፍራንክሊን የተባለው ሰው "By failing to prepare, you are preparing to fail" አለ። ይህም ማለት ሰዎችን ማዘጋጀት ሲያቅተን እኛም ለውድቀት እየተዘጋጀን ነው ማለት ነው። ስለዚህ ምዕመናን ስንል በክርስቶስ አምነው የዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሲሆኑ ለመንግሥቱ ሥራም የተጠሩ ናቸው።

## 2. የምዕመናን የወንጌል ተልዕኮ

የወንጌል ምስክርነት የወንጌላዊያንና የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ኃላፊነት ብቻ አይደለም። ብዙ ምዕመናን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃላፊነታቸውን ስለማያውቁ የወንጌል ምስክርነቱን ለወንጌላዊያንና ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ይተውታል። ይህ ብቻ ሳይሆን ወንጌላዊያንን ለመላክ ገንዘብ ስለሰጡ ኃላፊነታቸውን ሁሉ የተወጡና ታላቁን ትዕዛዝ የፈጸሙ ይመስላቸዋል። በአንድ በኩል የወንጌል ምስክርነት የወንጌላዊያን ብቻ ሳይሆን የምዕመናንም ጭምር ነው። በሌላ በኩል ወንጌላዊን በገንዘብ መደገፍ ብቻ ሳይሆን በምስክርነትና በሌሎችም አገልግሎቶች መሳተፍ ከእያንዳንዱ ምዕመን ይጠበቃል። የሚከተሉት አራት ዋና ዋና ነገሮች ምዕመናን በወንጌል ተልዕኮ ማድረግ የሚገባቸው ናቸው።

### 2.1. ራስን መስጠት

ሐዋሪያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 9:22-23 «. . . በሁሉ መንገድ አንዳንዶቹን አድን ዘንድ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ። በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ» ይላል። በዚህ ቦታ ጳውሎስ ስለ ራሳቸው ብቻ እንደሚያስቡት እንደ ቆሮንቶስ ሰዎች ሳይሆን ራሱን ስለ ወንጌል ሲል ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት ወንጌል ለሁሉም እንዲደርስ ያለውን መሰጠት እንመለከታለን። ለዚህ መሰጠት ምክንያቱ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ወንጌል ዓለም ሁሉ እንዲሰሙ ነው። ይህን ለማድረግም ራሱን የሁሉ አገልጋይ አደረገ፤ መብቱ የሆኑትንም ነገሮች



ሁሉ ለወንጌል ሲል ተወ። ስለዚህም ጌታ ዋጋውን እንደሚከፍልለትና የወንጌልን በረከት እንደሚካፈል ይናገራል። ይህም በረከት ጌታ «አንተ ታማኝ ባሪያ» (ማቴ. 25:1-23) ማለቱንና ሰዎችም ወንጌልን ሰምተው በክርስቶስ አምነው ሲድኑ ማየቱን ነው።

በ2ቆሮ. 8:5 የመቄዶኒያ ሰዎች በብዙ መከራና ጥልቅ በሆነ ድህነት ውስጥ እያሉ ከዓቅማቸው የሚበልጥ ስጦታ እንዲሰጡ ያደረገበትን ምክንያት ሲገልጽ «አስቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብን አይደለም» አለ። ይህ ማለት የመቄዶኒያ ሰዎች መጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጥተው ስለነበር እየተፈተኑ ያሉበት መከራና እየኖሩ ያሉበት ጥልቅ የሆነ የድህነት ኑሮ በፍጹም ልግስና ያላቸውን ለሌሎች ለማካፈል አላገዳቸውም ማለት ነው።

ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክት ደግሞ «እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፤ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና» (1ተሰ. 2:8) በማለት ራሱ ለጌታም ለሚያገለግላቸው ሰዎችም በፍጹም እንደተሰጠ ይናገራል። ጳውሎስና አብረው ያሉት አገልጋዮች ለተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌልን ሰበኩላቸው። ሚስዮናውያኑ ለተሰሎንቄ ሰዎች ያላቸው ፍቅር ከጌታ የተቀበሉትን የወንጌልን አገልግሎት ማገልገል ብቻ ሳይሆን

ነፍሳቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ እንዲሆኑ አደረጋቸው። ይህም እነርሱ ካገለገሉአቸው ሰዎች ጋር ምን ያህል የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ያሳያል። ይህም የጳውሎስን መስጠት ብቻ ሳይሆን ወንጌልን የሚያገለግሉ ሁሉ የዚህ ዓይነት መሰጠት ለሚያገለግሉአቸው ሰዎች እንዲኖራቸው ትልቅ ትምህርት ነው።

### 2.2. ወንጌልን መመስከር

የወንጌል መልእክት በፍጥነት እንዲደርስ ክተፈለገ ምዕመናን ሁሉ መስካሪ መሆን አለባቸው። ይህ ደግሞ የሰው ሥርዓት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ነው። በአሁን ጊዜ የተለመደው ወንጌላዊያንን በመላክና በገንዘብ በመደገፍ ወንጌልን መስበክ ነው። ይህ በጣም አስፈላጊና ብዙ ፍሬም እያየን ያለንበት አገልግሎት ቢሆንም ምዕመናን መስካሪዎች ካልሆኑ የወንጌል ስርጭት ስኬታማ ሊሆን አይችልም። በመጀመሪያ አጠገቡ ያለው ወደ ሲያል እየሄደ «ኢየሱስ ያድናል» ለማለት ሸክሙ ከሌለ ለማያውቀው ሰው ለመመስከር ወንጌላዊ መላክ የወንጌል ሸክም ሳይሆን ገንዘብ ስላለ ወይም ቤተ ክርስቲያን ስላለች ብቻ የሚደረግ አገልግሎት ይሆናል። በሁለተኛ ደረጃ ለጓደኞቻቸው፤ ለዘመዶቻቸው፤ አብረው ለሚኖሩና ለጎረቤቶቻቸው የማይመሰክሩ ሰዎች ከላይ እንደተጠቀሰው የሚሰጡት ሸክም ተሰምቲቸው ስላይደለ በአንድ ወቅት የገንዘብ ስጦታቸውን ማቆማቸው የማይቀር ነው። ስለዚህም የወንጌል ስርጭት



እንዲቀጣጠልና ስጦታውም ቋሚ እንዲሆን ምዕመናን መስካሪ መሆን አለባቸው። ከዚህም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ በጌታ ኢየሱስ ያመኑ ሁሉ እንዲመሰክሩ አጥብቆ እንደሚያስተምር በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመለከታለን።

ሀ. የታላቁ ተልዕኮ ትዕዛዝ አማኝ ሁሉ እንዲመሰክር ያስገድዳል።

«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ማር. 16:15 ጌታ ኢየሱስ ይህንን አስደናቂ ትዕዛዝ ከሰጣቸው በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ትቶ ወደ አባቱ ሄደ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ዓለም ሁሉ ሲሰማው የሚገባ እንደዚህ ዓይነት መልካም ዜና አልነበረም።

ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ዜና ለዓለም ሲያበስሩ ሌላ ሊፈጽሙት የሚገባ ሥራም ነበራቸው። በዓለም ሁሉና በትውልድ ሁሉ እነርሱ የሚሠሩትን ሥራ የሚሠሩ ሌሎችን ማዘጋጀት ነበረባቸው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ እንደዚህ አላቸው። «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ማቴ. 28:19-20

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትዕዛዝ ለሰው ልጆች ከተሰጡት ትዕዛዛት ሁሉ ትልቁ ነው። እነርሱ በዘመናቸው እንደታዘዙትና እንደፈጸሙት እኛም በዘመናችን

ልንታዘዘውና ልንፈጽመው ኃላፊነት አለብን፡፡ እኛ ያለንበት ዘመን እነርሱ ከነበሩበት የበለጠ አስቸጋሪ አይደለም፤ የሰው ፍላጎትም በዚያን ዘመን ከነበሩት ሰዎች የተለየ አይደለም፤ የወንጌል መልእክት ለዓለም ሁሉ በእኩልነት ያስፈልጋልና፡፡ «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው» 1 ጢሞ. 1:15፡፡

ግልጽ የሆነ የሚስዮናዊነት አሳብ የሚገኘው በዘፍ. 12:1-3 እግዚአብሔር አብርሃምን ለመባረክና የምድር ነገዶችም ሁሉ በዘሩ እንደሚባረኩ ቃል በገባበት ክፍል ነው፡፡ ቁ. 3 «የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ይላል፡፡ እዚህጋ በረከት ለእግዚአብሔር የተስፋው ኪዳን ቁልፍ ቃል ሆኖ እናገኛለን፡፡ እግዚአብሔር «የምድር ነገዶች ሁሉ» ሲል ከአንድ ቤተሰብ የበለጠ እንደሆነ በግልጽ እንረዳለን፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ቃል ኪዳን መጀመሪያ ከአብርሃም ጋር መሠረተ (ዘፍ. 12:1-3፤ 18:18-19፤ 22:15-18)፡፡ በኋላ ከይስሐቅ ጋር (26:2-4) ከዚያም ከያዕቆብ ጋር (28:14) አደረገ፡፡ በዘጸ. 19:5-6 እስራኤላውያንን «ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ትውልድ፤ የካህናት መንግሥት፤ የተቀደሰ ሕዝብ» በማለት ኪዳኑ ለእስራኤል ሁሉ እንደሆነ አስታወቀ፡፡ ይህም ኪዳን መጀመሪያ ዮሴፍ ለግብፃውያንና ለእስራኤላውያን (ለምድር ነገዶች ሁሉ) በረሃብ ዘመን በረከት በመሆን (ዘፍ. 41:57) የተፈጸመ ሲሆን ቀጥሎም ዮናስ ለነነዌ ሰዎች የንስሐን ስብከት በመስበኩ ተፈጽሟል፡፡



ጌታ ኢየሱስም ከሞት ከተነሣ በኋላ «አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» በሚለው ታላቁ ትዕዛዙ ተከታዮቹን አዟቸዋል፡፡ ጳውሎስ በገላቲያ 3:8-9 «መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ፡፡ እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ» ብሏል፡፡ በቁ. 14 ደግሞ «የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ» ይላል፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑት የእምነት ሰው ከሆነው አብርሃም ጋር ተባርከዋል ማለት ነው፡፡

በማቴ. 28:18-20 የምናገኘው ታላቁ ተልዕኮ የትንሣኤው ጌታ አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ ያዘዘን ትዕዛዝ ነው፡፡ በዚህ ትዕዛዝ «ሂዱ» የሚለው ቃል በወቅቱ የነበሩት ደቀ መዛሙርቱና በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሁሉ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ጌታን ያላወቁ ሰዎች ወዳሉበት እንዲሄዱ ያዛል፡፡ ፕራካሽ የተባለ ሕንዳዊ ምሁር «አንተ ዓሣዎች ወዳሉበት ሂድ፤ ዓሣዎች ወደ መረቡ አይዋኙም» ያለው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ በሐዋ. 1:8 «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፤ በይሁዳም ሁሉ፤ በሰማርያም፤ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሎ ጌታ ኢየሱስ የመሄዳቸውን ኃይልና አድራሻ ገለጠላቸው፡፡

የመሄድ ዋና ዓላማ ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ነው። ደቀ መዝሙር ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው? ዊሊያም ሄንድርክሰን የተባለ ጸሐፊ እንደዚህ ብሎ ያብራራል።

ምንም እንኳ ደቀ መዝሙር ማድረግ የሚለው ቃል ሰዎች ወደ ጌታ እንዲመጡ ማድረግ የሚለውን የሚያካትት ቢሆንም ሁለቱ ግን የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ደቀ መዝሙር ማድረግ ማለት ሰው አእምሮውን ፈቃዱንና ልቡን ሁሉ ለእግዚአብሔር ማስገዛት ማለት ነው። ደቀ መዝሙር ማለት ተማሪ ማለት ስለሆነ መምህሩን የሚመስል ነው ማለት ነው። ስለ ክርስቶስ አውቆ መከተል ብቻውን በቂ አይደለም። ክርስቶስ በውስጡ ተተክሎ እሱም በአነጋገሩና በኑሮው ሁሉ በቃሉ እውነት የሚኖር መሆን አለበት። አማኞች የራሳቸውን ፈቃድ ያደርጋሉ፤ ደቀ መዛሙርት ግን የጌታቸውን ፈቃድ ያደርጋሉ።

አንድን ሰው ደቀ መዝሙር ለማድረግ ቢያንስ አምስት ነገሮች መደረግ አለባቸው።

1. ክርስቶስ በውስጡ መኖር አለበት

«በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ፤ በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል (ዮሐ.15:1-8)። አንድ ዘር እንዲበቅልና እንዲያድግ ሲፈለግ መጀመሪያ ይዘራል። ክርስትናም እንደዚህ ነው። አንድ ሰው ደቀ መዝሙር ለመሆን መጀመሪያ ዘር በውስጡ መኖር አለበት። ያም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።



ሰው በውስጡ ክርስቶስ መኖር ሲጀምር ሕይወቱ መለወጥ ይጀምራል። ቀድሞ የሚኖረውን ኑሮ መኖር አይችልም።

2. በእግዚአብሔር ቃል ሥር መስደድ አለበት

«እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ» (ዮሐ. 8:31)።

ዘር የቱንም ያህል ወደ ላይ ቢያድግና ወደ ጎን ቢወፍር ሥር ከሌለው ሊቆም አይችልም። አንድ ሰው ጌታን የግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ በቃሉ ሥር ካልሰደደ እንደዚሁ ነው። የብዙ ሰዎች ክርስቲናም እያመለኩ፤ እየዘመሩ፤ መባና አሥራትም እየሰጡ ግን መቆም ያልቻለው በቃሉ ሥር ስላልሰደዱ ነው። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 7:24-27 ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው (በቃሌ ሥር የሰደደው) በዓለት ላይ ቤትን የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል ብሎ ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው (በቃሌ ሥር ያልሰደደው) ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል ያለው። በማቴ. 4:1-11 የሰይጣንን ፈተና «ተብሎ ተጽፏልና» እያለ ያሸነፈው ለዚህ ነበር። ጌታን መከተል አንድ ነገር ነው፤ ደቀ መዝሙር መሆን ግን ሌላ ነገር ነው። ደቀ መዛሙርት ሳይሆኑ ተከታዩች ብቻ የሆኑት ሁኔታዎች ሲለወጡ ትተው ይሄዳሉ፤ ደቀ መዛሙርት ግን እንደ ጴጥሮስ «ከአንተ ወደ ማን እንሄዳለን» ይላሉ። ስለዚህም አንድ አማኝ ደቀ መዝሙር ለመሆን ማድረግ ያለበት ሁለተኛው ነገር በቃሉ ሥር መስደድ ነው።

3. በጸሎት ወደ ላይ ማደግ ነው

«ወደ እኔ ጩኽ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ» ኤር. 33:3::

«ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል» ማቴ. 7:7

ሰው የሚጮኸው ወደ ላይ ነው:: ወደ ላይ በጮኸ ቁጥር ከላይ ጋር ያለው ግንኙነት እየጠነከረ ይሄዳል:: ሰው በጸሎቱ ከአምላኩ ጋር በተጣበቀ ቁጥር የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገቱም በዚያው ልክ ይፈጥናል:: ስለዚህ በቃሉ ሥር የለደደ አማኝ በጸሎት ደግሞ ወደ ላይ ማደግ አለበት::

4. ከአማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ አለበት

«ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው» መዝ. 133:3

«ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ፤ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው» ሐዋ. 4:32

አማኝ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ያስፈለገውም ወንጌልን ለመመስከርና ያመኑት በአንድነትና በኅብረት እንዲኖሩ ነው:: ይህ ኅብረት አራት ነገሮችን ያካትታል፤ እነርሱም የሐዋሪያት ትምህርት፤ ኅብረት፤እንጀራን መቁረስና ጸሎት ናቸው:: የመጀመሪያዎቹ አማኞች ይህን ያደርጉ ስለነበር



- የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣዔ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር::
- በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው::
- በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረም:: አንድ አማኝ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ከሌለው የመስቀሉን ጉዞ መዝለቅ አስቸጋሪ ይሆናል:: ወንድማችን ታምራት ወልባ እንደዚህ ብሎ ዘምሯል::

  አንዱ የሌላውን ሸክም ይዞ
  ካልተወጣው እርስ በርስ ተጋግዞ
  እንዴት ይዘለቃል የመስቀሉ ጉዞ

5. ላልሰሙት መመስከር አለበት::

ጌታ ኢየሱስ «ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል» (ዮሐ. 15:2)፤ «ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል» (15:8):: አንድ ጌታን የተከተለ አማኝ ደቀ መዝሙር ሆነ የሚባለው ፍሬ ሲያፈራ ነው:: እነዚህ አምስት ነገሮች በአንድ ሰው ሕይወት ሲከናወኑ ደቀ መዝሙር ሆነ ማለት ነው:: ሰዎች እርሱን ሲመለከቱ አማኝ ራሱ መስቀል መሆኑን ያያሉ::

ሉቃስ 9:23

በአምልኮና በምልጃ ማገልገል






# የታላቁ ተልዕኮ ትዕዛዛት በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ

| ጥቅስ | ሥልጣን | ኃይል | የተልዕኮ ስፋት | መልእክቱ | ተግባር |
|---|---|---|---|---|---|
| ማቴ. 28:18-20 | በሰማይና በምድር ሥልጣን ተሰጠኝ | እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ | አሕዛብን ሁሉ | ክርስቶስ ያዘዘውን ሁሉ | በመሄድ፤ በማጥመቅና በማስተማር ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው |
| ማር. 16:15 | | | ለዓለም ሁሉ | ወንጌል | ስበኩ |
| ሉቃ. 24:46 | በስሙ | አብ የሚሰጠው ተስፋ. . . መንፈስ ቅዱስ | ከኢየሩሳሌም ጀምሮ አሕዛብን ሁሉ | ንስሐንና የኃጢአት ይቅርታን | መስክሩ፤ ስበኩ |
| ዮሐ. 20:21 | አባቴ እንደላከኝ እኔም እልካችኋለሁ | | | | |
| ሐዋ. 1:8 | | የመንፈስ ቅዱስ ኃይል | በኢየሩሳሌ፤ በይሁዳም ሁሉ፤ በሰማርያም፤ እስከ ምድር ዳር ድረስ | ክርስቶስ | ምስክሮቼ ትሆናላችሁ |

የሐዋርያው ጳውሎስን የታላቁን ተልእኮ አስተምህሮ ጆርጅ ፐተርስ የተባለ ምሁር እንደሚከተለው አስቀምጦታል፡፡

- ዓለምና በውስጥዋ ያሉት ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህም ስለ እግዚአብሔር ይናገራሉ፤ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥልጣን ሥር ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ለእግዚአብሔር ተጠያቂዎች ናቸው (ሮሜ 18:1ff)፡፡
- ሰው ሁሉ የመጣው ከአዳም ዘር ነው፤ ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የተጻፈ ነው (ሮሜ 5:12-21)፡፡
- ሰው ሁሉ በአዳም ውድቀት ምክንያት ኃጢአተኛ ሆኗል (ሮሜ 5:12-21)፡፡
- በክርስቶስ ምክንያት ሰው ሁሉ ከኃጢአቱ የሚድንበት የደኅንነት መንገድ ተዘጋጅቶለታል (ሮሜ 5:1፤2-21)፡፡
- እግዚአብሔር ያዘጋጀው የደኅንነት መንገድ አንድ ብቻ ነው . . . በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መዳን፡፡ ይህ ደግሞ ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም ጭምር ነው (ሮሜ 3:21፤ 5:21)፡፡
- እግዚአብሔር ያዘጋጀው የደኅንነት መንገድ ነጻ ስጦታ እንጂ በሰው ሥራ አይደለም፡፡ ይህ የተገለጠውም የምሥራች በሆነው በቃሉ ስለሆነ ለሰው ሁሉ ሊነገር ይገባል (ሮሜ 10:8-17፤ 16:25-26)፡፡
- ሐዋሪያው ጳውሎስ ራሱ ለዚህ ለተገለጠው ወንጌል ለዎች እንዲታዘዙና እንዲያምኑ ለመስበክ እንደ ተጠራና እንደ ተለየ ተረድቷል፡፡ ይህ የሐዋሪያነቱ ማኅተም ነው፤ ለዚህም ቀንና ሌሊት ሲተጋ ኖሯል፤ ለዚህም ዋጋ ከፍሏል (ሮሜ 1:1ነ5ነ14፤ 11:13ነ25፤ 15:15-16፤ 16:25-27)፡፡

ይህ ታላቁ ትዕዛዝ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው የዳኑ ሁሉ ሊመሰክሩት ወይም ለሌሎች ሊያካፍሉት፤ ያላመኑ ሁሉ ደግሞ ሊሰሙት የሚገባ ታላቁ ትዕዛዝ ነው፡፡

ለ. የአማኞች ሁሉ ክህነት ያስገድደናል፡፡

«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» 1ጴጥ. 2:9

ሰው ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ተለይቶ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ልዩ ፍጡር ሊሆን የእግዚአብሔርን ዓላማና ተልዕኮ ለመፈጸም ኃጢአት የሌለበት ሆኖ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ ምክንያት በራሱ ምርጫ ኃጢአተኛ ሆነ፡፡ ከዚህም የተነሳ ከእግዚአብሔር ክራሱና ከተቀመጠለት መለኮታዊ ዓላማ

ራሱን ለየ:: ይህም ከእግዚአብሔር ጋር የተቋረጠው ኅብረት እንደገና ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ቅዱስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ የክህነት አገልግሎት እንዲኖር አስገደደ::

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተለያዩ የክህነት ዓይነቶች እንዳሉ እንመለከታለን::

*የግል ክህነት*- ከሰው ውድቀት ጀምሮ እስከ አባቶች ድረስ ባለው ጊዜ ሰው በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኝ ነበር:: ቃየልና አቤል በየግላቸው መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ማቅረባቸው የክህነት አገልግሎት ነበር (ዘፍ. 4:3-16)::

*የአባቶች ክህነት*- በአባቶች ዘመን የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባወራ ለቤተሰቡ ካህን ሆኖ በማገልገል ለእግዚአብሔር መሥዋትን እንዳቀረበና ከእግዚአብሔርም መገለጥን እንደ ተቀበለ እንመለከታለን:: የእስራኤል አባቶች የሆኑት አብርሃም (ዘፍ. 12:7-9)፤ ይስሐቅ (ዘፍ. 26:24-25)ና ያዕቆብ (ዘፍ. 35:6-8)፤ ኖኅ (ዘፍ. 8:20)፤ ኢዮብ (ኢዮብ 1:4-5)፤ መልከጼዴቅ (ዘፍ. 14:18)ና ሌሎችም የክህነትን አገልግሎት አገልግለዋል:: ኢዮብ ለልጆቹ የሚያቀርበው መሥዋዕት ለዚህ ትልቁ ምሳሌ ነው::

*የሕዝብ ክህነት*- «አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፤ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፤ እናንተም የካህናት መንግሥት፤ የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ» (ዘጸ. 19:5-6)::



እግዚአብሔር በሲና ተራራ በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ ከሰጣቸው የተስፋ ቃሎች አንዱ እነርሱ ቃሉን ቢጠብቁ የተመረጠ ርስት፤ የካህናት መንግሥት፤ የተቀደሰ ሕዝብ እንዲሆኑ ማድረግ ነው:: እግዚአብሔር እስራኤልን ከሌላው ሕዝብ ለይቶ ባርኮ ነበር፤ ነገር ግን እነርሱ ቃሉን ባለመጠበቃቸው በካህናት አማካይነት ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ተገደዱ::

*የአሮን ክህነት*- «አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ» (ዘጸ. 28:1):: ምንም እንኳ እስራኤል ባለ መታዘዝ ካህናት መሆን ባይችሉም እግዚአብሔር በምሕረቱ ከሌዊ ልጆች አሮንንና ልጆቹን ለክህነት አገልግሎት መረጣቸው:: ኃጢአተኛ የሆነው ሕዝብ ቅዱስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ቀጥታ መገናኘት ስለማይችል አሮንና ልጆቹ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በመሆን የማስታረቅ አገልግሎት እንዲያገለግሉ አደረገ::

*የክርስቶስ ክህነት*- «ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን» (ዕብ. 8:1)::

የአሮን ክህነት የሕዝቡንና የራሱን መስዋዕት ይዞ የሚቀርብ ሊሆን ደም ሳይዝ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አይገባም:: የክርስቶስ ክህነት ግን ለራሱ ሳይሆን ለዓለም ሁሉ አንድ

ጊዜ ራሱን መሥዋዕት ያደረገበት ክህነት ነው። የአሮን ክህነት ለሚመጣው ለክርስቶስ ክህነት ምሳሌና ጥላ ነበር (ዕብ. 8:1-6፤ 9:6-14)። ክርስቶስ በምትሻለውና በምትበልጠው በእጆችም ባልተሠራች ድንኳን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ። ይህ ክህነት የማይለወጥ የዘላለም ክህነት ነው፡ አሁን በአባቱ ቀኝ ሆኖ ይማልድልናል (ሮሜ 8:34፤ ዕብ. 7:25፤ 1ዮሐ. 2:1፤ 1ጢሞ. 2:5)።

*የአማኞች ሁሉ ክህነት-* «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ጴጥ. 2:9)። በአዲስ ኪዳን አማኞች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ መሥዋትን እንዲያቀርቡ ታዘዋል። ይህ በብሉይ ኪዳን ከምናየው በካህኑ አማካይነት ከሚቀርበው መሥዋዕት የተለየ ነው። ባሕሪውም ይለያል።

- በአማኞች ሁሉ ክህነት አማኝ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥታ መገናኘት ይችላል፤ በዚህም እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት የራሱ አገልግሎት አለው።
- እያንዳንዱ አማኝ ከጌታ በተቀበለው ጸጋ የማገልገል ኃላፊነት አለበት።



- ቤተ ክርስቲያንም አማኞች ሁሉ በተሰጣቸው ጸጋ ጌታን የሚያገለግሉበትን ሁኔታ የማመቻቸትና ጸጋቸውንና ጥሪያቸውን የመለየት ኃላፊነት አለባት።

የብሉይ ኪዳን ክህነት እስራኤልን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ እንደሆነ የአማኞች ሁሉ ክህነትም ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በኩል ያልታረቁትን የማስታረቅ ኃላፊነት ነው። ይህን ኃላፊነት መወጣት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታ ነው። ስለዚህም አማኞች ሁሉ የደኅንነትን ወንጌል በመመስከር ሰዎችን በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ እግዚአብሔርን መታዘዝ አለባቸው።

*ሐ. የክርስቶስ መልእክተኞች መሆናችን ያስገድደናል።*

ሐዋሪያው ጳውሎስ በ2ቆሮ. 5:17-20 በክርስቶስ አምኖ የዳነ ሁሉ የክርስቶስ መልእክተኛ መሆኑን ይናገራል፤ በቁ. 17 «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» ይላል። ይህ በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ መለወጣቸውን ያሳያል። በቁ. 18 ና 19 «ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን፤ የማስታረቅን አገልግሎት ከሰጠን . . . በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ» ይላል። እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት ያደረገን በክርስቶስ በኩል ከራሱ ጋር አስታርቆን ሲሆን በታረቁት ሰዎች ላይ የማስታረቅን ቃል አኖረ። ቀጥሎ ቁ. 20 ላይ «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤

ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» ይላል:: እዚህጋ መልእክተኞች ያደረጋቸው በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀው አዲስ ፍጥረት የሆኑትን ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ ያላመኑትን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅ ግዴታ አለበት ማለት ነው::

የነቢዩ ዮናስን ሕይወት ከመጽሐፉ ስንመለከት መልእክት ይዞ መኮብለል ወይም መተኛት በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል እናያለን:: ዮናስ ከ120,000 የሚበልጡ የነነዌ ሰዎች የሚድኑበትን መልእክት እንዲናገር እግዚአብሔር ልኮት እርሱ ግን ወደ ቴርሴስ ለመኮብለል ዋጋ ከፍሎ መርከብ ውስጥ ገባ:: ዮናስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክትን እየተቀበለ ለእስራኤል ይናገር ነበር፤ ትንቢቱም ይፈጸም ነበር:: በዚህ ጊዜ ግን ለመኮብለል የፈለገበት ምክንያት በ4:1 እንደምንመለከተው እርሱ ከሰበከ በኋላ የነነዌ ሰዎች ንስሐ ቢገቡ እግዚአብሔር በባሕሪው መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነ ስለሚምራቸው፤ እርሱ ግን የነነዌ ሰዎች አሕዛብ ስለሆኑ (የአብርሃም ነገዶች ስላይደሉ) መገልበጥ አለባቸው ብሎ ስለሚያምን ይህን መልእክት መናገር አልፈለገም:: እዚህ ላይ ማየት የሚገቡን ነገሮች አሉ::

- ዮናስ በራሱ አሳብ ስለተሞላ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪና ለሁሉ የሚራራ መሆኑን አልተገነዘበም፤



እግዚአብሔርን ለአይሁድ ብቻ የሚገደው አይሁዳዊ አድርጎ አስቧል::

- የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባሉት እስራኤላውያን ብዙ ነቢያት የንስሐ መልእክት ሰብከው ንስሐ መግባት ሲገባቸው አንገታቸውን ሲያደነድኑ አሕዛብ ናቸው የተባሉ የነነዌ ሰዎች ግን በአንድ መልእክት ንስሐ ገብተው እንደሚድኑ አላሰበም::
- እርሱ የተናገረው መልእክት የግድ መፈጸም አለበት ብሎ ያምናል፤ ከዚህም የተነሳ ሰበክ ተብሎ ሄዶ «ትገለበጣላችሁ» ብሎ ትንቢት ተናግሮ ሳይገለበጡ ሲቀሩ «ሞት ይሻለኛል» እያለ ከእግዚአብሔር ጋር ሲከራከር ነበር:: እግዚአብሔር ለነነዌ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለዮናስም መሐሪ ነው::
- ማንም እንዳይጠፋ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ አልተገነዘበም::

ስለዚህም ወደ ቴርሴስ ይኮበልል ዘንድ ተነሣ:: እግዚአብሔር ደግሞ ከ120,000 የሚበልጡ የነነዌ ሰዎች የሚድኑበትን መልእክት ይዞ እንዲያመልጥ አልፈቀደም::

ከዚህም ሌላ መርከቢቱ ስትናወጥና ሰዎች ሁሉ ወደየአምላካቸው ሲጮኹ እርሱ ግን ይህን ክቡርና ድንቅ መልእክት ይዞ በመርከቢቱ ወደ ውስጠኛው ክፍል ገብቶ በከባድ እንቅልፍ ተኛ:: ይህ ደግሞ የመርከቢቱን መሪ አስገረመው፤ «ምነው ተኝተሃል?» አለው:: የእንግልዝኛው

ትርጉም «እንዴት ልትተኛ ትችላለህ?» ይላል። ይህ ማለት እኛ እንደዚህ ስንሆን አንተ እንዴት አድርጎ እንቅልፍ ይወስድሃል? ማለቱ ነው። ዮናስ ያን የመሰለ ከባድ መልእክት ይዞ ይኮበልል ዘንድ ተነሳ፤ እንደዚያ ያለ መልእክት ይዞ መርከቢቱ ስትናወጥ፤ ማዕበሉ ሲያስጨንቅ እርሱ ግን በከባድ እንቅልፍ ተኛ። ከባድ መልእክት ይዞ በከባድ እንቅልፍ መተኛት።

የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን ዘመናችን በጠላት ማዕበል ሲናወጥ፤ ብዙዎች ወደማያድን አምላክ ሲጮኹ እኛ ግን ክቡር የሆነውን መልእክት ይዘን የምንተኛበት ጊዜ አይደለም፤ ይልቅስ ተግተን የምንመሰክርበትና ወንጌልን የምናውጅበት ጊዜ እንጂ።

መ. በጌታ እራት ወቅት የምንገባው ቃል ኪዳን ያስገድደናል።

«ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፤ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና» 1ቆሮ. 11:26

ቤተ ክርስቲያናት የየራሳቸው የሆነ የጌታ እራት አወሳሰድ ሥርዓት አላቸው። በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሚወሰደው በየወሩ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደሚነግረን «ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፤ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ» ማለት ከአንዱ የጌታ እራት በኋላ እስከ ሁለተኛው የጌታ እራት ድረስ አንድ አማኝ



ቢያንስ ለአንድ ሰው የጌታን ሞትና ትንሣዔ መናገር አለበት ማለት ነው። የጌታ እራት ብዙ ዓላማዎች አሉት።

- የክርስቶስ ሞትና ትንሣዔ መታሰቢያ ነው (1ቆሮ. 11:24)
- ሞቱንና ትንሣዔውን ለመመስከር ቃል የምንገባበት ነው (1ቆሮ. 11:26)
- አማኞች በክርስቶስ አንድ መሆናቸውን የሚያሳዩበት ነው (ሐዋ. 2:42)
- በአዲሱ መንግሥት ከጌታ ጋር ስምንካፈለው አዲስ እራት ምሳሌ ነው (ማቴ. 26:29)

ስለዚህም የጌታን እራት የሚካፈል አማኝ ሁሉ እስከሚቀጥለው የጌታ እራት ድረስ ቢያንስ ለአንድ ሰው ለመመስከር ቃል በገባው መሠረት ግዴታ አለበት።

ሠ. የሰማነውንና ያየነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም (ሐዋ. 4:20)።

በሐዋ. 3 ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለ40 ዓመታት ሽባ የነበረው ሰው በጴጥሮስና ዮሐንስ አገልግሎት በመፈወሱ ምክንያት በተሰበከው ወንጌል ወንዶች ብቻ ሲቆጠሩ ሦስት ሺህ የሆኑ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ሲድኑ ይህ ያበሳጫቸው የአይሁድ ሸንጎ ወኅኒ ቤት ጣሉአቸው። በነጋታው በዚህ ስም (በኢየሱስ ስም) ሁለተኛ እንዳይናገሩ ሲዝቱባቸው «እኛ ስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም» አሉ።

አማኞች መናገር የሚችሉት ብዙ ታሪክ አለ። ከሁሉ የሚበልጠው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱን፤ ከሞት መነሣቱንና ዳግመኛ ሊፈርድ መምጣቱን፤ ደኅንነት የሚገኘው በዚህ ጌታ በማመን ብቻ መሆኑን መናገር ነው። አማኞች ከዚህ የተነሣ ስላገኙት ሰላም፤ ስለሚጠብቃቸው በእጅ ያልተሠራ ስማያዊ ቤት መናገር አለባቸው።

ረ. ለበዛው መከር ሠራተኞን ለማብዛት አማኞች ሁሉ መመስከር አለባቸው።

«መከሩስ ብዙ ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው» ማቴ. 9:37። ጌታ ኢየሱስ ይህንን የተናገረው በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፤ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፤ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ሲዞር እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀውና ተጥለው ባየ ጊዜ ነው። በቁ. 36 አየ፤ አዘነላቸው የሚሉ ቃላት ትልቅ ትርጉም አላቸው። ጌታ የተጨነቁትንና የተጣሉትን አየ። ማየት ለተግባር የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ለመልካምም ሆነ ለክፉ ተግባር የመጀመሪያውን እርምጃ የሚወስደው ዓይን ነው። ሔዋን ፍሬዋን መጀመሪያ አየች ይላል። ዳዊትን የመሰለ ንጉሥ ከቤርሳቤህ ጋር ስላደረገው ኃጢአት መጀመሪያ ያደረገው ማየቱን ነበር። ጌታ የተቸገረውን ሕዝብ መጀመሪያ አየ። ወንጌልን ለመመስከር ማየት መቻል አለብን። ማየት በሥጋ ዓይን ከሆነ ከሌሎች ሰዎች የተለየ አመለካከት አይኖረንም።



እግዚአብሔር ሰውን በሚያይበት ዓይን ካየን ግን ሁለተኛው ተግባር ይከተላል።

ጌታ ካየ በኋላ «አዘነላቸው» ይላል። ዛሬ የወንጌልን ምስክርነት ደካማ ያደረገው ለሚጠፉትና ወደ ሲዖል ለሚሄዱት አለማዘን ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተላቸው፤ ደሙን ያፈሰሰላቸው ሰዎች ሲጠፉ አለማዘን የዘመናችን ትልቁ ችግር ነው።

ጌታ ኢየሱስ ካየና ካዘነ በኋላ «መከሩስ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው» አለ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያናት ወንጌልን ለማድረስ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ወንጌላዊያንንና ሚስዮናዊያንን እየላኩ ነው። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ይህ ጽሑፍ ሲዘጋጅ 1091 የአገር ውስጥና 15 ቤተሰብ የውጭ አገር ሚስዮናዊያንን በመላክ ትልቅ ምሳሌያዊት ቤተ ክርስቲያን ነች። ነገር ግን አሁንም የአገልጋይ ጥያቄ የሚያቀርቡ ቦታዎች በርካታዎች ናቸው፤ ጥያቄውም ብዙ ነው። ይህንን ፍላጎት ሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን በመላክ ብቻ ማሟላት ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። ስለዚህም እያንዳንዱ አማኝ መስካሪ መሆን አለበት።

ሰ. የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች

በመጽሐፍ ቅዱሳችን በብሉይና በአዲስ ኪዳን በፍጹም ያልታሰቡና በሰው ዘንድ የተናቁ ግን ለትልቅ የማዳን ሥራ ምክንያት የሆኑ ሰዎችን ተመዝግበው እናገኛቸዋለን።

ከእነዚህ ውስጥ ከብሉይ ኪዳን ሁለቱንና ከአዲስ ኪዳን ደግሞ ሁለቱን ለአብነት መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል::

1. ከብሉይ ኪዳን

የታናሽ ብላቴና ልጅ አስደናቂ ምስክርነት

2ነገ. 5 አንድ አስደናቂ ታሪክ ያስነብበናል:: ከሶሪያ አገር አደጋ ጣዮች ወጥተው ከእስራኤል ምድር አንዲት ብላቴና ማርከው ነበር:: ይህች ብላቴና የሶሪያ ንጉሥ አለቃ በሆነው ንዕማን ቤት አገልጋይ (ሠራተኛ) ሆና ታገለግል ነበር:: ንዕማን ግን ለምጻም ነበር:: እነዚህ ሁለት ሰዎች ምንም ሊያገናኛቸው የሚችል ሁኔታ አልነበረም:: እሱ ትልቅ ባለ ሥልጣን፤ እሷ ግን ምርኮኛ ብላቴና፤ እሱ ሶሪያዊ እሷ ደግሞ እስራኤላዊ ሁለት የተለያዩ ወገኖች፤ እሱ አሕዛብ እሷ ደግሞ እግዚአብሔርን የምታውቅ የአብርሃም ዘር የሆነች አይሁዳዊት ናቸው:: ነገር ግን ቁ. 5ን ስናነብ «ጌታዬ በሰማርያ ካለው ከነቢዩ ፊት ቢደርስ ኖሮ ከለምጹ በፈወሰው ነበር» ብላ ለእመቤትዋ ነገረቻት:: ይህ ማለት የሚያድን አምላክ፤ የሚፈውስ አምላክ፤ እናንተ ከምታመልኩት የተለየ አምላክ አለ ማለቷ ነበር:: ይህ መልእክት ለባለ ሥልጣኑ ንዕማን ትልቅ የምሥራች ነበር:: ስለዚህም ሄዶ ከተፈወሰ በኋላ እንዲህ አለ፤ «እነሆ ከእስራኤል ዘንድ በቀር በምድር ሁሉ አምላክ እንደሌለ አወቅሁ» (ቁ. 15)::

በመጽሐፍ ቅዱላችን ተአምራት የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት በብሉይ ኪዳን ሰዎች ሁሉ ከእስራኤል አምላክ



በቀር በምድር ላይ ሌላ አምላክ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ ነው:: ስለዚህም በኤሊያስ ጸሎት እሳት ከሰማይ ከወረደ በኋላ ሰዎች ሁሉ «እርሱ (እግዚአብሔር) አምላክ ነው»፤ ሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ ከእሳት ውስጥ ሲወጡ ከእሳት ውስጥ የሚያወጣ እርሱ አምላክ ነው፤ ዳንኤል ከአንበሶች ጉድጓድ ሲወጣ የዳንኤል አምላክ እርሱ አምላክ ነው» አሉ::

በአዲስ ኪዳን ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 2 ውኃን ወደ ወይን ጠጅ ሲለውጥ ክብሩ ተገለጠ፤ ብዙዎችም በእርሱ አመኑ፤ በዮሐ. 11 አልአዛርን ከሞት ሲያስነሣው ብዙዎች በእርሱ አመኑ:: ይህ ማለት የተአምራት ዋና ዓላማ በብሉይ ኪዳን ሰው ሁሉ ከእስራኤል አምላክ በቀር አምላክ እንደሌለ እንዲያውቁና በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ዓለምን የሚያድን መድኃኒት እንደሆነ እንዲያውቁ ነው::

የዚህች ታናሽ ምርኮኛ ብላቴና የምሥራች መልእክት ሶሪያዊውን ባለ ሥልጣን በእግዚአብሔር እንዲያምን አደረገው:: የወንጌል ምስክርነትን ብላቴንነት አያግደውም፤ እግዚአብሔር ብላቴኖችን ተጠቅሞ ታላላቆችን መማረክ ይችላልና:: ዛሬ በየቤተ ክርስቲያናት የሞሉ ሰዎች ከዚህች ምርኮኛ ብላቴና በብዙ መልክ ይሻላሉ፤ ነገር ግን የምሥራቹን መልእክት ይዘው ተቀምጠዋል:: ይህን ማበረታታትና ማነሳሳት የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው::

የአራት ለምጻሞች ምስክርነት

በዚያው በ2ኛ ነገሥት 7 ሌላ አስደናቂ ታሪክ እናገኛለን:: በም. 6 የሶርያ ሠራዊት የሰማርያን ከተማ እንደ ከበቡአት ከቁ. 24 ጀምሮ እናነባለን:: ከዚህም የተነሳ የሚገዛ ነገር ሁሉ እጅግ ተወድዶ ሴቶች ልጆቻቸውን ቀቅለው እስኪበሉ ድረስ ታላቅ ረሃብ ሆነ:: በዚህ ጊዜ አራቱ ለምጻሞች «እስክንሞት ድረስ በዚህ ለምን እንቀመጣለን? ወደ ከተማ እንገባ ዘንድ ብንወድ ራብ በከተማ አለ፤ በዚያም እንሞታለን፤ በዚህም ብንቀመጥ እንሞታለን:: እንግዲህ ኑ: ወደ ሶሪያውያን ሰፈር እንሸሽ፤ በሕይወት ቢያኖሩን እንኖራለን፤ ቢገድሉንም እንሞታለን» (ቁ. 3-4) ተባብለው ራብ ከሚገድላቸው እየበሉ በሶርያውያን ቢገደሉ እንዲሻል በመምረጥ ወደ ሶርያውን ካምፕ ሄዱ:: ሲሄዱ ግን ያልጠበቁት ነገር ሆነ:: እግዚአብሔር ለሶርያውያን የሰረገላና የፈረስ የብዙም ጭፍራ ድምፅ አሰምቶ ነበርና ነፍሳቸውን ያድኑ ዘንድ ሸሹ:: ስለዚህ ሲደርሱ ካምፑ ባዶ ነበር (ቁ. 5-7):: በዚህ ጊዜ የሚፈልጉትን ሁሉ በልተውና ጠጥተው፤ ወርቅ፤ ብርና ልብስ ወስደው ሲመለሱ አንድ ነገር አሰቡ:: «መልካም አላደረግንም፤ ዛሬ የመልካም የምሥራች ቀን ነው፤ እኛም ዝም ብለናል፤ እስኪነጋም ድረስ ብንቆይ በደለኞች እንሆናለን፤ ኑ፤ እንሂድ፤ ለንጉሥ ቤተ ሰብ እንናገር ተባባሉ» ይላል ቁ. 9:: ይህን የምሥራችም በነገሩአቸው ጊዜ የሰማርያ ከተማ ታሪክ ተለወጠ::



የሶርያ ሠራዊት ለከበባት ሰማርያ መድኃኒት ከአራቱ ለምጻሞች ይመጣል ብሎ ማንም አይጠብቅም:: እነርሱ ለሌላው ሲተርፉ ቀርቶ ራሳቸው ከኅብረተሰቡ የተገለሉ ነበሩ:: ነገር ግን እግዚአብሔር ተጠቀመባቸው:: ይህ ለክርስቲያኖች ትልቅ መልእክት ነው::

- የምሥራችን ቃል አለመናገር እግዚአብሔርን መበደል ነው::
- እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን የተናቁና ያልታሰቡ ሰዎችን መሣሪያ አድርጎ ይጠቀማል:
- እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ራሳችንን መስጠትና ማዘጋጀት አለብን::

2. ከአዲስ ኪዳን

ከመቃብር ሥፍራ የመጣ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው

በማር. 4:35-41 ኢየሱስ ክርስቶስ ማዕበሉን ጸጥ ካደረገው በኋላ በም. 5 ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ጌርጌሴኖን አገር እንደ መጡ እንመለከታለን:: ከታንኳይቱም በወጡ ጊዜ በመቃብር ሥፍራ ይኖር የነበረ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ወጥቶ ኢየሱስን ተገናኘው:: ይህን ሰው የያዘው ርኩስ መንፈስ ምን ያህል ክፉ እንዳደረገው ከቁ. 3-5 እንዲህ ብሎ ይገልጻል::

- በመቃብር ሥፍራ ይኖር ነበር::
- በሰንሰለት ስንኳ ማንም ሊያስረው አይችልም ነበር::

- ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር።
- ሊያሸንፈው የሚችል አልነበረም።
- ሁል ጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር።
- ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።

ይህን ሰው ኢየሱስ ከፈወሰው በኋላ ወደ ቤተ ሰቦቹ ሄዶ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት ይሰብክ እንደ ጀመር ቁ. 20 ይነግረናል። ጌታ ኢየሱስ ወደ ቤተ ሰቦቹ በምልክበት ጊዜ በእርሱ አገልግሎት በጌታ ኢየሱስ አምነው የሚድኑ ሰዎች እንዳሉ አይቶ ነበር። ክፍሉ ምን ያህል ሰዎች እንዳመኑ ባይነግረንም ከሌሎቹ ታሪክ እንደምንመለከተው ብዙ ሰዎች እንዳመኑ መገመት አያዳግትም። እግዚአብሔር ይህን ሰው ለውጦ ለክብሩ ከተጠቀመውና ለብዙዎች መዳን ከሆነ ማንነታችንና ደካማነታችን በምክንያትነት ሊቀርብ አይችልም፤ ጌታ መጠቀም ይችላልና።

ሰማርያዊት ሴት

በዮሐ. 4 ታሪኳን የምናገኘው ሰማርያዊት ሴት ውኃ ልትቀዳ የመጣችው እኩለ ቀን ላይ በጠራራ ጸሐይ ነበር። ይህን ጊዜ የመረጠችው ሌላ ሰው ወደ ውኃው ጉድጓድ የማይመጣበት ሰዓት ስለሆነ ነው፤ ምክንያቱም እርሷ ከሰው የተገለለች ሴት



ስለነበረች ከሰው ጋር እኩል ውኃ መቅዳት አትችልም ነበርና። ኢየሱስ ደግሞ ወደ ገሊላ ሲሄድ በሰማርያ በያዕቆብ ውኃ ጉድጓድ አጠገብ ማረፍ ነበረበት። ለዚህ ሁለት ምክንያቶች አሉ፤ የመጀመሪያውና ትልቁ የዚህችን ሴት ሕይወት ለመለወጥና በእርሷ አማካይነት ብዙ ወደ መንግሥቱ የሚጨመሩ ሰዎች ስለነበሩ በሰማርያ ሊያልፍ ግድ ስለሆነበት ነው። ሁለተኛው ፍጹም ሰው ስለሆነ ማረፍ ስለ ነበረበት ነው። በዚያም ጌታ የእሷን ሕይወት ስለ ለወጠው እንስራዋን ጥላ ወደ ከተማ ሄዳ ጌታ ያደረገላትን (የምሥራቹን) ነገረቻቸው። «ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት» (ቁ. 39)። ጌታ ከእነርሱ ጋር በቆየባቸው ሁለት ቀናትም የበለጠ ብዙ ሰዎች አመኑበት። ለጌታ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችም መሣሪያ ይሆናሉ።

ሸ. ቤተ ክርስቲያን የሰፋው በአማኞች ምስክርነት ነው።

መጋቢት 9 ቀን 1945 ዓ.ም. በወላይታ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊያን ሰብከት ያመኑት አማኞች የሚጠመቁበት የጥምቀት ሥርዓት በሁርጂ ይካሄድ ነበር። የኤስ አይ ኤም ሚስዮናዊ የነበሩት ሚስተር ፊሉውስ የወላይታ ወንጌላዊ የሆነውን ጊዮርግስ የተባለውን ሰው ወደ ጥምቀት ሥርዓቱ ጋበዙት። ጊዮርግስ ከጥምቀቱ ሥርዓት በኋላ ሲመለስ ማናና በተባለ ቦታ አቶ ቡጃ የተባለውን ሰው ያገኘውና ይመሰክርለታል።. ቡጃም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል

አዳኙና ጌታ አድርጎ ይቀበላል:: ጊዮርግስም የያዛትን ትንሽ መጽሔት ነገር ይሰጠውና ወደ ጨንቻ ይሄዳል:: ከጨንቻ ሲመለስ አቶ ቡጃ ለጎረቤቶቹ መስክሮ አሥር ሰዎችን ወደ ጌታ አምጥቶ ይጠብቀዋል:: ካመኑት ሰዎች አንዱ ታደሰ የተባለው ሰው ሲሆን ለሁለት ዓመታት በኪንታሮት ሕመም ይሰቃይ የነበረ ነው:: ታደሰ ጌታን ተቀብሎ ከሕመሙ ሲፈወስ በተከታታይ ይደማ የነበረውም ቆመ:: በዚህም ምክንያት ብዙ የማናና ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ተጨመሩ:: ቤተ ክርስቲያን ያደገው በዚህ ዓይነት ምስክርነት ነው::

የኤስ አይ ኤም ሚስዮናዊያን በኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ኢትዮጵያን ለቀው ሲወጡ በሦስት አጥቢያዎች የሚሰበሰቡ ከ150 የማይበልጡ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አማኞች ነበሩ:: እነዚህ አማኞች ወደ ጌታ የመጡት ሚስዮናዊያኑ ለ10 ዓመታት ዋጋ ከፍለው ካገለገሉ በኋላ ነበር:: የኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያ አርበኞች ተሸንፎ ከአገሪቱ ከወጣ በኋላ ሚስዮናዊያኑ ተመልሰው ሲመጡ ለማመን ያስቸገራቸውን ነገር አዩ:: እነርሱ ባልነበሩባቸው አምስት ዓመታት የአማኞቹ ቁጥር ወደ አሥር ሺህ ደርሷል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ወንጌልን ሰምተው ያመኑት ሁሉ ይመሰክሩ ስለ ነበረ ነው::

በ1927 ዓ.ም. አቶ ሂርቦሮና አቶ ፈረንጅ (አባቴ) ሥራ ፍለጋ ወደ ጋሞ ይሄዳሉ:: ቀን ሥራቸውን ሲሠሩ ውለው ማታ



ወደ አቻሎ እየተመለሱ ወንጌልን ይመሰክሩ ነበር:: በጋሞ አቶ ጌምቦ ሌጋሞ የተባለውን ሰው ያገኙትና ይመሰክሩለታል:: አቶ ጌምቦም ከዚህ በፊት ሚስተር አሀማን የተባለው የኤስ አይ ኤም ሚስዮናዊ በአቻሎ የተናገረውን አስታውሶ መልእክቱ ትክክለኛ እንደሆነ ያስብና በጌታ ኢየሱስ ያምናል:: አቶ ጌምቦ ደግሞ ለሌሎች ሁለት ሰዎች ይመሰክርላቸዋል:: እነዚያ ሁለት ሰዎች ደግሞ ለሌሎች ስድስት ሰዎች:: አቶ ሂርቦሮና አቶ ፈረንጅ ወደ ወላይታ ተመልሰው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነግረዋቸው ወንጌላዊ ተልኮ ቤተ ክርስቲያን ይተከላል:: ዛሬ የደቡብ ምዕራብ ቀጣና ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊ የሆኑት አቶ ሳሙኤል ጌምቦ የዚህ አገልግሎት ውጤት ናቸው::

ወንድዬ ዓሊ በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅጽ ሁለት አንድ አማኝ የጸለየውን ጸሎት እንዲህ ብሎ ይጠቅሳል:: «ጌታ ሆይ፤ እባክህ ቃልህን እንዴት አድርጌ ለሌሎች መናገር እንደምችል አሳየኝ፤ የምሥራቹን ቃል ለመናገር የሌላ ሰውን እርሻ በነጻ አያረስኩም ቢሆን ወንጌልን ልመስክር» አለ:: ይህ ሰው ምን ያህል ወንጌልን የመመስከር ጥማት እንደነበረው ከጸለየው የሞኝነት ጸሎት በቀላሉ እንረዳለን::

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየን በዓለማችን ታላላቅ የተባሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ ጌታ የመጡት በአማኞች አገልግሎት ነው:: ብዙ ሰዎች እነ ጆን ዌስሊን፣

እነ ዲ ኤል ሙዲንና ዶክተር ቢሊ ግራሃምን ያውቁአቸዋል። እነዚህን ታላላቅ ሰዎች ወደ ጌታ ያመጡት ግን እንደ እነርሱ ታዋቂ ሚስዮናዊያን ሳይሆኑ ዛሬ ስማቸው የማይታወቅ ተራ ሰዎች ነበሩ። አንዳንዶች በአባቶቻቸው ወይም በእናቶቻቸው፤ አንዳንዶች በጓደኞቻቸው፤ አንዳንዶቹም በመምህራኖቻቸውና በጎሬቤቶቻቸው የተመሰከረላቸው ናቸው።

በደቡብ ኮሪያ በዓለማችን ትልቅ የተባለውን ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት የሚመራው ያንግ ቾ በአንድ ወቅት በጠና ታሞ በተኛበት አንዲት ወጣት ልጅ ስለ ኢየሱስ መሰከረችለት። እሱም አመነ፤ ከሕመሙም ተፈወሰና ዛሬ የዓለማችን ትልቅ ሰዎች ከሚባሉት አንዱ ሆነ። በአንድ መጽሐፉ «እኔ ዛሬ ስሚን በውል የማላውቃት ወጣት ሴት ስሙን በፍጹም ልረሳው ከማልችለው ጋር አስተዋወቀችኝ» አለ።

ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በወንጌል ስርጭት ወሳኝ ሥራ መሥራት የሚችሉበትን ጸጋ እግዚአብሔር ለጥቶአቸዋል። ስለዚህም የወንጌል ስርጭትን ለናስብ ምዕመናንን ማንቀሳቀስና ጸጋቸውን መጠቀም ካልቻልን አገልግሎቱ ፍሬያማ ሊሆን አይችልም። በዚህ ምዕራፍ እንደተመለከትነው ምዕመናን ለወንጌል ስርጭት ያላቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃላፊነት አጠንክሮ ማመልከት የተፈለገውም ለዚህ ነው። ለበዛው መከር ምዕመናንን መስካሪ ካላደረግን ታላቁን ተልዕኮ መፈጸም አንችልም።



## ማጠቃለያ

ትዕዛዛት ሁሉ እኩል ዋጋ የላቸውም። አንድ ትዕዛዝ ተደጋግሞ ከተነገረና በተለይም የሚሰናበት ሰው ካዘዘ የግድ መፈጸም ያለበት ትዕዛዝ ነው ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ ታላቁን ትዕዛዝ ከትንሣዔው በኋላ ወደ አባቱ ሊያርግ ሲል ያዘዘው ሲሆን በአራቱ ወንጌላትና በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ሁሉ ተጠቅሶ እናገኛለን። በሐዋሪያት ሥራ 1:8 «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ሲል ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ አደራ ነው። በይሁዳ ያስቆርቱ ምትክ ማቲያስ እንዲተካ ሲደረግ ዓላማው የትንሣዔው ምስክር እንዲሆን ነው (ሐዋ.1:22-26)።

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለችበት ዋና ምክንያት ወንጌልን እንድትመሰክር ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ መድረስ አለበት። በዚህ ረገድ ከአማኞች የሚጠበቀው ኃላፊነት ትልቅ ነው።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጫ እየቀረበ በመምጣቱ ጠላት ዲያቢሎስም ተግቶ እየሠራ ነው። ሰው ከሰማያዊ ነገር ይልቅ በምድራዊ ነገር እንዲያተኩር፤ ከወንጌል ምስክርነት ይልቅ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን ተከታትሎ፤ ለራሱ አምልኮ፤ ለራሱ ተባርኮ ደስ ተሰኝቶ እንዲኖር እያደረገ ነው። ድግስ የሚደገሰው ለእንግዳ ነው እንጂ ለቤት አይደለም። የምንደግሰው እኛ፤ የምንበላው እኛ መሆናችን ደግሞ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ነው። አገልግሎታችን

የሰሙትን ማሰማት፤ የተባረኩትን መባረክ፤ የተጽናኑትን ማጽናናት፤ የሚያመልኩት እንዲያመልኩ ማድረግ፤ ደቀ መዛሙርቱን ደቀ መዛሙርት ማድረግ፤ ለሚያውቁት መናገር ሆኗል። ዛሬ በምድራችን እግዚአብሔር ከምን ጊዜም የበለጠ ወንጌልን የምንመሰክርበትን ዕድል ሰጥቶናል። ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 9:4 «ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል» አለ። ይህ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት የተሰጠ ቀን ነው። ነገ የሚሆነውን አናውቅም። ዛሬ እግዚአብሔር በሰጠን ጊዜ ምስክሮቹ ልንሆን ይገባናል።



# ዋቢ መጻሕፍት


Coleman, Robert E., *The Master Plan of Evangelism.* Michigan: Grand Rapids, 2001

Cotterell, F. Peter, *Born at Midnight.* Chicago: Moody Press, 1973.

Daniel, Robin, *Mission Strategies Then and Now.* Tamarisk Publications, 2012.

Elwell, Walter A. (ed.), *Evangelical Dictionary of Theology.* Michigan: Baker Book House, 1984.

Green, Michael, *Evangelism Now & Then.* Illinois: Intervarsity Press, 1979.

Greenway, Roger S, *Go and Make Disciples.* New Jersy: P & R Publishing, 1999.

Hiebert, Paul G., *Anthropological Insights For Missionaries.* Michigan: Baker Book House, 1985

Hofstede, Geert and Gert Jan Hofstede, *Cultures & Organizations: Software of the Mind.* New York: McGraw-Hill, 2005.

Kane, J. Herbert, *Christian Mission in Biblical Perspective.* Grand Rapids: Baker Books, 1976.

Moreau, A. Scott (ed.), *Evangelical Dictionary of World Missions.* Michigan: Baker Books, 2000.

Myron, Rush, *Management: A Biblical Approach.* Illinois: Victor Books, 1983.

Palau, Luis and Timoty Robnett. *Telling the Story. Evangelism for the Next Generation.* California: Ventura, 2006.

Patterson, George and Richard Scogglns. *Church Multiplication Guide.* Pasadena: California: William Carey Library, 1993.

Schilling, S. Paul, *Evangelism and Contemporary Issues.* Nashville: Tennessee: TIdings, 1962

Shultze, Quentin J., *Tele-Evangelism and American Culture.* Grand Rapids: Baker Book House, 1995.

Smith, Donald K. *Creating Understanding.* Michigan: Zondervan Publishing House, 1992.

Warren, Rick. *The Purpose Driven Church.* Michigan: Zondervan Publishing House, 1995.

Wondiye Ali. *The Ethiopian Kale Heywet Church History (Amharic), Volume I.* Ethiopia: Addis Ababa, 1998.

Wondiye Ali, Volume II.

Yesudian, Prakash, *Practical Evangelism.* Haggai Institute for Advanced leadership Training, 2001.

ወንጌል ለቤተክርስቲያናችን ቁልፍ አቢይ ተግባር ነው፡፡ ዛሬ ቤተክርስቲያናችን በዚህ አብይ ስራ ላይ ተጠምዳ ትገኛለች፡፡አገር አቀፍና ድንበርና ባሕል ዘለል ወንጌላውያን በአግር ውስጥና ከአገር ውጭም ተሰማርተው የላቀ አገልግሎት በመፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡ ዶ/ር ኢያሱ ፈረንጅ ያዘጋጀው ይህ መጽሐፍ ለዚሁ ለወንጌል አገልጋዮችና ምዕመናንም ጭምር ትልቅ ግብዓት በመሆኑ የቤተክርስቲያናችን እንዲሁም የአገራችን ቤተክርስቲያናት የወንጌል አገልጋዮችም ሆኑ ምዕመናን ሊገለገሉበት የሚገባ መጽሐፍ ነው፡፡

**ፕሮፌሰር ተከተል ዮሐንስ**
**የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ፕሬዝዳንት**

ዶ/ር ኢያሱ ፈረንጅ የወንጌላዊነት አገልግሎት ታላቅነትና ዓውዳዊ የወንጌል አገልግሎትን አስፈላጊነት ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወትና አስተምህሮ ጋር በማነጻጸር በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላለው ትውልድ ወንጌል ሳይመቻመች በምንና እንዴት ባለ መልኩ መተላለፍ እንደሚገባው ዘርዘር አድርጎ በማቅረቡ የሚያስመሰግን ሥራ ሠርቷል፡፡ መጽሐፉ እንደ አብዛኛዎቹ በወንጌል ምስክርነት ላይ የተጻፉ መጻሕፍት በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ያለ መመሪያን ብቻ የሚያቀብል ሌላ መጽሐፍ ሳይሆን በተግባር በተፈተነና በቅዱስ ቃሉ የተደገፈ ምስክርነት የወንጌላዊነትን ክብርና ዓውዳዊ የወንጌል አገልግሎትን አስፈላጊነት በግልጽ ያብራራል፡፡
በመሆኑም በተለይም ለሙሉ ጊዜና ባህል ዘለል የወንጌል አገልጋዮች ጠቃሚ ምክርን የሚሰጥ መጽሐፍ በመሆኑ በእያንዳንዱ አገልጋይ እጅ እንዲገባና እንዲጠቀሙበትም እመክራለሁ፡፡

**ዶ/ር ወንዳፈራሁ አድነው**
**የኢት/ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሚሽንስ ኤክስፐርትና አማካሪ**

ይህ መጽሐፍ ለወንጌላውያን ብቻ ሳይሆን በጌታ ኢየሱስ አምኖ የዳነ ሁሉ በምድር የሚኖርለትን ትልቁን ዓላማ አውቆ በተለያየ የባህል አውድ እንዴት ወንጌልን መመስከር እንደሚቻል የምትገልጥ ግሩም መጽሐፍ ናት፡፡ ፈር ቀዳጅና አቅጣጫ ጠቋሚ ከመሆኗ አንጻር መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምዕመናን እንዲያነቧት አበረታታለሁ፡፡ ወደ ዘመኑ ፍጻሜ በፍጥነት በምንገሰግስበት በዚህ ወቅት ከወንጌል ሥርጭት ውጪ ሌላ ምን አጀንዳ ሊኖረን ይገባል!

**መልካም ንባብ**
**ዶ/ር ኤርሚያስ ማሞ**
**የኢት/ ስነ መለኮት ድኅረ ምረቃ**
**ት/ቤት የተማሪዎች ዲን**



**ዋጋ 35 ብር**
**$10**

ርኖቦት ስታሚዎች